እፕድ
# አዲስ ዘመን
ሐሙስ
82ኛ ዓመት ቁጥር 173 የካቲት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ልዩ ዕትም

# "የዓድዋ ድል ከጊዜ ጋር ዋጋው እየጨመረ እንደሚሄድ ተቀማጭ ገንዘብ ይቆጠራል"



- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

መዓዛ ማሞ




አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ያለው ትርጉም ከጊዜ ጋር ዋጋው እየጨመረ እንደሚሄድ ተቀማጭ ገንዘብ ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የዓድዋ ድልን በማስመልከት ትናንት ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸው እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ትውልድ ሁሉ እየመነዘረ ሰላም፣ ልማት፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ጽናት፣ ጀግንነት፣ ክብርና ልዕልና ሊገዛበት የሚችል፤ ኩራትም እራትም የሚሆን፤ ቀደምቶቻችን ያስቀመጡልን አንጡራ ሀብት ነው።

ይህ አንጡራ ሀብት ባለፉት መቶ ዓመታት በተደጋጋሚ የተቃጣብንን ወረራ፣ ቅኝ ግዛትንና ቅኝ ገዥዎችን እንድንመክት አድርጎናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ ሀብቱ በማይከፋፈል ኅብረ ብሔራዊነት፣ በማይጠቀለል አንድነት ጸንተን እንድንኖር እንዳበቃን ጠቁመዋል።

የዓድዋን ድል ከፍ አድርገን እንድናከብረው የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛው ምክንያት ድሉ የሁላችንም በመሆኑ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ላይ ብንዘዋወር በዓድዋ ጦርነት ያልተሳተፉ ቀደምቶች የበቀሉበት ምድር አይገኝም ብለዋል።

ሁሉም እንደ አቅምና ችሎታው ደምና ላቡን እንዳፈሰሰ፤ አጥንት-ሥጋውን እንደገበረ፤ እውቀት

"የዓድዋ ድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## የዓድዋ ድል ታሪካዊ ይዘቱን ጠብቆ በድምቀት ይከበራል

ገጽ 4

# የዓድዋ በዓል በሶሎዳ ተራራ ስር

ጌትነት ምህረቴ

በታሪካዊቷ ዓድዋ ከተማ በሶሎዳ ተራራ ስር የጥቁር ሕዝቦች ታላቅ ድል የሆነውን የዓድዋ በዓል ለማክበር ነዋሪዎች ዝግጅት አድርገዋል። ወጣቶች ድንኳን ይተከላሉ ፤ በህብረት ሆነው ለበዓሉ ተሳታፊ የሚያሳዩትን ትርኢት አውራ መንገዱ ላይ ልምምድ ያድርጋሉ። በአውራ መንገዶች የብሄር ብሄረሰቦች ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሏል።ከተማዋ ሞቅ ደመቅ ብላለች፡፡

"የዓድዋ ድል በዓል ለእኔ ልዩ ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም ኢትዮጵያዊ አባቶቻችን ልዩነታቸውን ይዘው አንድነታቸውን ይበልጥ አጎልተው ያሳዩበት ነው።ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቋንቋ፣ ብሄር፣ ሃይማኖት ሳይገድበው በኢትዮጵያዊነቱ ተሰባስቦ ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች የተረፈ ድል የተቀናጀበት ነው። ከዚህ አኳያ በዓሉን ለእኔ ኢትዮጵያዊነቴን ከፍ አድርጌ የምዘምርበት ቀን ነው ያሉን


የዓድዋ በዓል በሶሎዳ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ ፡- እዮብ ተፈሪ






# ልዩ ዕትም



አርቲስትና ደራሲ ማህተመ ኃይሌ

## የዓድዋ ድልን የሚያጎሉ ጠንካራ የኪነጥበብ ስራዎችን ማብዛት ይገባል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድልን የአንድነት ስሜት የሚያጎሉ ጠንካራ የኪነጥበብ ስራዎችን ማብዛት ይገባል ሲሉ አርቲስቶች ተናገሩ።

አርቲስትና ደራሲ ማህተመ ኃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ ዓድዋን አስቦ ከመዋል ባለፈ ትውልዱን ለመቅረጽ ልንጠቀምበት ይገባል። በተለይ የኪነጥበብ ስራዎችን በማስፋፋት የሀገር ፍቅር ስሜትና አንድነት እንዲጎለብት ማድረግ ይቻላል፤

በኪነጥበብ ዘርፉ ስለዓድዋ ድልና አርበኞች ጀብዱ የሚገባውን ያክል ተሰርቷል ማለት አይቻልም ያለው አርቲስት ማህተመ፤ በእያንዳንዱ የአርበኛ ታሪክ ላይ ፊልምና መጽሐፍ ማዘጋጀት የሚቻልበት ዕድል አለ። በዚህ ረገድ ቀሪ የቤት ስራዎቻችንን ለይተን ለትውልዱ የሚሆን ዝግጅት በቀጣይ ማቅረብ ይጠበቅብናል ብሏል።

አርቲስትና የፊልምና የቴያትር ባለሙያዎች እንዲሁም ደራሲዎች በዓድዋ ላይ የተመረኮዙና ትውልድን ሊቀርጹ የሚችል የጥበብ ስራዎችን በትብብር መስራት የሚችሉባቸውን መንገድ ማሰብ አለባቸው ሲልም ተናግሯል።

በተለይ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ዶክመንት ተደርገው የተቀመጡ የኢትዮጵያ ጀግኖችን ታሪክ በማቀነባበር ወጥነት ያለውና አስተማሪ የሆነ ስራ መስራት የሚቻልበት ዕድል እንዳለ ጠቁሟል።

አርቲስት ሰለሞን ታፈሰ በበኩሉ የኪነጥበብ ዘርፉ ጥራት ያለውና በዕውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን ካቀረበ ፤ ወጣቱ አገር ግንባታና አንድነት ላይ የማይሳብበት ምክንያት አይኖርም። በመሆኑም የኪነጥበብ ባለሙያዎች ለሀገራችን ስንል የአርበኞችንና የአገር ወዳዶችን ታሪክ የሚያጎሉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ላይ መሳተፍ ይገባናል ብሏል።

በተለያዩ ሀገራት በሚገኙ የጦር ትምህርት ቤቶች ስለዓድዋ ድል ትምህርቶች ይሰጣል። የዓድዋ ድል አኩሪ ታሪክ ፈረንጆቹ ሳይቀር እያጠኑት በሚገኙበት ወቅት አርቲስቶችና ደራሲዎች ደግሞ ትውልዱ ይበልጥ ስለአገሩ ታሪክና አንድነት እንዲያውቅ የዓድዋን ገድሎች እያነሱ በኪነጥበባዊ ስራዎች ማስተማር ይገባል ሲል ተናግሯል።

አርቲስቶችናን ደራሲዎችም የአባቶችን የሀገር ፍቅር ስሜትና አንድነት የሚያጎሉ ትውልድ ቀራጭ የኪነጥበብ ስራዎችን በማስፋፋት ለአገር የሚጠቅሙ ክንውኖችን ማበራከት እንዳለባቸው አስተያየቱን ሰጥቷል።

አርቲስቶቹ እንዳስታወቁት፤ በዓለም ላይ ጥቂት አገራት ብቻ ናቸው የድል በዓል የሚያከብሩት፣ አብዛኛው የአፍሪካና የደቡብ አሜሪካ አገራት ጭምር የነጻነት በዓል ነው ያላቸው። ኢትዮጵያ በዓድዋ ምክንያት የድል በዓል ያላት አገር በመሆኗ ትውልዱ ስለአባቶቹ የአገር ፍቅር ስሜትና ጀግንነት ይበልጥ እንዲያውቅና በጋራ የመኖርን ባህል እንዲያዳብር በኪነጥበብ ዘርፉ መስራት ይገባል።

# ዜና

## ድሉችን ለማጽናትና ችግሮችን ለመፍታት በጋራ እንደሚሰሩ የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች አስታወቁ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር የተመዘገቡ ድሎችን በማጽናት የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በጋራ እንደሚሰሩ የአማራና ኦሮሚያ ክልል የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች በሮ ኃላፊዎች በጋራ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። የሁለቱም ክልል ከፍተኛ አመራሮች የካቲት 21 በጋራ ውይይት አድርገዋል።

የአማራ ክልል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ፤ የሁለቱም ክልሎች ከፍተኛ አመራሮች በአገራዊ እና በክልላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል። በውይይቱ እንደ ክልልም ይሁን እንደ አገር መልካም የሆኑ የልማት ስራዎችን በጋራ በማስቀጠል፣ ፈተናዎችንና ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ውጤታማ ውይይት ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ግዛቸው ገለፃ፤ ውይይቱ ሁለቱም ክልሎች በጋራ አጀንዳዎቻቸው፤ በወቅታዊ አገራዊና ክልላዊ ሁኔታ ላይ ውይይትና ግምገማ ተደርጓል። ውይይቱ አሁን የተጀመረ ሳይሆን ቀደም ሲልም በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተካሂዷል። እንደ አገር የተመዘገቡ ወሳኝ የሆኑ ድሎች አሉ። በዛው ልክ ደግሞ ተግዳሮቶች ስላሉ ችግሮችንና ፈተናዎችን በመለየት በቅንጅት ለመፍታት ስምምነት ተደርጓል።

ትልቅ ሕዝብ እንደሚመራ ክልል እንደ አንድ መንግሥት በጋራ የተመዘገቡ ድሎችን በማጽናት ለቀጣይ የብልጽግና ጉዞ የጋራ አቋሞች በመያዝና ተሞክሮ ልውውጥ የተደረገበት በመሆኑ የጋራ ክልላዊ ፈተናዎችን ለመፍታት ስምምነት መደረሱን አቶ ግዛቸው ገልጸዋል።

የአንድ ክልል ችግር ውሎ አድሮ የሌላው ክልል ችግር ስለሚሆን ችግሮቹ በሚፈቱበት መንገድና በጋራ ማለፍ በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያ ውይይት መደረጉን የገለጹት አቶ ግዛቸው፤ በክልሎች ደረጃ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፤ በሰላምና ደህንነት፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ በተለይም በግብርናው፤ በትምህርት እና በጤና ከሁለቱም ክልሎች መልካም የሚባሉ ተሞክሮዎች



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

አቶ ሃይሉ አዱኛ

አሉ። እነዚህ መልካም ስራዎች የሕዝብን ችግር የሚፈቱ በመሆናቸው የበለጠ የማጠናከር፤ የሚፈጠሩ ችግሮች እንዳሉ በዝርዝር ተቆጥረው አቅጣጫ ተቀምጦባቸዋል። ስኬቶቹና ችግሮቹ የአመራር መሆናቸው ታውቆ በቂ የሆነ አመራር መስጠት እንደሚገባ ውይይት ተደርጎባቸው የቀጣይ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሰራ ስለመሆኑ አቶ ግዛቸው ገልጸዋል፡

የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሃይሉ አዱኛ በበኩላቸው፤ በሁለቱ ክልሎች መካከል የተሰሩ የመልካም አስተዳደር፣ የልማትና መሰል ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የሚያስችል ውይይት ተደርጓል። ውይይቱ በአመራሩ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በቀጣይም በምሁራንና በአገር ሽማግሌዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ምክክር ይደረጋል ብለዋል።

እንደ አገርና እንደየ ክልሎቹ የታቀዱ እቅዶችን ለማሳካት በተቀመጠው አቅጣጫ መፍታት በሚያስችሉ ሁኔታ ላይ ውይይት ተደርጓል። ችግሮቹን በዘላቂነት በሚፈቱባቸው አንኳር ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል ነው ያሉት።

በውይይቱ በሁለቱም ክልሎች ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን በማጠናከር ልዩነቶችን በዘላቂነት መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት መደረጉን የገለጹት አቶ ኃይሉ፤ችግሮች ሳይከሰቱ መፍታትንና በጋራ መቆም ከሁሉም የተሻለ መሆኑን ግብዓት የተገኘበት መድረክ ነው ብለዋል።

የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ማጠናከር አስፈላጊ ነው ያሉት የኦሮሚያ ክልል የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ፤ አገራዊ አንድነትን ለማጽናት ምክክር አስፈላጊ መሆኑ የታመነበት ስለሆነና ቀደም ሲል ባህርዳርና አዳማ ከተሞች ላይ በተደረገው ውይይት የተቀመጡ አቅጣጫዎች አፈፃፀማቸው ተገምግሞ የተፈጸሙትንና ያልተፈጸሙትን የተለዩበትና ለቀጣይ ትግበራ ግብዓት የተገኘበት ውይይት ነው ብለዋል።

## የዓድዋን ድል በኢኮኖሚው መስክ ለመድገም ሁሉም በተሰማራበት የሙያ መስክ እንዲረባረብ ጥሪ ቀረበ

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የዓድዋን ድል በኢኮኖሚው መስክ ለመድገም እያንዳንዱ ዜጋ በየተሰማራንበት የስራ ዘርፍ የዕውቀትን ሰይፍ በማንሳት ድህነትን መዋጋት እንዳለበት ተገለጸ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፤ የሰላም ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እና የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት በጋራ በትናንትናው ዕለት 127ኛውን የዓድዋ የድል በዓልን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጽህፈት ቤት አክብረዋል።

በበዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉት የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታየ ደንደአ ፤ የዓድዋ ድል ያልሠለጠነ ማህበረሰብ የሠለጠነ ማህበረሰብን በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ ድል የመታበትና ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቁር ነጭን ያሸነፈበት ታላቅ ታሪክ ነው ብለዋል።

በጥንት አባቶቻችን መካከል የነበረው የመሪና የተመሪ የእርስበርስ መተማመን ታላቁን የዓድዋ ታሪክ ከመስራት ባለፈ በቅኝ ግዛት የተያዙ የዓለም ሀገራት ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ትልቅ የሥነልቦና ጥንካሬ እንደሆናቸው ነው አቶ ታዬ የገለፁት።

በጊዜው የመልካም አስተዳደር ችግር ቢኖርም በጦርነቱ አንድ በመሆን ለወረራ አሰፍስፎ የመጣውን የጣሊያንን የጦር ኃይል ድል መተዋል ያሉት አቶ ታየ በዚያ ጊዜ የነበረው የመልካም አስተዳደር ችግር አሁንም ባለመቀረፉ ኢትዮጵያውያን ከነጮች በተሸመተ የብሔር፣ የሃይማኖትና የቋንቋ የግጭት አጀንዳዎች እየተበጣበጥን ነው ሲሉ አቶ ታዬ አብራርተዋል።

አባቶቻችን የሰሩትን የዓድዋ ድል ታሪክ ለማስቀጠልና ለትውልድ ለማስተላለፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፕሮጀክት ቀርጾ በትኩረት እየሰራበት መሆኑን







ገልጸዋል።

“የራስን ንቆ የሌላውን አጉልቶ እድገት አይመጣም” ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው የውጭ ሀገራት ሸቀጥ ማራገፊያ ከመሆን ለመዳን በትኩረት መስራት እንደሚገባና የዕውቀትን ሰይፍ በማንሳት ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር፤ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶችን መከላከል እንደሚገባም አመላክተዋል።

የዓድዋ በዓል ግዛትንና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የተደረገ የተጋድሎ በዓል ነው። ማንኛውም ዜጋ በየተሰማራበት የስራ ዘርፍ የእውቀት፣ የጥበብና የማስተዋል ሰይፍ በማንሳት የኢኮኖሚ ለውጥ በማምጣት ታሪክ መስራት አለበት ያሉት ደግሞ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶኮ ናቸው።

ሀገራዊ እሴቶችን የሚሸረሽሩ አክራሪ ፅንፈኝነትና ብሔርተኝነት፣ ሌብነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መኖራቸውን የጠቀሱት አቶ ሰለሞን ከዓድዋ የምንማረው ኢትዮጵያዊነትን በመሆኑ በቁርሾ ታላቋን ሀገር እንዳናፈርሳት መጠንቀቅ ይገባናል ብለዋል።

ጊዜው የሳይበር ጦርነት የሚደረግበት ዘመን በመሆኑ ሀገራችን ከሳይበር ጥቃት ራሷን ለመከላከል የሳይበር አርበኞች ያስፈልጓታል፤ በትኩረትም ሊሰራበት እንደሚገባም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዳሬክተር ዶክተር ታየ ግርማ በበኩላቸው ዓድዋ የዓለም የጥቁር ሕዝቦች ኩራትና የነፃነት ተምሳሌት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ምንም አይነት የመገናኛ ቴክኖሎጂ ባልተፈጠረበት በዚያ ዘመን ከአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ሕዝቦች ተጠራርተው ፣ተግባብተውና ተናበው የዓድዋን ድል ያመጡ አባቶቻችን ሊመሰገኑ ይገባል ብለዋል።

ታሪኩን ጠብቆ በማስቀጠልና በየተሰማራንበት የሙያ ዘርፍ ኃላፊነታችንን በመወጣት ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪክ መስራት እንደሚገባም ዶክተር ታየ ገልፀዋል።

# "ዓድዋ ኢትዮጵያውያን በጥቁር ሕዝቦች ልብ ውስጥ በደማቅ ቀለም እንድንጻፍ ምክንያት ሆኗል"

- አቶ ወንደሰን ግርማ
የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር

**እፀገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ፡- ዓድዋ የቅኝ ገዢዎችን ህልም በማምከን ኢትዮጵያ በጥቁር ሕዝቦች ልብ ውስጥ በደማቅ ቀለም እንድትጻፍ ምክንያት ሆኗል ሲሉ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን ግርማ ተናገሩ።

ዳይሬክተሩ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳሉት የዓድዋ ድል የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ እንዲቀጣጠል ያደረገና መላው ጥቁር ሕዝብ ቅኝ ግዛት በቃኝ የሚልበትን አቅም እንዲያገኝ ያስቻለ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሚናቸው ላቅ ያለ በመሆኑ በመላው ጥቁር ሕዝብ ልብ ውስጥ እንዲታተም አድርጓል።

"ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም ቢሆን አገራቸው በምትነካበት ጊዜ ቀፎው እንደተነካ ንብ "ሆ" ብለው መነሳት ልማዳቸው ነው፣ ለዚህ ማሳያው ደግሞ ዓድዋ ነው" ያሉት አቶ ወንደሰን፤ የዛሬ 127 ዓመት ያከናወኑት ገድል ዛሬም ድረስ ለልጆቻቸው ስንቅ ሆኖ መብቶቻቸውን ለማስከበር ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደ ጥሩ መደላድል እያገለገለ መሆኑን ጠቁመዋል።



ዓድዋ በወቅቱ ምንም አይነት ቴክኖሎጂ ባልነበረበት ሁኔታ ሕዝቡ ከአራቱም ማዕዘን በመነሳትና በመጠራራት መረጃዎችን በመቀባበል የመጣውን የውጭ ጠላት ለመመከት በአንድነት ቆሞ የሰለጠነ የሚባለውን ጦር ገጥሞ ድል ያደረገበትና ራሱንና ሀገሩን ነጻ ያወጣበት፤ ከዛም አልፎ በመላው ዓለም ለሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች የነጻነትን ብርሃን ያበራበት ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ወንደሰን ገለጻ፤ ዛሬም ተባብረን እጅ ለእጅ ተያይዘን በየጊዜው በሚፈጠሩ ክስተቶች ሳንደናገጥና ሳንበረግግ ዓላማችንን ሳንስት አብረን እስከቆምና ጽናታችንን እስካሳየን ድረስ አንዲት የበለጸገችና ለዜጎቿ የምትተርፍ አገር ለመስራት እንችላለን ፤ በመሆኑም እነዚህን ጉልበቶቻችንን ተጠቅመን አባቶቻችን የዛሬ 127 ዓመት በፊት የፈጸሙትን ገድል የምንደግም የእነሱ ልጆች መሆናችንን ማሳየት ይገባናል ብለዋል።

በመላው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያውያን የአገራችን አቅሞች ናቸው ብለን እናምናለን የሚሉት አቶ ወንደሰን እንደየደረጃቸው አገራቸውን ሊያግዙ የሚችሉበት እውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ያላቸው በመሆኑ እነዚህን በማሸጋገር አገራቸውን ሊያግዙ እየሞከሩ ነው ብለዋል።

አቶ ወንድወሰን እንደተናገሩት የተለያዩ ዲያስፖራዎች የተሳተፉባቸው የእውቀትና የቴክኖሎጂ መስኮች ብዙ ናቸው፤ በመሆኑም እነዚህን ነገሮች አጠናክረን በመቀጠል ሀገራችንን ወደተሻለ ከፍታ ለማሻገር ሁላችንም ልንረባረብ ይገባል።

# ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ 169 የፌዴራል ተቋማት የግዢ ሥርዓታቸውን በኤሌክትሮኒክስ ይፈጽማሉ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ በቁጥር 169 የሚሆኑ የፌዴራል ተቋማት የፋይናንስ ግዢ ሥርዓታቸውን በኤሌክትሮኒክስ እንደሚፈጽሙ የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዢ ሥርዓትን ተግባራዊ ከሚያደርጉ የፌዴራል ተቋማት ጋር ምክክር አካሂዷል።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ እንደተናገሩት፤ የኤሌክትሮኒክ የግዢ ሥርዓት መንግሥት ትኩረት ከሰጣቸው ዋነኛ የስራ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። አሁን ላይ 74 የፌዴራል ተቋማት የፋይናንስ ግዢ ሥርዓታቸውን በኤሌክትሮኒክስ እየፈፀሙ እንደሆነና ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ 169 የፌዴራል ተቋማት ወደ ትግበራው እንደሚገቡ አብራርተዋል።

እንቅስቃሴዎች ከተጀመሩ አጭር ጊዜ ቢሆንም ኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓትን በመተግበር ከአፍሪካ በስድስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች ብለዋል።

ከሁለት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ በኤሌክትሮኒክስ የፋይናንስ ግዢ ሥርዓት ለአፍሪካ ሀገራት ሥልጠና መስጠት ትጀምራለች ያሉት አቶ ሃጂ፤ በቅርቡ ሁለት የአፍሪካ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ልምድ እንደሚወስዱና የማላዊ መንግሥት ባለሙያዎች ተልከው ሥልጠና እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበዋል ነው ያሉት።

"ከሞትና ከኢ-ጂፒ የሚቀር አንድም የመንግሥት ተቋም አይኖርም ሁሉም ቁርጡን ይወቅ" ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ በአዲስ አበባ ከተማና በሲዳማ ክልል ሥርዓቱን የመዘርጋት ስራዎች ቢኖሩም በ2016 ዓ.ም የፌዴራል ተቋማትን በማጠናቀቅ ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ ዘመቻው ወደ ክልሎች እንደሚዞርና በሒደት



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አቶ ሃጂ ኢብሳ

ወደ ዞንና ወረዳዎች በመውረድ በመላው ሀገሪቱ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ዓመታዊ በጀት 450 ቢሊዮን ብር ግዢ ይፈፀምበታል። ይህንን ገንዘብ ከሌብነት ማዳን ዋጋ እንዳለው ገልፀው፤ ይህ ሥርዓት መዘርጋቱ ለግዢ የሚባክነው ጊዜና ጉልበት ማዳን እየተቻለ ነው ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም በያዝነው ዓመት ብቻ 726 ጨረታዎች ግዢያቸው በኤሌክትሮኒክስ እንዲፈፀም አየር ላይ ውለዋል። ጨረታዎችን ለመሳተፍ ከክልል ከተሞች ወይም ከሌሎች ሀገራት ያባክኑ የነበረውን ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ጉልበትና ከሁሉም በላይ በዘርፉ የሚካሄደውን የሙስና ሰንሰለት ለመቁረጥ ጥረት እየተደረገ ነው።

መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓትን ለመተግበር በሚሞክርበት ወቅት የተቋማት ፍቃደኝነት እንዳልነበረ አስታውሰው፤ አሁን ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ሳይሆን እራሳቸው ወደ ተቋሙ በመምጣት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው ጥያቄ እያቀረቡ እንደሆነ አቶ ሀጂ አብራርተዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓትን በመተግበር የተሻለ አፈፃፀም ያሳዩ አራት የፌዴራል ተቋማት ማለትም፤ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተሞክሮዎቻቸውን አቅርበዋል።

ተሞክሮ አቅራቢ ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት የገጠሟቸውን ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶችን በማቅረብ ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ አድርገዋል።

በውይይቱም ተቋማት የሚገዙትን እያንዳንዷን ዕቃ ከንፁህ ውሃ ጀምሮ በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው ተገልጿል።

ከበይነ መረብ ጋር ተያይዞ የሲስተም መቆራረጥ፣ በየተቋማቱ ያለው የመሰረተ ልማት ልዩነት፣ የተቋማት ከሲስተም ውጭ ግዢ መፈጸምና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች እጥረት እንዳለ በውይይቱ የተገለፀ ሲሆን፤ ችግሮቹንም ለመፍታት ብሔራዊ የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓትን የሚቆጣጠር ቡድን እንደሚዋቀር ተጠቁሟል።



ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ

# ዓድዋ በዓለም ላይ የሰው ልጆች ሁሉ እኩል እንደሆኑ የተመሰከረበት ድል ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ዓድዋ በዓለም ላይ የሰው ልጆች ሁሉ እኩል እንደሆኑ የተመሰከረበት ድል ነው ሲሉ የቀድሞ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የታሪክ ክፍል ሃላፊና የታሪክ ተመራማሪው ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ ገለጹ።

ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች በዓድዋ ጥቁር ከነጭ ጋር እኩል መሆኑን ያረጋገጡበት፤ በዓለም ላይ የሰው ልጆች ሁሉ እኩል እንደሆኑ የተመሰከረበት የድል በዓል ነው።

የዓድዋ በዓልም በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ ሊከበር የሚገባው የነጻነት እና የአይበገሬነት በዓል ነው ያሉት የታሪክ ተመራማሪው፤ በዓሉ በዓመት ለአንድ ቀን ብቻ ተከብሮ መታለፍ የለበትም። ድንበር ዘግተንም ማክበር የለብንም እንደ ኦሎምፒክ አይነት ፕሮግራም አዘጋጅተን ለመላው ዓለም ጥሪ አድርገን ብናከብረው ከገቢም ከታሪክም አንጻር አትራፊ ሊያደርገን ይችላል ብለዋል።

ልጅ ጀርሚያስ እንደገለጹት አርበኝነት ለሌላው መስዋት መሆን በታማኝነት ለሀገር እና ለወገን እራስን አሳልፎ መስጠት ነው። ሴት አርበኞች በቀደመው ዘመን ከተዋጊነት ጀምሮ ቁስለኛ ማንሳት፣ የመዋጊያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና ማደራጀት እንዲሁም ሚስጥራዊ በሆነ የስለላ ስራ ላይ እስከመሰማራት የደረሰ ስራ ሲያከናውኑ ነበር። ስለዚህ ዓድዋ ሲከበር የሴት አርበኞችም አስተዋጽኦ የላቀ እንደነበረ ማሰብ አለብን ሲሉ ተናግረዋል።

የዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊ አርበኝነት የሚገለጸው በቴክኖሎጂ፣ በሥነምግባር በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ልማት ነው ያሉት ተመራማሪው፤ ሕዝቡ አዲስ የተከፈተብንን ዘመናዊ ወረራ በዘመናዊ የአርበኝነት መንፈስ ከመንግሥት ጋር በመሆን ሊዋጋው እንደሚገባ ተናግረዋል። ክፍተቶችን በመሙላት ከዚህ የተሻለች ሉዓላዊነቷን የምታስከብር ሀገር መፍጠር አለብን ሲሉም አክለዋል።

እንደ ልጅ ጀርሚያስ ገለፃ፤ ያደጉት ሀገራት አፍሪካን በአሁኑ ሰአት እየወረሯት ያሉት እንደ ከዚህ ቀደሙ የጦር መሳሪያ ይዘው እየመጡ አይደለም። የዘመኑ ጦርነት ባሏቸው ሚዲያዎች፣ በአለባበስ፣ በእውቀት፣ ማንነታችንን በማስለቀቅ እና በመሳሰሉት ነው። በመሆኑም እኛ ራሳችንን በመሆን ሉዓላዊነታችንን ማስመስከር አለብን ብለዋል።

እኛ ብዙ ብሄር ብሄረሰብ ያለን ሀገር እንደመሆናችን እርስ በእርሳችን እንድንጣላ እና ተጋግዘን እንዳንሰራ የሚደረግ ብዙ ሴራ አለ። በዚህ መካከል የራሳቸውን ትርፍ ለማካበት የሚሰሩ ሃይሎች አሉ። በመሆኑም በእጅ አዙር የሚደረገውን የቅኝ አገዛዝ እንደ አመጣጡ ለመመለስ መሞከር የኛ ፋንታ ነው።

አቶ ጀርሚያስ፤ ኢትዮጵያ ለጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተምሳሌት ናት። ይህንን አስጠብቃ እንድትቆይ ደግሞ የሁላችንም ሃላፊነት ነው። በተለይ የእጅ አዙር የወራሪ ሴራዎችን ቀድመን በመንቃት መመከት ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል ብለዋል።

## ልዩ ዕትም

# የዓድዋ ድል ታሪካዊ ይዘቱን ጠብቆ በድምቀት ይከበራል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ ፡- 127ኛው የዓድዋ ድል በዓል ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር የበኩሉን ኃላፊነት እንደሚወጣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር አስታወቀ።

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ በደማቅ ሥነሥርዓት እንዲከበር ለማስቻል የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር የበኩሉን ኃላፊነት ይወጣል።

በበዓሉ ዕለት አርበኞችና ቤተሰቦቻቸው የድልን ስሜት የሚያንጸባርቁ አልባሳትን ለብሰው በተለያዩ ሁነቶች እንደሚሳተፉ ገልጸዋል።

ስለሰላም፣ አንድነትና የሀገር ፍቅር የሚሰብኩ አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች ለወጣቱ እንዲተላለፉ ይደረጋል ሲሉም አስረድተዋል።

ማኅበሩ የዓድዋን ታሪክ ከማስተማር አኳያ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥትና ሕብረተሰቡ የበዓሉ አከባበር በተሻለ ሁኔታ እንዲከበርና ታሪካዊ ይዘቱን እንዳይለቅ ከማድረግ አኳያ የበኩላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይ የትምህርት ተቋማት በቀጥታ ስለሚመለከት ትክክለኛውን ታሪክ ለትውልዱ በማቅረብና በማስተማር በተጨማሪም ታሪካዊ ይዘት ያላቸው መጽሐፍትን በማሳተም ብሎም በማሰራጨት ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ጠቁመዋል።

በዓሉ በሰላም እንዳይከበር በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት ያለሙ የጥላቻ ትርክቶችን የሚነዙ አካላት ይኖራሉ። ወጣቱ እንደዚህ አይነት እኩይ ዓላማ ያላቸው አካላት የሚነዙትን የሃሰት መረጃ በጭፍን ከመከተል ሊቆጠብ ይገባል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ የዓድዋ ድል በዓል አንድነትን ከማጠናከር አኳያ ትልቅ ትምህርት ሰጪና በሃይማኖት፣ በቋንቋ እንዲሁም በብሔር ሽፋን የሚዘራውን የጥላቻና የመከፋፈል ሴራ የሚያከሽፍ ነው። ማኅበሩም ይህንን የአንድነት ዓላማ አንግቦ በዓሉ እንዲከበር ዝግጅት አድርጓል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ የዓድዋ ድል ታሪካዊ ይዘቱን ለማሳጣት በግልም ሆነ በቡድን የሚንቀሳቀሱ አካላት ይኖራሉ። ነገር ግን እንደዚህ አይነት እኩይ ተግባሮችን ከመመከት አኳያ መንግሥትና ሕብረተሰቡም በተባበረ ስሜት ታሪክን መሰረት ያደረገ በዓል እንዲከበር በቅንጅት መስራት አለባቸው።

የዓድዋ በዓል ሀገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ በዓል ነው ያሉት ልጅ ዳንኤል ጆቴ፤ በዓሉ ለመላው አፍሪካና ጥቁር ሕዝቦች ከባርነት ቀንበር ነጻ አውጥቶ እኩልነትን ለዓለም ያስተማረ በመሆኑ ከተለያዩ አገራት የሚመጡ እንግዶችም የሚታደሙበት ነው ብለዋል።

የዓድዋ ድል ጠንካራ ሀገራዊ አንድነት የሰፈነበት ድል ነው። ቀደምት አባቶቻችን በደምና በአጥንቶቻቸው ዘመን የማይሽረው ዐቢይ ታሪክ ጽፈውልን አልፈዋል። ይህን የአሸናፊነት ስሜት የሚያስቀጥል ስራ በቀጣይ መከናወን አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

ልጅ ዳንኤል አክለው እንዳስታወቁት፤ የዓድዋ ጀግኖች በዘመናቸው አኩሪ ገድል የሰሩት በቋንቋና በብሔር ሳይከፋፈሉ በአንድነት ስሜት ነው። ትውልዱም ከአባቶቹ ታሪክ በመማር በጎሳና በቡድን መከፋፈልን በማስወደግ የአገር ግንባታው ላይ በአንድነት ሊነሳ ይገባል።

ቀደም ሲል የዓደዋ ድል በዓል የሚከበረው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር በኩል ነበር ያሉት ፕሬዚዳንቱ የዘንድሮ የዓድዋ ድል ለየት ባለ መልኩ በሀገር መከላከያ ሠራዊት ስር ሆኖ በድምቀት እንደሚከበር ገልጸዋል።

# ከ 5 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የምገባ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆናቸው ተገለጸ። ስምንተኛው የአፍሪካ ተማሪዎች የምገባ ቀን ትናንት በአዲስ አበባ ተከብሯል።

ስምንተኛው አገር በቀል የአፍሪካ ትምህርት ቤት ምገባ ቀን "የአገር ውስጥ የምገባ ፍጆታ ግዥ ሥርዓትና ቀጠናዊ የአቅርቦት እሴቶችን በማሳደግ ቀጣይነት ያለው አገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባን ማሻሻል" በሚል መሪ ቃል ትናንት በአፍሪካ ህብረት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተከብሯል።

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በመርሀ ግብሩ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ መንግሥት ከትምህርት ሴክተሩ ባሻገር በብሄራዊ ማህበራዊ ፖሊሲዎች አገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባን እየተገበረ እንዳለ ጠቅሰዋል። በአሁኑ ወቅትም መንግሥት ከአጋሮቹ ጋር በመተባበር ከአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን እየመገበ መሆኑን ገልጸዋል።

በርካታ ተማሪዎች በምግብ እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እንደሚቀሩ የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ የምገባ ሥርዓቱ ይህን ችግር እንደሚቀርፍና የትምህርት ጥራቱ እንዲሻሻል አዎንታዊ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል።

የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣና የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ በዚህም ኢትዮጵያ በአሁን ወቅት ከአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን በመመገብ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዳይስተጓጎሉ ማድረግ መቻሏን ገልጸዋል።

አገር በቀል የምገባ ሥርዓቱን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመተግበር ምርትና ማርታማነትን በመጨመር ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እምርታን ማረጋገጥና የግብርና እሴት ሰንሰለቱን ማጠናከር እንደሚገባም ተናግረዋል።

አገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ የተማሪዎችን ጤንነት ለመጠበቅና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከሚያግዙ ተግባራት ውስጥ አንዱ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ እንደ አህጉርም ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት የሚደግፍ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

የሀገር ውስጥ የምግብ ግዥ ሥርዓት እና ቀጠናዊ የእሴት ትስስርን ማጠናከር የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሞችን ተደራሽ ከማድረግና የተሻለ ትምህርት ከመስጠት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ "ትናንት ስንጀምረው ቀላል ይመስል የነበረው የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ዛሬ ላይ አድጎ እና ዓለምአቀፍ እውቅናን አግኝቶ የተለያዩ ሀገራት ልምድ የሚወስዱበት ስራ በመሆኑ እጅግ ደስ ይለናል" ብለዋል።

ለተማሪዎች ምግብ ብቻ ሳይሆን ፍቅርንም በመስጠት አገራቸውን እንዲሁም አህጉራቸውን የሚወዱ ጠንካራ ትውልድ የመገንባት ስራን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

በአፍሪካ ህብረት የትምህርት፣ ሳይንስ ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ኮሚሽነር ፕሮፌሰር ሞሐመድ ቤልሆሲን በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር፤ የበለጸገችና ሠላማዊ የሆነች አፍሪካን ለመገንባት የተማሪዎች ምገባ ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል። የምገባ ሥርዓቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በፋይናንስና በቴክኒክ መደገፍ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ የአፍሪካ አገራት ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በትብብር ሥራውን እየተገበሩ እንዳለ ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የብራዚል አምባሳደር ጃንዳራ ፌረር ዶሳንቶስ፣ የትምህርት ቤት ምገባ የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ፣ የአመጋገብ ሥርዓትን የሚጠብቅ እንዲሁም የትምህርት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችን የሚደግፍ ነው ብለዋል።

በዚህ ዙሪያ ብራዚል የዳበረ ተሞክሮ እንዳላትና ይህንኑ ልምድ ለአፍሪካ አገራት ለማጋራትና ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ ተማሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት የስራ ሃላፊዎች እንዲሁም የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ተገኝተዋል።

# "የዓድዋ ድል ከጊዜ ጋር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ችሎታውን እንዳዋጣ የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አያት ቅድመ አያቶቻችን ያንን ሁሉ ዋጋ የከፈሉት ለግዛት አንድነት፤ ለኢትዮጵያዊነት ክብር እና ለሀገር ሉዓላዊነት መሆኑን ገልጸዋል። ዛሬ የምንኮራበት ማንነት፣ እንዳሻን የምንቦርቅበት ነጻነት፣ ውለን የምናድርባት ሀገር ያገኘነው በእነሱ መስዕዋትነት እንደሆነም ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት በብዙ ነገሮች ላንተሳሰር እንችላለን፤ ዓድዋ ገመድ ሆኖ ያስተሳስረናል። በብዙ ጉዳዮች ላንመሳሰል እንችላለን፤ ዓድዋ ቀለምና ቅርጽ ሰጥቶ ያመሳስለናል። በብዙ ነገሮች ላንግባባ እንችላለን፤ ቅድመ አያቶቻችንን አግባብቶ በአንድ አውድማ ያጋደለ "የዓድዋ ድል" ያግባባናል።

ዓድዋ የጎራዴና የመድፍ፣ የጦርና የጠብመንጃ፣ የጋሻና የባሩድ ፍልሚያ የፈጠረው ድል ብቻ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወኔና ጀግንነት፣ ጥበብና መደመር የተባሉ እሴቶች ውጤት ጭምር መሆኑን ጠቁመዋል።

በመሣሪያ ብዛትና ጥራት የሚበልጠንን ጠላት ያሸነፍነው በእነዚያ እሴቶች የበላይነት ስለነበረን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጣልያን የቱንም ያህል ዘመናዊ ጦር መሳሪያ ቢታጠቅ የኢትዮጵያውያንን ወኔና ጀግንነት መርታት አልቻለም፤ የቱንም ያህል ጠንካራ ምሽግ ቢገነባ የቀደምቶቻችን ድምር ጉልበት አልመከተም፤ የቱንም ያህል ባንዳዎችን በጥቅምና በድርጎ ቢያባብል ከጦር መኮንኖቻችን ዘዴና ብልሃት እንዳላመለጠም ገልጸዋል።

በነጻነትና ሉዓላዊነታችን ላይ የሚሰነዘሩ እኩይ እርምጃዎች በመከራ የወረስናት ኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ እንደበቀሉ እባጮች ቆጥረን እንፋለማቸዋለን ፤ዓድዋ ያጋመደንን ማንነት ሊበጥሱ እንደተሳሉ ምላጮች አስበን በጋራ እንታገላቸዋለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉት የዓድዋን ድል ስንዘክር አራት አካላትን ልናስታውስ ይገባል። የዘመቻው መሪዎችን፣ የጦር ዘማቾችን፣ የጦሩ ደጀኖችን እና የዘማቾቹ መሠረት የሆነውን ሕዝብ። ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ መላውን የኢትዮጵያን ጦር አስተባብረው እጅግ አስደማሚ የሆነ ዘመቻና ድል እንደመሩም ማስታወስ ይገባል።

የዓድዋ ድል የፊት አውራሪዎች ድል ብቻ አልነበረም፤ የደጀኖች ድል ጭምር እንጂ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩነት በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፤ ግጭት በዕርቅ፣ ጠብ በፍቅር፣ የግል ጥቅም በሀገር ጥቅም እንዲሸነፍ ያደረገው ሕዝቡ እንደሆነ ተናግረዋል።

የዛሬዋም ኢትዮጵያ አራቱ ኃይሎች ለአንድ ዓላማ እንዲቆሙላት ትፈልጋለች። መሪዎች፣ ዘማቾች፣ ደጀኖች እና መሠረቶች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዓላማችን አንድ ነው፤ ኢትዮጵያን በሁለመናዋ የበለጸገች አፍሪካዊት ሀገር ማድረግ እንደሆነም ጠቁመዋል።

"ዓድዋ በችግር ተተብትቦ መቅረትን አላስተማረንም፤ ዕድልን ቆጥሮ ችግርን መሻገር እንጂ" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከትናንት ይልቅ በነገ ላይ ካተኮርን፣ ሁሉን ነገር ከኢትዮጵያ በታች ካደረግን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ካጸናን፣ እንደ ጉም የከበበን ፈተና ሁሉ እንደ ጢስ በንኖ እንደሚጠፋና በድህነትና በኋላ ቀርነት ላይ፣ በመለያየትና በመከፋፈል ላይ ድሉ እንደሚደገምም አክለው ገልጸዋል።

# የዓድዋ በዓል በሶሉዳ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የዓድዋ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ማና ግደይ ናቸው።

የአሁኑ ትውልድ ከዓድዋ ድል ብዙ የሚማርበት ትልቅ መጸሀፍ ነው።እኔ፣ እኔ የምንልበትን ትተን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ አንድነቱን፣ ሰላሙን፣ ልማቱን የምናሳይበት መሆን አለበት።አሁንም ይህን ትልቅ የጥቁር ሕዝቦች የኩራት ምንጭ በዓል ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልዩነታችንን ትተን ወደ አንድ የምንመጣበት በዓል እንዲሆን እምነት አለኝ ሲሉ ገልጸዋል።

እኛም ወላጆች ልጆቻችንን ወጣቱን በሥነ ምግባር ማነጽ፤ የሰላምና አንድነትን ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን ማስተማር፣ መምከርና መገሰጽ ይጠበቅበታል ብለዋል።ይህን ማድረግ ከቻልን በቅርብ ጊዜ ዘላቂ ሰላም በማረጋገጥ ረገድ መልካም ፍሬ ማጨድ እንችላለን ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

ዓድዋ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለም የጥቁር ሕዝቦች ታላቅ ድል ነው።እናም በዓድዋ ከተማ ለዓድዋ ድል መታሳቢያ ተብሎ ይሰራል ተብሎ ቃል የተገባው የፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ እንዲሰራልን መንግሥትን እንጠይቃለን ብለዋል።

አባቶቻችን የእከሌ ብሄር ነህ፤ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ነህ፤ ሳይሉ የአንድ አገር ልጆች መሆናቸውን ተማምነው ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀውን የውጭ ወራሪ ሃይል ድል አድርገዋል የሚለው የዓድዋ ከተማ ነዋሪ ወጣት ኤፍሬም ሀጎስ፤ አንድነት ደግሞ ጥንካሬ ስለሆነ ነው አኩሪ ድል ያስገኘው።አንድነት በአገር ውስጥም ሰላም ያመጣል፤ ልማትን ያስፋፋል፤ የአሁኑ ትውልድም ከዚህ መማር አለበት ነው ያለው።

እኛ በአሁኑ ትውልዶችም አባቶቻችን ከተቀናጁት አኩሪ ድል ሚስጥሩን ተምረን እርስ በእርስ ከመጠራጠርና ከመገፋፋት ወጥተን አሁን የተገኘውን ሰላም ማጽናትና ልማትን ማፋጥን ይኖርብናል ብሏል።በተለይ ወጣቱ ትውልድም የሰላምና ልማት ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት አለበት።የአሁኑ ትውልድ ያለበት ጊዜ ብዙ ፈተና ቢሆንም ከዓድዋ ድል ብዙ ትምህርት ወስዶ ፈተናውን ለማቅለል ህብረትና አንድነቱን በማጠናከር፤ አገሩንና ሰላሙን የሚያስጠብቅ፣ ልማቱን የሚያስፋፋ መሆን ይኖርበታል ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

127ኛውን በዓል ለማክበር በመዘጋጀቴ ደስተኛ ነኝ የሚሉት በዓድዋ ከተማ አሉላ ቀበሌ ነዋሪው መምህር ገዛኸኝ በላይ፤ ዓድዋ የአባቶቻችን ትልቅ ተጋድሎ የተገኘ አኩሪ ድል ስለሆነ ልናከብረውና ትምህርት ልንወስድበት ይገባል ብለዋል።

ወጣቱ ትውልድ ሰላም፣ አንድነትና ህብረ ብሄረብሄራዊነት ድል እንደሚያስገኝ ከአባቶቻችን ትምህርት መውሰድ አለበት።ሰላምን ከሚያናጉ፤ ጥላቻን ከሚሰብኩትና ከሚለያዩ ጉዳዮች ራሱን ማራቅ ይኖርበታል።በተለይ የማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ ነገር መጠቀም አለበት ብለዋል።

ጥሩ ከተመኘን ጥሩ ካሰብን ጥሩ ከሰራን ትልቅ ተስፋ አለ።ለምሳሌ የሰላም ስምምነቱ መደረጉ፤ ከሁለት ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓድዋን በዓል እንድናከብር አድርጎናል፤ ይህን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል።ለዚህም የወጣቱ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን እንዳለበት አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ




## ዓድዋ፡- ኢትዮጵያውያን በክቡር ደም፤ ጽናትና ጀግንነት የጻፉት ታላቅ ድል!

ብዙዎች አገር ከፍ ባለ መስዋእትነት እና በታላቅ ምጥ ተወልዳ አገር እንደምትሆን ለመረዳት የሚቸግራቸውን ያህል፤ ብዙዎች የመስዋእትነቱ እና የምጡ ባለቤት በመሆን በታሪክ ውስጥ ልዩ ስፍራ የመያዛቸው እውነታ የተለመደና ዛሬም ዓለም እየሄደችበት ያለው ያልተለወጠ የጉዞ ምዕራፍ ነው።

የቀደሙት አባቶቻችንም ቢሆኑ የዛሬዪቷን ኢትዮጵያ ለዘመናት አሻግረው ለዚህ ትውልድ ያበቁት በዚሁ የተለመደ የጉዞ ምዕራፍ ነው። በየዘመኑ እንደ አገር ያጋጠሙንን ፈተናዎች (ተግዳሮቶች) በብዙ መስዋእትነት እና በታላቅ ትግል በመሻገር፤ በአሸናፊነትና በነፃነት መንፈስ የተገነባች ታላቅ አገር በመፍጠር ነው።

ይህ በአሸናፊነት ትርክት (ከፍ ባለ የሥነ ልቡና ልዕልና) የተገነባች አገር ባለቤት የመሆናችን ምስጢር፤ ስለ አገር ከፍያለ፤ መረዳት እንዲኖረን ከማድረግ ባለፈ እንደ ሕዝብ ስለአገር መሞት ክብር መሆኑን የሚያጸና የአስተሳሰብ መሠረት ላይ እንድንቆም አድርጎናል። በየዘመኑም ስለአገር በመሞት የደማቁ ታሪኮች ባለቤት እንድንሆን አስችሎናል።

ከነዚህ በመስዋእትነት ደም ከደመቁ፤ የአትንኩኝ ባይነትና የተጋድሎ ታሪካችን አንዱ እና በዋነኛው የዓድዋ ጦርነትና በጦርነቱ በየተገኘው አንጸባራቂ ድል ነው። ይህ ከእኛ አልፎ ለዓለም ጭቁን ሕዝቦች የብሩህ ነገዎች ጸዳል፤ የነፃነት ትግል ተስፋ እርሻ የሆነው ድል፤ አባቶቻችንን ብዙ ያስከፈለ፤ የአይቻልም ትርክትን የገለበጠ፤ ዛሬም የይቻላል መነቃቃት ዘር ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

አባቶቻችን ስለ ነፃነታቸው ያላቸውን ቀናኢነት በተግባር በመስዋእትነት በገዘፈ ታሪክ ለመላው ዓለም ያሳዩበት፤ አገርና አገረ መንግሥት የቱን ያህል በመስዋእትነት እንደሚፀና፤ ለዚህ የሚሆን ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣ የዓላማ ቁርጠኝነትና የመንፈስ ጽናት ያለን ሕዝቦች እንደሆንን በተጨባጭ ያሳየንበት ነው።

ለአንድ አገር ሕዝቦች ሁለንተናዊ የጋራ ልዕልናና አንድነት ብሎም ከዚህ የሚመነጭ ኅብረትና መተሳሰብ ወሳኝ አቅም እንደሆነ፤ ይህ አቅም አገርን እንደ አገር ለማስቀጠልም መተኪያ እንደማይኖረው፤ አይቻልምን ወደ ይቻላል መለወጥ የሚያስችል የተፈተነ አገራዊ ብቃት መሆኑን ጭምር ያስመሰከርንበት ነው።

በብዙ ጭቆና እና ግፍ ውስጥ የነበሩ በመላው ዓለም የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች ከግፍ ዋሻ ጫፍ የብርሃን ጭላንጭል ማየት የቻሉበትን ዕድል መፍጠር ያስቻለ፤ ነገ በዛሬ የመስዋእትነት ተጋድሎ ዘር ፍሬ ተስፋ ሆኖ እንደሚወለድ ማስተዋል የቻሉበት፤ ለዚህ የሚሆን ሥነልቦናዊ ዝግጁነት እንዲፈጥሩ ያስቻለ ነው።

ከመስዋእትነት በስተጀርባ ያለውን የነፃነት ሕይወት ተስፋ አድርገው፤ ራሳቸውን ከፍ ላለ መስዋእትነት በማዘጋጀት ለቀጣይ ትውልዶች አዲስ ነገዎችን በመስዋእትነት በደመቁ ዛሬዎች መፍጠር እንደሚቻል ከተጨባጭ ተሞክሮ መረዳት የቻሉበትን ታሪካዊ አጋጣሚ መፍጠር የቻለ ክስተት ነው።

በአጠቃላይ ዓድዋና የዓድዋ የተጋድሎ የመስዋእትነት ድል፤ ዛሬም የኢትዮጵያዊነት፣ የአንድነትና የነፃነት ዜማ የሚደመጥበት፤ የጽናት፣ የሉአላዊነት ቅኔ መወድስ የሚሰማበት በመስዋእትነት ደም የተዋጀ የነፃነት ማማ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## «... ሁሉን ነገር ከኢትዮጵያ በታች ካደረግን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ካጸናን፣ እንደ ጉም የከበበን ፈተና እንደ ጢስ በንኖ ይጠፋል»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**(የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የዓድዋ በዓል አስመልክተው ያስተላለፉት መልዕክት ሙሉ ቃል)**

**እንኳን ለ127ኛው የዓድዋ ድል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!**

የዓድዋን ድል ከፍ አድርገን እንድናከብረው የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛው ምክንያት ድሉ የሁላችንም በመሆኑ ነው። በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ላይ ብንዘዋወር በዓድዋ ጦርነት ያልተሳተፉ ቀደምቶች የበቀሉበት ምድር አይገኝም። ሁሉም እንደ አቅምና ችሎታው ደምና ላቡን አፍስሷል፤ አጥንት-ሥጋውን ገብሯል፤ እውቀት ችሎታውን አዋጥቷል። አያት ቅድመ አያቶቻችን ያንን ሁሉ ዋጋ የከፈሉት ለግዛት አንድነት፤ ለኢትዮጵያዊነት ክብር እና ለአገር ሉአላዊነት ነው። ዛሬ የምንኮራበት ማንነት፣ እንዳሻን የምንቦርቅበት ነፃነት፣ ውለን የምናድርባት አገር ያገኘነው በእነሱ መስዕዋትነት ነው። ዓድዋ የሁላችን አርማ ነው የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው።

በሁላችን እውን የሆነ፣ ለሁላችን የተበረከተ ውድ ስጦታችን በመሆኑ ዓድዋን እንደከበረ እንቁ በስስት እናየዋለን። በብዙ ነገሮች ላንተሳሰር እንችላለን፤ ዓድዋ ገመድ ሆኖ ያስተሳስረናል። በብዙ ጉዳዮች ላንመሳሰል እንችላለን፤ ዓድዋ ቀለምና ቅርጽ ሰጥቶ ያመሳስለናል። በብዙ ነገሮች ላንግባባ እንችላለን፤ ቅድመ አያቶቻችንን አግባብቶ በአንድ አውድማ ያጋደለ «የዓድዋ ድል» ያግባባናል።

ዛሬ የግዛት አንድነታችንን የሚፈታተኑ ኃይሎች ከጉያችንም ይብቀሉ ከውጭ፣ የቅድመ አያቶቻችንን አደራ ትቢያ ላይ ሊጥሉ የተነሱ ናቸውና የሁላችንም ጠላቶች ናቸው። በነፃነትና ሉአላዊነታችን ላይ የሚሰነዘሩ እኩይ እርምጃዎች በመከራ የወረስናት ኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ እንደበቀሉ እባጮች ቆጥረን እንፋለማቸዋለን። ኢትዮጵያን ለማሳነስና ኢትዮጵያዊነትን ለማኮሰስ ሌት ተቀን ሴራ የሚጎነጉኑ አካላት፤ ዓድዋ ያጋመደንን ማንነት ሊበጥሱ እንደተሳሉ ምላጮች አስበን በጋራ እንታገላቸዋለን።

ዓድዋ የጎራዴና የመድፍ፣ የጦርና የጠብመንጃ፣ የጋሻና የባሩድ ፍልሚያ የፈጠረው ድል ብቻ አይደለም። ወኔና ጀግንነት፣ ጥበብና መደመር የተባሉ እሴቶች ውጤት ጭምር እንጂ። በመሣሪያ ብዛትና ጥራት የሚበልጠንን ጠላት ያሸነፍነው በእነዚያ እሴቶች የበላይነት ስለነበረን ነው። ጣልያን የቱንም ያህል ዘመናዊ ጦር መሳሪያ ቢታጠቅ የኢትዮጵያውያንን ወኔና ጀግንነት መርታት አልቻለም፤ የቱንም ያህል ጠንካራ ምሽግ ቢገነባ የቀደምቶቻችን ድምር ጉልበት አልመከተም፤ የቱንም ያህል ባንዳዎችን በጥቅምና በድርጎ ቢያባብል ከጦር መኮንኖቻችን ዘዴና ብልሃት አላመለጠም።

በብዙ ምክንያቶች የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ያለው ትርጉም ከጊዜ ጋር ዋጋው እየጨመረ እንደሚሄድ ተቀማጭ ገንዘብ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ትውልድ ሁሉ እየመነዘረ ሰላም፣ ልማት፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ጽናት፣ ጀግንነት፣ ክብርና ልዕልና ሊገዛበት የሚችል፤ ኩራትም እራትም የሚሆን፤ ቀደምቶቻችን ያስቀመጡልን አንጡራ ሀብት ነው። ይህ አንጡራ ሀብት ባለፉት መቶ ዓመታት በተደጋጋሚ የተቃጣብንን ወረራ እንድንመክት አድርጎናል። ይህ አንጡራ ሀብት ቅኝ ግዛትንና ቅኝ ገዥዎችን እንድንመክት አድርጎናል። ይህ አንጡራ ሀብት ሊፈርሱ ነው ከተባልን በኋላም እንደ ንሥር ታድሰን እንድንበረታ አስችሎናል። ይህ አንጡራ ሀብት በማይከፋፈል ኅብረ ብሔራዊነት፣ በማይጠቀለል አንድነት ጸንተን እንድንኖር አብቅቶናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

የዓድዋን ድል ስንዘክር አራት አካላትን ልናስታውስ ይገባል። የዘመቻው መሪዎችን፣ የጦር ዘማቾችን፣ የጦሩ ደጀኖችን እና የዘማቾቹ መሠረት የሆነውን ሕዝብ። የዓድዋን ዓይነት ድል ለማምጣትም እነዚህ ኃይሎች ተስማምተው፣ ተቀናጅተውና ተናብበው ለአንድ አገራዊ ዓላማ መሥራት ነበረባቸው።

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ መላውን የኢትዮጵያን ጦር አስተባብረው መርተዋል። ተገቢውን ጊዜና ሁኔታ መርጠው፣ የውስጥ ዐቅምና የውጭ ድጋፍን አስተባብረው፣ በአመራር ጥበብና በዲፕሎማሲ ብልሃት ችግሮችን እያለፉ፤ መቶ ሺዎችን ያስተባበረና ያስተሣሠረ፣ በዓለም በንቅናቄው እጅግ አስደማሚ የሆነ ዘመቻና ድል መርተዋል። የመሪ ብልህነት ቸኩሎ በመወሰን አይታወቅም። ተገቢውን ውሳኔ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በመወሰን እንጂ። ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ በጣልያኖች ምክንያት የገባው የከብት በሽታ ለአራት ዓመታት ሕዝቡንም ከብቱንም ጎድቶት ነበር።

ከፍተኛ ረሃብም ተከሥቶ ነበር። ምንም እንኳን ጣልያን ወሰን እየገፋ መምጣቱ ቢታወቅም ክፉው ቀን እስኪያልፍ፣ መሣሪያውም ከውጭ እስኪገባ መታገስ ይፈልግ ነበር።

ባለ ሦስት እርከን ከነበረው አመራር የምንወስደው ትምህርት አለ። ከላይ ንጉሠ ነገሥቱ፤ ቀጥሎ የየአካባቢው መሪዎች፣ ከዚያም የጦር አበጋዞቹ። የየአካባቢው መሪዎች አንዳንዶቹ ከንጉሡ ጋር የማይስማሙ ናቸው። ብሔራዊ ጥቅም ግን አንድ አደረጋቸው። አንዳንዶቹ ሸፍተው ነበር። አገር ተወረረ፣ ድንበር ተደፈረ ሲባሉ ግን የግል ጠባቸውን ርግፍ አድርገው ለኢትዮጵያ ዘመቱ።

አንዳንዶቹ በነበረው የአስተዳደር ሥርዓት የማይስማሙ ነበሩ። አገር የሚያጠፋ ጠላት ሲመጣ ግን ልዩነታቸውን ችለው፣ አለመስማማታቸውን ከኢትዮጵያ በታች አድርገው ዘመቱ። ያንን ሁሉ መኳንንትና መሳፍንት፣ ያንን ሁሉ የየአካባቢ ገዥ፣ ያንን ሁሉ የየማኅበረሰቡ መሪ ለአንድ ዘመቻ ያስተባበረው ምንድን ነው?

ሥርዓቱ፣ አስተዳደሩ ወይም ርእዮተ ዓለሙ አይደለም። ከሁላችንም ኢትዮጵያ ትበልጣለች የሚለው እምነት እንጂ። ከክብራችንም፣ ከልዩነታችንም፣ ከቅሬታችንም፣ ከጠባችንም፣ ኢትዮጵያ ትበልጥብናለች ብሎ ማሰብ እንጂ። ከዚህ የምንወስደው ትምህርት አለ።

በዚህ ኅብረ ብሔራዊነትና አገራዊ አንድነት ጎልቶ በታየበት ታላቅ ዘመቻ ያልተሳተፈ ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ አልነበረም። ከየአቅጣጫው የመጡትን ብሔር ብሔረሰቦች ያግባባቸው ቋንቋ «ነፃነት» ሲሆን፤ ያንን ሁሉ ጦር ወደ አንድ ዕዝ ያመጣው ሥርዓት «ኢትዮጵያዊነት» ይባላል። ከዚያ በፊት በዚያ መጠን፣ ከአራቱ ማዕዘን የመጡ ኢትዮጵያውያን በአንድ ቦታ ተገናኝተው አያውቁም። እንደ ዛሬው ብዙሃን-መገናኛ ባልነበረበት ዘመን የአዋጁ ዜና በፍጥነት እንዲዳረስ ያደረገው በሁሉም ዘንድ የነበረው የአገር ፍቅር ስሜት ነው።

የዓድዋ ድል የፊት አውራሪዎች ድል ብቻ አልነበረም፤ የደጀኖች ድል ጭምር እንጂ። የጠላትን መረጃ ያመጡ የደኅነት ጀግኖች፤ ከተለያዩ አገራት የመሣሪያ ድጋፍ ያስገኙ የዲፕሎማሲ ጀግኖች፣ ጦሩን ሲያበረታቱ የነበሩ የኪነ ጥበብ ጀግኖች፤ ጦሩን ለዓላማ ሲያጸኑ የነበሩ የሃይማኖት አባቶች፣ ስንቅ ሲያዘጋጁና ሲያቀብሉ የነበሩ ሥራ ቤቶች፣ ቁስለኛ ሲያክሙ የነበሩ የሕክምና ጀግኖች፣ መንገድ ሲቀይሱና ሲያስተካክሉ የነበሩ የምሕንድስና ጀግኖች፣ ታሪክ ሲመዘግቡ የነበሩ ጀግኖች ነበሩ። ያልዘመተ ባለሞያ፣ ያልተሳተፈ ጥበብ አልነበረም። ልጆችና አዛውንቶች፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ሁሉም እንደሙያና ችሎታው በተለያዩ ግዳጆች ዘምቷል። ኢትዮጵያ እዚህ የደረሰችው፤ ወደፊት የምትጸናውና የምትለማውም በዚህ መልኩ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

የዚህ ሁሉ ገድልና ድል መሠረቱ ግን ሕዝቡ ነው። ጀግኖቹን ያፈራው ሕዝቡ ነው። ጀግንነት ባህላችን እንዲሆን ያደረገው ሕዝቡ ነው። ልዩነት በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፤ ግጭት በዕርቅ፣ ጠብ በፍቅር፣ የግል ጥቅም በአገር ጥቅም እንዲሸነፍ ያደረገው ሕዝቡ ነው። ስንቁን ያዘጋጀው፣ እየሸለለና እየፎከረ ጀግኖቹን የሸኘው ሕዝቡ ነው። ከየቦታው መሣሪያ አፈላልጎ ጀግና ያስታጠቀው ሕዝቡ ነው። ጦሩ ግንባር ሲዘምት አካባቢውን የጠበቀው ሕዝቡ ነው። ከድል በኋላ አገር እንዳትራብ እህል ያመረተው፣ ከብቱን የጠበቀው ሕዝቡ ነው። የተሠዉትን ልጆች ያሳደገው፣ የቆሰሉትን ጀግኖች የተንከባከበው ሕዝቡ ነው። ድል አድራጊ ሕዝብ በሌለበት ድል አድራጊ ሠራዊት እንደማይፈጠር መዘንጋት የለበትም።

**ውድ የአገሬ ልጆች፣**

የዛሬዋም ኢትዮጵያ አራቱ ኃይሎች ለአንድ ዓላማ እንዲቆሙላት ትፈልጋለች። መሪዎች፣ ዘማቾች፣ ደጀኖች እና መሠረቶች። ዓላማችን አንድ ነው፤ ኢትዮጵያን በሁለመናዋ የበለጸገች አፍሪካዊት አገር ማድረግ። በየደረጃው ያሉ መሪዎች፣ በየተቋማቱ ያሉ ዘማቾች፣ ዘማቾቹን በዕውቀት፣ በገንዘብ፣ በምክር፣ በተግሣጽ፣ በሐሳብ፣ በጥበብ የሚደግፉ ደጀኖች፣ የዚህ ሁሉ ባለቤትና ተጠቃሚ የሚሆነው ሕዝብ አንድ ሆነን ካልሠራን ግን ብልጽግና ምኞት እንጂ ሕይወት አይሆንም። እንኳን ታሪክ ሠሪ ታሪክ ዘካሪም አንሆንም።

የዓድዋ ዘማቾች ከወረርሽኝና ከተፈጥሮ ፈተና ጋር ታግለዋል፤ በአስተዳደርና በአገዛዝ መንገድ ልዩነት ነበራቸው። የውጭ ጫና ገጥሟቸዋል። የውስጥ ባንዳ ፈትኗቸዋል። ይህ ሁሉ ግን ከኢትዮጵያ በታች ነው ብለው ለአንድ ዓላማ ታግለዋል። ለአንድ ዓላማ ተሠዉተዋል። ካገኙት ይልቅ የሰጡን ይበልጣል። ከተጠቀሙት ይልቅ የጠቀሙን ይበልጣል። ለአገሩ የሚሠራ ሰው መንገዱ ይሄው ነው።

ዛሬም ፈታኞችና ፈተናዎች ከፊታችን አሉ። የጀግኖች መለኪያ ግን እነዚህን ፈተናዎች ለነገው ተስፋ ብሎ ማለፍ ነው። በተከፈለልን ዋጋ እየኖርን ነውና እኛም ለሚመጣው ትውልድ ዋጋ መክፈል አለብን። በወቅቱ ኢትዮጵያ በአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች መከበቧን፣ በውስጥ በከብት እልቂትና በረሃብ መፈተኗን ብቻ ብትመለከት ኖሮ ብርታትና ወኔ አይኖራትም ነበር። ችግሮቹን ብቻ የሚቆጥር ሕዝብ ዕድሎቹ ያመልጡታል። ዕድሎቹን ቆጥሮ የሚጸና ግን ችግሮቹን ያሸንፋል። ዓድዋ በችግር ተተብትቦ መቅረትን አላስተማረንም፤ ዕድልን ቆጥሮ ችግርን መሻገር እንጂ። ከትናንት ይልቅ በነገ ላይ ካተኮርን፣ ሁሉን ነገር ከኢትዮጵያ በታች ካደረግን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ካጸናን፣ እንደ ጉም የከበበን ፈተና ሁሉ እንደ ጢስ በንኖ ይጠፋል። ያኔ በድህነትና በኋላ ቀርነት ላይ፣ በመለያየትና በመከፋፈል ላይ የዓድዋ ድል ይደገማል።

**መልካም የድል በዓል ለሁላችንም ይሁን።**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**የካቲት 22፤ 2015 ዓ.ም**

## ልዩ ዕትም



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ዓድዋ ! የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል አርማ ፤

በዓድዋ ድል ላይ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ምሁራን የተደረጉ ጥናቶች፣ ምርምሮች፣ ደርሳናት፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎች፣ ተረኮች እና አካዳሚያዊ ሙግቶች፤ ዓድዋ ከኢትዮጵያውያን አልፎ የአፍሪካውያን ከፍ ሲልም የጥቁር ሕዝቦች ድል መሆኑን የሚተርኩ ናቸው።የዓድዋን ድል ከዚህ አንፃር ብቻ መመልከት የአሸናፊዎች ታሪክ ብቻ እንዳያደርገው እሰጋለሁ።ዳሩ ግን ታሪኩ የተሸናፊዎች፣ የቅኝ ገዥዎች፣ የተስፋፊዎች፣ የወራሪዎች፣ የነጮች ጭምር አድርገን ስናየው የዓድዋ ድል ከጥቁር ሕዝቦች ድል አልፎ የሰው ልጆች ታሪክ፣ ገድል ይሆናል።።

ጽሑፍት የዓድዋ ዘመቻ ከወሰደው ጊዜና ከሚያካልለው የቦታ ስፋት እንዲሁም በድል ከመደምደሙ አንፃር ሲታይ የ19ኛው መ. ክ .ዘ ታላቁ ጦርነት እንደሆነ ያወሳሉ።ዓድዋን አንድ እርከን ከፍ በማድረጉ ላይ ከተግባባን፤ ይሄን የሰው ልጅ ታላቅ ታሪክ ያነበሩትን መግፍኤዎች፣ መነሻዎች፣ ውጤቶችን አክለን ትምህርቱን የዘመናዊ ኢትዮጵያ እርሾነቱንም ለጋዜጣው እንዲመጥን ቀንጨብ አድርገን እንመልከታለን፤

የፈረንሳይ ቱኒዚያን የመያዝ፣ የናፒየር ዘመቻ፣ የቤልጅየሙ ንጉሥ ኮንጎን የመቆጣጠር፣ የአውሮፓውያን የተስፋፊነት ሕልም፣ የስዊዝ ካናል መገንባትን ተከትሎ የቀይ ባህር ጂኦ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ከፍ ማለቱና በወቅቱ የነበረው የዘውድ ሽኩቻ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመያዝ ለመቋመጧ በመግፍኤነት ከሚጠቀሱት ሰበቦች ዋነኞቹ ናቸው።

በጊዜው የንጉሥ ምኒልክ ወደዙፋኑ መቃረብ ያስደሰተው የጣሊያን ወኪል ፔትሮ ኢንቶኔል ግንኙነቱን በፎርማ ለማረጋገጥ ሚያዝያ መገባደጃ ላይ በ1881 ዓ.ም ውጫሌ ላይ የሁለትዮሽ ስምምነት ለመፈራረም በቃ።ስምምነቱ ስውር ደባ ያለው ቢሆንም ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው የባሪያ ንግድን ለማስቀረትና ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር ላሰበችው የንግድ ልውውጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያገለግል ነበር።።

ዳሩ ግን ውሎ ሳያድር የስምምነቱ አንቀፅ 17 ውዝግብ አስነሳ።በዚህ አንቀፅ የጣሊያንኛ ቅጅ መሠረት ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን የምታደርገው በጣሊያን በኩል እንደሆነ የሚያስገድድ መሆኑ በተዘዋዋሪ አገሪቱን በጣሊያን ሞግዚትነት የምትተዳደር ያደርጋታል።የአማርኛው ቅጂ ግን የውጭ ግንኙነት ማድረግ ትችላለች ይላል።በስምምነቱ አንቀፅ 19 ላይ የአማርኛና የጣሊያንኛ ቅጂዎች እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው መደንገጉ አለመግባባቱን አካረረው።።

በ1887 ዓ.ም በወርሀ መስከረም በገበያ ቀን ቅዳሜ አፄ ምኒልክ ታሪካዊውን የ «ወረ ኢሉን » ክተት አዋጅ አስነገሩ። «...አገርንና ሃይማኖት የሚያጠፋ ጠላት ባሕር ተሻግሮ መጥቷል።እኔም የአገሬ ሰው መድከሙን አይቼ ብታገሰውም፤ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር እርዳታ አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም።

ያገሬ ሰው ጉልበት ያለህ ተከተለኝ፤ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ እርዳኝ ፤ ...» አዋጁን ተከትሎ በአፄ ምኒልክ አዝማችነት፣ ከመላው አገሪቱ በከተቱት መኳንንትና መሳፍንት ባለሚልነት ከ100ሺህ በላይ ወዶ ገብ የገበሬ ጦር እና 29ሺ ፈረሰኞች በኢትዮጵያዊ አንድነት፣ ጀግንነት፣ ቆራጥነት፣ አልበገር ባይነት፣ ዳርድንበሩን ፤ ሉዓላዊነቱን ሊያስከብር ቀፎው እንደተነካ ንብ ወደ ሰሜን ተመመ ።ጄኔራል ባራቲየሪም ሰራዊቱን ወደ መህል ትግሬ እንዲንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጠ።።

አፄ ምኒልክ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ፋሽስታዊውና ወራሪው የጣሊያን ጦር ከግዛታቸው ለቆ እንዲወጣ ቢጠይቁም፤ ጄኔራሉ አሻፈረኝ ከማለቱ ባሻገር በዕብሪት የማይሆን ቅድመ ሁኔታ ይደረድር ጀመር፤ የአፄው ጦር ትጥቅ እንዲፈታ፣ ራስ መንገሻ እንዲታሰሩ፣ መላውን ትግሬን እንዲያስረክብ እና የጣሊያንን የበላይነት እንዲቀበል ጠየቀ።በዚህም ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑ እርግጥ ሆነ።ወራሪው ጣሊያን የመጀመሪያውን የሽንፈት ኩታውን በሁለት ሰዓት ውጊያ አምባላጌ ላይ ተከናነበ።።

የአምባላጌው አኩሪ ድል ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ላይ የተቀዳጁት የመጀመሪያው ታላቅ ፋና ወጊ ድል ቢሆንም፤ ከወታደራዊ ስኬቱ በላይ ስነ ልቦናዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነበር።ኢትዮጵያውያን የአውሮፓን ጦር ድል መንሳት እንደሚችሉ ያረጋገጡበት፤ የአፄ ምኒልክን ጦር የውጊያ ሞራል ያነቃቃ ከመሆኑ ባሻገር በአገር ውስጥም ሆነ በውጭም የንጉሡን ክብር፣ ተቀባይነት ከፍ አደረገ።።

የአፄ ምኒልክ ጦር ግስጋሴውን ቀጥሎ መቀሌን ተቆጣጠረ።ይሄን ተከትሎ ስብሀትና ሀጎስ የተባሉ ለጣሊያን ያደሩ ባንዳዎች ከድተው ለንጉሡ መግባታቸው ለወራሪው አስደንጋጭ መርዶ ነበር።የንጉሡ ጦር በወርሀ የካቲት እኩሌታ ለዓድዋ ጥቃት ዝግጁ ሆነ።የጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦር ወዲህና ማዶ ተፋጠጠ።የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በተካሄደ ጦርነት የጀኔራል ባራቲየርና የሌሎች ጄኔራሎች ጦር ተሸነፈ።ሸሸ።ተፈታ።ወደ 10ሺህ የሚጠጋ የጣሊያን ጦር ሙት፣ ቁስለኛ፣ ምርኮኛ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ድርሳናት ሲያትቱ፤ ሌሎች ደግሞ የሟቹን ቁጥር 11ሺህ፣ የተማረከውን 4ሺህ ያደርሱታል።።

ከጄኔራሎች አርሞንዲና ዳቦርሚዳ ሲሞቱ፤ በ1850ዎቹ የአገራቸውን ነፃነትና አንድነት በማስከበሩ ብሔራዊ ጀግና ከነበረው ጁሴፔ ጋሪባልዲ ጋር ይነፃፀር የነበረው የጄኔራል አርቤርቶኔ መማረክ ለጣሊያናውያን ሌላው አስደንጋጭና በሀፍረት አንገት ያስደፋ መርዶ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።ከጦር መሣሪያም መድፍ፣ 11ሺህ ጠመንጃ፣ በርከት ያለ ጥይትና ቁሳቁስ ተማርኳል።።

ከኢትዮጵያ የጦር አበጋዞችና የንጉሡ የቅርብ ባለሚሎች ጀግናውን ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ልዑል ዳምጠው ፤ ደጃዝማች መሸሻ፣ ደጃዝማች ጫጫ ፤ ቀኛዝማች ገነሜና ሌሎች ለአገራቸው ነፃነትና ሉዓላዊነት መውደቃቸውን፤ በተጨማሪም 4ሺህ ሲሞቱ 6ሺህ ኢትዮጵያውያን መቁሰላቸውን የተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ቢያትቱም ቁጥሩ ከዚህ ሊበልጥ እንደሚችል ይገምታል።።

ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እስካፍንጫው የታጠቀው የጣሊያን ጦር አፍሪካዊና ኋላቀር በሆነ የገበሬ ጦር የኢትዮጵያ ሕዝብ መረታቱ ለማመን የሚቸገር መነጋገሪያ ሆነ።አንዳንድ ምዕራባውያን ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች የኢትዮጵያውያንን ጥቁርነት እስከ መካድ ደርሰው ነበር።የታላቁ የዓድዋ ድል የአፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱ ( ብርሃነ ዘኢትዮጵያ ) ዝና በመላው ዓለም እንዲናኝ ከማድረጉ ባሻገር አገሪቱን በዓለምአቀፉ የዲፕሎማሲ መድረክ መነጋገሪያ አደረጋት።

ከአፅናፍ አፅናፍ የዓለምን ትኩረት እንድትሰብ አደረጋት።ድሉ ጥቁሮች ነጮችን ድል መንሳት እንደሚችሉ በማሳየቱ፤ በቅኝ ግዛት፣ በጭቆና ለሚገኙ የዓለም ሕዝቦች በተለይ ለአሜሪካ ጥቁሮች መነቃቃትን ፈጥሯል።ለማርከስ ጋርቬ ፤ ለፓን አፍሪካኒዝም፣ ለኔልሰን ማንዴላ ፤ ለኩዋሚ ንኩሩማህ ፤ ለስቲቭ ቢኮ እና ሌሎች ንቅናቄዎች እርሾ በመሆን አገልግሏል።ለደቡብ አፍሪካ የፀረ አፓርታይድም ሆነ ለሌሎች ለፀረ ቅኝ ግዛት ትግሎች ጉልበት ሆኖ አገልግሏል።

የአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራችን ከ20 በላይ የአፍሪካና የካሪቢያን አገራት ሰንደቅ በተለያየ ቅርፅ የመገኘቱ ምስጢርም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ተቀባይነትም የራሳቸው ጥረት እንዳለ ሆኖ መነሻው አንፀባራቂው የዓድዋ ድል ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ።አንዳንድ የፖለቲካና የታሪክ ልሂቃን የትናንቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ ) ሆነ የዛሬው የአፍሪካ ህብረት ( አ ህ ) የምስረታ ሃሳብ የዓድዋ መንፈስ የበኩር ልጅ የሆነው የፓን አፍሪካኒዝም የመንፈስ ክፋይ ነው ይሉታል።።

### የዓድዋ ትምህርት

በዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር የሆነው ሬይሞንድ ጆናስ የዓድዋን ድል ትምህርት፣ አንድምታ፣ ጥልቀት፣ ከፍታ፣ ንዑድነትና ትርጉም በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲህ ይገልፀዋል፡- « ...ምኒልክ እና ጣይቱ ወደ ሰሜን የዘመቱት ስልጣናቸውን በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ብቻ አልነበረም።...የትግራይ፣ የሸዋ ፤ የኦሮሞ ፤ የወላይታ እና የሌሎች ሕዝቦችን ውስጣዊ አንድነት በደም አስተሳስረው በጋራ ጠላት ላይ በመዝመት የጋራ አገር ለመገንባት እንጂ፤ የሕዝቦች ጥብቅ ትስስር የሚፈጠረው በእያንዳንዱ ሃይማኖት፣ ማንነት ብሔር ላይ ተመስርቶ ሳይሆን የጋራ ነፃነትን ለመቀዳጀት በሚከፈል መስዋዕትነት ነው።

ይህ ዓይነቱ መተሳሰር ብቻ ነው የኢትዮጵያ የነፃነት ከፍታ መገለጫ፤ የዓድዋ ትምህርትም ይኸው ነው።ልንታደለው የሚገባን ነፃነት ልንከላከለው የሚገባ መሆን እንዳለበት ዓድዋ ያስታውሰናል።የዓድዋ ድል ያስገኘው ነፃነት ብቻ ሳይሆን የተገኘበትን መንገድ ብናጤነው የዘመናችንም ታላቅ ወታደራዊ ድል እንድሆነ እንረዳለን።በጠመንጃ ብቻ በመታገዝ የተገኘ ድል አይደለም።የበርካቶችን ልብ በማሸነፍ እንጂ ፤ ...»

ይህ የሬይሞንድ ጥልቅ ፤ ምጡቅ የዓድዋ ትምህርት፣ ፍልስፍና ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መፅሐፍት የሚወጣው ከመሆኑ ባሻገር አዲስ አተያይን ንጻሬን የገላለጠ ነው ማለት ይቻላል።የዓድዋን ትምህርት አገራችንና ሕዝባችን ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሊተረጎም፣ ሊተነተን፣ ሊመከርበት የሚገባ ከቡድ ሀሳብ ነው።በአንድ በኩል የምንገኝበትን ዘመንና ትውልድ የዋጀ፤ ከፍ ሲልም እኛን እንደ ዜጋ ተከሳሽ ሳጥን ላይ አቁሞ በመስቀለኛ ጥያቄዎች የሚሞግት፣ የሚዳኝ ሆኖ ይሰማኛል።በሌላ በኩል በአግባቡ ተንትነን ከተረዳነው መሻገሪያ ይሆነናል።።

አዎ ! በጀግኖች አባቶቻችን ከ124 አመታት በፊት የተቀዳጀነውን ታላቁ የዓድዋ ድልም ሆነ፤ ከጣሊያን የአምስት አመቱ ቆይታ፤ ከንጉሣዊ አገዛዙ ፤ ከጊዜአዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ነፃ የወጣንባቸውን ድሎች ልንከላከላቸውና ልንጠብቃቸው ባለመቻላችን ለአንድ ምዕተ አመት ከሩብ ለዘለቀ አሳር እንደዳረገን ውድ ዋጋ እንዳስከፈሉን በጥሞና ልናንሰላስለው ይገባል።።

የሚያሳዝነው ከእነዚህ ወሳኝ የታሪክ መታጠፊያዎች ዛሬም አለመማራችን ነው።ብልጥ ብንሆን ከሌሎች የሰው ልጆች ታሪክ መማር በቻልን።እኛ ግን ከራሳችን ታሪክ መማር ባለመቻላችን ዛሬ ለምንገኝበት ቅርቃር ዳርጎናል።ከትናንቱ የ27 አመታት ግፍ፣ መከራና አሳር እንኳ መማር አልቻልንም።አይደለም የዓድዋውን፣ የአምስት አመት የጣሊያን ወረራ ፤ የደርግና የትህነግ / ኢህአዴግ ነፃነቶችን ባለፉት 23 ወራት በአደራ የተረከብነውን የነፃነት ቀብድ እንደቀደሙት ባከኖ ፤ ትርጉም አጥቶ እንዳይቀር በአግባቡ ለመጠቀም፣ ከቅልበሳ ለመከላከልና ለመጠበቅ የተዘጋጀን አይመስልም።።

ሬይሞንድ ከላይ አፄ ምኒልክ፣ እቴጌ ጣይቱ ወደ ሰሜን የዘመቱት ወራሪውን ፋሽስት ጣሊያን ድል ለመንሳት ብቻ አልነበረም።የአገሪቱን ውስጣዊ አንድነት በደም አስተሳስረው በጋራ ጠላት ላይ በመዝመት የጋራ አገር ለመገንባት እንጂ ይለናል።ይሁንና ዛሬ አገራችን ድንበርን ተሻግሮ የሚወር ጠላት ባይኖራትም ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞም ሆነ በሌሎች ፈተናዎች በብሔራዊ ጥቅሟ ጉሮሮ ላይ ለመቆም የጦር ዕቃውን ታጥቆ፣ የራስ ቁሩን ደፍቶ፣ ጡሩሩን ለብሶ ፤ ጦሩን እየሰበቀና ዘገሩን እየነቀነቀ ግዳይ ለመጣል አጋጣሚውን በንቃት የሚጠብቅ ኃይል መኖሩን ያቃለልን መሆኑን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚያ ሰሞን ፓርላማ ቀርበው አርድተውናል።በቅጡ ተረድተናቸዋል የሚል እምነት ግን የለኝም ።ለስልጣን ጥም ማርኪያ ብሔራዊ ጥቅሟን፣ አገራዊ አንድነቷን ያለምንም ማቅማማት አሳልፎ ለመስጠት በጥፍሩ የቆመ ኃይል መኖሩን አናንቀነዋል።።

የሰላማችን ፤ የአንድነታችን ፤ የሉዓላዊነታችንና የተስፋችን ስጋት የሆኑ ኃይሎችን ልናስቆማቸው የምንችለው አያት ቅድመ አያቶቻችን የዓድዋ ድል ለመቀናጀት በአንድነት እንደቆሙት ሁሉ እኛም ልዩነቶቻችንን አቆይተን ይሄን ክፉ ቀን ለማለፍ ዳር እስከ ዳር እጅ ለእጅ ተያይዘን በአንድነት መቆም ስንችል ነው።በታላቅ መስዋዕትነት እጃችን የገባ የጋራ ነፃነትን ለመከላከልና ለመጠበቅ ሌት ተቀን በንቃት መቆም አለብን።

የዓድዋ አንጸባራቂ ድል የተመዘገበው ሰው ተከፍሎለት አጥንት ተከስክሶለት፣ ደም እንደጎርፍ ፈሶለት እንጂ ዳር ቆሞ አይዞህ በማለት አይደለም።በአገራችን ሀቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአለት ላይ እንዲመሰረት መተኪያ የሌላት የአገራችን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ጣት መጠቋቆሙን፣ መጠላለፉን፣ ልዩነትን ፤ ወንዜነትን ፤ አቃቂር ማውጣቱን ፤ አቅላይነትን ፤ አሉባልታውን ፤ ወዘተ. ትተን የመፍትሔው አካል በመሆን የዜግነት ግዴታን መወጣት ይጠይቃል ።

የዓድዋ ትምህርት ሀ ሁ .... ይህ ነው ።ለአለፉት 124 አመታት ብንቆጥረው ብንቆጥረው አልገባን ፤ አልገባው ያለን የታሪክ ፊደል ።ለእነ ማዲባ ፤ አሊቨር ፤ ንኩሩማህ ፤ ማርከስ፣ ስቲቭ ቢኮ ፤ ጆሞ ፤ ሙጋቤ ፤ ቦብ ፤ ለመላው አፍሪካ ፤ ለዩናይትድ ስቴትስ መብት ተሟጋቾች ለእነ ማርቲን ፤ ሮዛ፣ ጄሲ ጃክሰን ፤ ማልኮም ኤክስ ፤ ሉዊስ ፋራካህ ፤ ኤሊጃህ ሞሀመድ፣ ኦባማ የተቆጠረው የፊደል ገበታ እኛ በአጥንት ፤ በማንነት ፖለቲካ፣ በታሪክ ምርኮኝነት፣ በታሪክ ሽሚያ ተጋርዶብን፣ ዛሬም ቅኔ፣ ምስጢር እንደሆነ አለ።

በዚህ የተነሳ የጋራ ህልም፣ ርዕይ ፤ የታሪክ ብያኔ ፤ የጋራ ጀግና ፤ የጋራ ድል ፤ የጋራ አገር ፤ የጋራ መሪ ፤ የጋራ መነሻና መዳረሻ ፤ ...፤ እንዳይኖረን አድርጓል።ግርዶሹን ለማንሳትና ከሚያለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉንን ማንነቶችን መመልከት እንድንችል በአያት ቅድመ አያቶቻችን ሰው የመሆን ኢትዮጵያዊ ንስር አይን እንመልከት ።።

### ዘመናዊ ኢትዮጵያ፤
### ባቡሩ ሰገረ ስልኩም ተናገረ ፤
### ምኒልክ መልአክ ነው ልቤ ጠረጠረ ። ።

ከታላቁ የዓድዋ ድል ማግስት ጀምሮ የአፄ ምኒልክ፣ የእተጌ ጣይቱ ፤ የኢትዮጵያ ዝና በመላው ዓለም፣ ከአፅናፍ አፅናፍ ናኘ።እንደ ዛሬው TIME መፅሔት በጊዜው ታዋቂ የነበረው " Vanity Fair " የአፄ ምኒልክን ምስል ይዞ መውጣቱ ፤ ከእነ ቻርለስ ዳርዊን ፤ ከታላቁ አሌክሳንደር፣ ከናፖሊዮን ሳልሳዊ እኩል ታዋቂ አድርጓቸዋል።አውሮፓውያን ለልጆቻቸው «ምኒልክ » የሚል ስም እስከማውጣትም ደርሰው ነበር። የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ከመላው ዓለም በሚጎርፉ ደብዳቤዎች ተጨናንቆ እንደነበርም የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት መስክረዋል።።

አፄ ምኒልክ በተቀዳጁት ሞገስ ተኩራርተው እጃቸውን አጣጥፈው ከመቀመጥ ይልቅ ይህን ዝናቸውን በመጠቀም የዘመናዊ ኢትዮጵያን መሠረት ጥለዋል።በአጭር ጊዜ ውስጥም በአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን ካቢኔአቸውን ከማቋቋም ጀምሮ 61 አዳዲስና የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን፣ አሠራሮችን፣ አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ችለዋል።ከእነዚህ ውስጥ የውሃ ቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ መብራት፣ በመንገድ የሚሄድ ሰርኪስ ባቡር፣ የሀዲድ ባቡር፣ የብረት መኪና ፤ አውቶሞቢል ይገኙበታል ።።

### እንደ መውጫ

በአፄ ቴዎድሮስ መሠረቱ የተጣለው የአገረ መንግሥት፣ የአንድነት ግንባታ ህልም ፤ በአፄ ዮሐንስ እውን ሊሆን ሲል ሞትና የእርስ በእርስ የስልጣን ሽኩቻ መንገድ ላይ አስቀርቶታል።በመጨረሻ በአፄ ምኒልክ እና በእቴጌ ጣይቱ ዋልታና ማገርነት በዓድዋ የማዕዘን ራስነት፤ በመላው ኢትዮጵያውያን ከዳንነት እውን ሊሆን ችሏል።።

ለ19ኛው መ/ክ/ዘ ታላቁ ዘመቻ ጀግኖች አባቶቻችንን ፤ እናቶቻችንን በጥበብ፣ በማስተዋል በፊታውራሪነት መርተው አኩሪ ድልንና ነፃነትን ላቀዳጁን፤ በጊዜው ዓለም ከእነ ናፖሊዎን ሳልሳዊ እኩል ክብር፣ ሞገስ የሰጣቸውን ፤ የጣሊያኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒን ከስልጣን ያወረዱትን፤ የሰው ልጆች የነፃነት ምልክት የሆኑትን አፄ ምኒልክንም ሆነ እቴጌ ጣይቱን ያለልዩነት ዕውቅና ለመስጠትና ብሔራዊ ጀግና ለማድረግ በማንነት ፖለቲካ የተቀየደው እግራችን ወደኋላ ሲጎተት ስመለከት እንደዜጋ ኃፍረት ይሰማኛል።

ባለፉት 50 አመታት በአንድ ሕዝብ ላይ አነጣጥሮ የተሠራ የጥላቻና የፈጠራ ታሪክ አገራችንን የብሔራዊ ጀግኖች ሾተላይ አድርጓት ቆይቷል።ወደፊት ለምንገነባት ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሐዊ አገር ይሄ አሜከላ፣ ኩርንችት በጥንቃቄ መለቀም አለበት።ትርክቶቻችን በሀቀኛ፣ ተጨባጭ፣ ተጠየቃዊ ፤ አመክኖአዊ እና ዘመነ ኋዴነትን contemporary በተከተለ ገለልተኛና ሳይንሳዊ ሥነ ዘዴ ላይ ሊመሠረቱ ይገባል።።

እንኳን ለታላቁ የሰው ልጆች ሁሉ የነፃነት የድል በዓል የሆነው ዓድዋ 127ኛ አመት ደረሰባችሁ።ደረሰብን።እኛ እዚያ ከፍታ ላይ መድረስ አይደለም ከማንነት ፈርማታችን ገና አልተንቀሳቀስንም።።

## ልዩ ዕትም

# ከዓድዋ ድል ሲነጠሉ የማይችሉ ተፈጥሯዊ ማንነቶች

**ግርማ መንግሥቴ**

«የሕብረ ብሔራዊ አንድነት አርማ» የሚለው በትክክል የሚገልፀው የዓድዋ ድል መልከ-ብዙ ስለመሆኑ ያረጀ ታሪክ ነው። በዓድዋ ድል የነጭ የበላይነት በጥቁር ሕዝብ ክንድ ተገርስሶ ግብአተ መሬቱ ተፈፅሟል። በዓድዋ ድል «የሰለጠነ» የተባለው የፋሺስት ጦር «አልሰለጠነም» በተባለው የሀበሻ ጦር አፈር ከድሜ በልቷል (ያውም ዓለምን ጉድ ባሰኘ የጦር መሳሪያ፤ በጥቂት ኋላ ቀር ጠመንጃዎች፣ በጦር፣ በጋሻና ጐራዴ)፤ የነጭ ወታደራዊ ስትራቴጂ በጥቁር ሕዝብ ወኔና ሕብረት ከሽፏል። የድሉ መልኮች ብዙ ነው፣ በዚሁ አቁመን ወደ ተነሳንበት እንሂድ።

ጦርነትና የደምና የአጥንት መስዋትነት የተከፈለበት የዓድዋ ድል ሲነሳም ሆነ ሲዘከር እንደ አጠቃላይ የድሉ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ላይ ይነሳ እንጂ፣ ሌሎች፣ ማለትም የመሪ ሚና የተጫወቱ ሰብእናዎች (ፐርሰናሊቲስ) የሉም ማለት አይደለም፤ አሉ። (በነገራችን ላይ፣ ይህ በዓለማችን ከታዩ ቀዳሚ ሰብዓዊ ዕልቂቶች የተመደበውን «የየካቲት 12 ሰማዕታት» ጭፍጨፋ በኃዘን የምንዘክርበት፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ የጥቁር ሕዝብ ድልና የድል ተስፋ የሆነውን የታላቁን የዓድዋ ድል በኩራት የምናስታውስበት ወር "ጥቁሮች ታሪክ ወር (Black History Month) ወይም በተለዋጭ ስሙ የአፍሪካ አሜሪካውያን ታሪካዊ ወር (African-American History Month) ተብሎ የሚዘከር መሆኑን ማስታወስ በብዙ መልኩ ጠቃሚ ነው።)

አሁን አሁን፣ እንደሌሉ የመቁጠር አባዜ ቢኖርም በዓድዋ ድል የመሪ ሚና የተጫወቱ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባለፈ የተመሪ ሚናንም ደርበው ስለ መጫወታቸው በቂ የሆነ መረጃም፣ ማስረጃም አለ። በወቅቱ መሪ የነበሩ ሰዎች ተዋጊም ሆነው በአውደ ውጊያው ላይ ድል አስመዝግበዋል።

ጥናቶች እንደሚያረጋግጡልን ከሆነ በዓድዋ ድል ዙሪያ በርካታ ስመ-ጥር መሪዎች፣ የጦር አበጋዞች፣ አዋጊ መኮንኖች፣ የተመሰከረለት ተዋጊ ሰራዊት፣ ደጀኖች . . . የነበሩ ሲሆን፣ የእነሱ ሁሉ ድምር ውጤት የዓድዋን ድል እንድንቀናጅና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የለውጥ ሐዋርያ እንድንሆን አስችሎናል።

የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍሬ ተገኝ ባለፈው አመት ባቀረቡት ጥናት እንደገለጹት፣ የዓድዋ ድል ሲነሳ የማንረሳቸው ሁለት ሰዎች አሉ፡- እነሱም እምዬ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱን። የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ለምኒልክ የሚሰጡትን ቦታ ያክል እኛ ኢትዮጵያውያን እየሰጠን ስላልሆነ ይህ በጥብቅ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው።

እንደ ዶክተሩ ጥናት ከሆነ፣ የዓድዋ ድልና ጦርነት የኢትዮጵያውያንን ጀግንነትና ድል አድራጊነት በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ እንዲታወቅ ያደረገ የድል ታሪክ ነው፤ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት፣ ርህራሄ፣ ንቅናቄና ጥንቃቄ፤ እንዲሁም፣ አገራዊ የፖለቲካ አንድነት በጉልህ የታየበትና ዓለምን ያስደመመ አመራርና የአመራር ጥበብ የተስተዋለበት፣ የላቀ ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ . . . ተግባር የተፈፀመበት ነው፤ ከዚህ ሁሉ ጀርባ "አንቱ!!!" የተባሉ ሰዎች አሉ።

ከላይ ከጠቀስናቸው በተጨማሪ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ)፣ ፊታውራሪ ገበየሁ (አባ ጎራው)፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ራስ ሚካኤል አሊ (በኋላ ንጉሥ ሚካኤል)፣ ራስ ወሌ ብጡል፣ ራስ አባተ ቧ ያለው . . . እና ሌሎች በርካቶችንም ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ «የኢትዮጵያ ታሪክ» ሥራ መመልከት ይቻላል።

በጦርነቱ የደቡቡን ውጊያ የመሩትና ለጣሊያን ባደረ ሀበሻ (ባንዳ) ጠቋሚነት ተይዘው በጣሊያን የተገደሉት ራስ ደስታ ዳምጠው («ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው / አስቀድሞ መግደል አሾክሿኪውን ነው።» የሚለው ቃል ግጥም ትዝ አይለን ይሆን?)፣

«የራሶች ራስ»፣ ታላቁ የጦር መሪ፣ «ራስ» ተብለው በንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አራተኛ የተሾሙት፣ በእንግሊዞች የጀነራልነት ማዕረግን የደረቡት፣ በታማኝነታቸውና ጀግንነታቸው የታወቁት፣ ራሱን ችሎ የሚነገር፣ የሚጠና . . . ሰብእና ያላቸው፤ ወደር የለሽ ጀግናው ራስ አሉላ አባነጋ፣ ልክ እንደ ቀድሞዎቹ ጦርነቶች ሁሉ፣ የዓድዋው ድል ባለሚል ነበሩና፣ እሳቸውንም ሆነ ሌሎችን እዚህ ስናነሳቸው በኩራት ነው።

### ሰንሰለታማዎቹ

ልክ የፈጣሪ ፍጡር የሆነው ሰው በጦርነቱ እንደ ተሳተፈ ሁሉ፣ በትግራይ ክልል በዓድዋ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ ተፈጥሯዊዎቹ ሰንሰለታማ ተራሮች (ያላያቸው እንደ ምንም ቢያያቸው)፣ ለምሳሌ ገሠሦ፣ ምንድብዳብ (በትግርኛ የተቆራረጠ ማለት ነው) ኪዳነ ምህረት ገሠሦ፣ ማርያም ሸዊት፣ ራዕዮ፣ እንዳባገሪማ ገዳም፣ ሶሎዳ ... እና ሌሎችም ከፍተኛ ውጊያ የተካሄደባቸውና የአገር ሉአላዊነትን ከማስከበር አኳያ በከፍተኛ ደረጃ ባለ ውለታ ተራሮች (እዚህ ጋ የሎሬት ፀጋዬን «ዓድዋ» ግጥም ያስታውሷል) ናቸውና ሊዘነጉ አይገባም።

ወደ ፊት አገር ሰላም ሲሆን፣ ሲሰለጥን፣ በተለይም መሰረቱ ዓድዋ ላይ የተጣለው የፓን አፍሪካኒዝም ዩኒቨርሲቲ ወደ ሥራ ሲገባ እነዚህ ቦታዎች ምን ማለት እንደሆኑ ከወዲሁ ማወቅ አያዳግትምና ለጊዜው ስማቸውን በመጥቀስ ብቻ ስናልፋቸው በዚሁ ይቀራሉ ማለታችን እንዳልሆነ ግንዛቤ እንዲያዝልን እንፈልጋለን። (ተራሮቹን «ጂኦፖለቲክስ» ከሚባለው (በፖለቲካው ዓለም) ተዝወታሪ ጽንሰሀሳብ ጋርም አስተሳስሮ መረዳት ይቻላል)

እዚህ ላይ የአዲስ አድማሱ መንግሥቱ አበበ «ያልተዘመረላቸው የዓድዋ ጀግኖችና አውደ-ውጊያዎች» በሚል ርእስ ለንባብ ባበቁት የቁጭት ጽሑፋቸው «ለወገን ጦር መሸሸጊያና መከታ፣ ለጠላት ጦር አበሳና ፈተና የሆኑት እኒያ የተፈጥሮ ተራሮች እውቅና ተሰጥቷቸው መከበር፣ መዘከርና መወደስ ቢገባቸውም፣ ዞር ብሎ ያያቸው እንኳ የለም።» በማለት ያሰፈሩትን እዚህ ሳይጠቅሱና የሀሳቡ ተካፋይ ሳይሆኑ ማለፍ ባለመቻሉ ጠቅሰነዋል።

እኝሁ ጸሐፊ አቶ አሳየ የተባሉን ምስክር በመጥቀስ «የኢትዮጵያ ጦር አሰላለፍ በአራት አቅጣጫ እንደነበር ይናገራል። ሶሎዳ ተራራ ስር፣ ከሸዋ የመጡ 400 የኦሮሞ ፈረሰኞች መሽገው ነበር። 2ኛው ከዓድዋ መውጫ፣ 3ኛው የራስ አሉላና የራስ መኮንን ጦር፣ እምባ መላክ ወይም ውጊያው በተካሄደበት ኪዳነምህረት ገሠሦ፣ በእቴጌ ጣይቱ የሚመራው 4ኛ ጦር፣ ከኪዳነምህረት ገሠሦ ጀርባና ጐን መሽጐ ነበር። የኢጣሊያም ጦር በአራት አቅጣጫ ነው የመጣው።» ሲሉም የሰዎችን፣ ጦሩን፣ ሰራዊቱንና ተራሮቹን ጥምር ሰብእናዎች ይጠቅሳሉ።

**በመጨረሻም፣**

ዛሬ፣ 127ኛውን፣ ሁለንታዊ (Universal) የሆነውን፣ የዓድዋ ድል በዓል አስመልክተን «በኩራት፣ በክብር፣ በደስታ፣ በፍቅር» (የጂጂን አገላለፅ ተጠቅመናል) ስናነሳቸው ምክንያታችን በነፃነት እየኖርነው ያለነው ሕይወትና በመላው ዓለም፣ በተለይም በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ፣ በዛሬው ዕለት እየተከበረ ያለው የድል በዓል (እንዲሁም እየተመለከትነው ያለነው የታሪክ ሽሚያ) ነውና አሁንም፣ ስማቸው «በኩራት፣ በክብር፣ በደስታ፣ በፍቅር» ሲነሳ ለዘለዓለም ይኖራል።

ዘላለማዊ ሕይወት ለዓድዋ ድል ሰማዕት አያቶቻችን!!!

# ህትመት የነቀሰው - ደማቅ የድል ታሪክ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ጊዜው ወራሪው የኢጣሊያ ጦር በሽንፈት ተዋርዶ ከምድረ- ኢትዮጵያ የተባረረበት ማግስት ነው። ግንቦት 1934 ዓ.ም። በዚህ ጊዜ በአገራችን የህትመት ሚዲያ ማቆጥቆጥ ጀምሯል። በወቅቱ የነበሩ ጥቂት ጋዜጦችም የድል ብስራትና የአሸናፊነት ገድል ዘገባዎችን በፊት ገጻቸው ይዘው ይወጣሉ።

በወቅቱ ለንባብ ከሚበቁ ጋዜጦች መካከል አንዱ የሆነው ‹‹ሰንደቅ ዓለማችን›› ጋዜጣ ከዛሬ ሰማንያ አንድ በፊት ግንቦት 5 ቀን 1934 ዓ.ም በፊት ገጹ ላይ አንድ ጽሑፍ አስነብቦ ነበር። ጋዜጣው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአፄ ምኒልክን መታሰቢያ ሐውልት ከመረቁ በኋላ በአዲስ አበባ የነበሩ የእንግሊዝ ሚኒስትርን ሲያሰናብቱ የሚታዩበትን ፎቶግራፍ ያሳያል።

‹‹ሰንደቅዓላማችን›› የተባለው ይህ ጋዜጣ በወቅቱ በመታሰቢያነት የቆመውን የዳግማዊ አፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሐውልት ጭምር በፎቶግራፍ ቀርጾ ለእይታ አብቅቷል። ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐውልቱን በገሀድ ከመረቁ በኋላ መታሰቢያውን ለሚያዩ፣ ታሪኩን ለሚሰሙ ሁሉ ያስተላለፉትን ድንቅ መልዕክት በፊት ገጹ ዘግቧል።

ይህ ‹‹ሰንደቅ ዓላማችን›› የተሰኘ ቀደምት ጋዜጣ የጀግንነት ትውስታዎችን፣ የዓድዋን ድል መታሰቢያንና የታሪካዊ ጠላቶቻችን ሽንፈት ለመላው ዓለም ‹‹ይድረስ›› ሲል የዘገበው በዚህ መልኩ ነበር። እነሆ ! ትውስታ።

**‹‹ታሪክ አይደመሰስም መታሰቢያ አይማረክም ››**

በዓለም ላይ ሥም ያለው ነገር ሁሉ ካለፈ በኋላ ቀሪ ሆኖ ለትውልድ የሚቆይለት ሀብት ታሪኩ እና መታሰቢያው ነው። ሁሉ ሲያልፍ የማያልፍ ስለሆነ ታሪክ አይደመሰስም፣ መታሰቢያም አይማረክም። በግፍ የተነሳ የጦር ሰራዊት ሊፈጥረው የማይችለውን ፍጥረት፣ ለማጥፋት ያልገዛውን አገር ለማስገበር ያላረባውን ከብት ለመቀማት፣ ባልሰራው ቤት ለመግባት፣ በወራሪነት በዘመተበት አውራጃ የአጥቂነት ኃይል ይሰማውና በጦር አንደበት፣ በፈረስ አንገት ምርኮ ለመንዳትና የሰውን ዘር ለመደምሰስ ይቻል እንጂ ታሪክን ለመደምሰስና መታሰቢያን ለመማረክ አይችልም።

**አበባ ከገቡ በኋላ የቀድሞዎቹን ጋዜጦቻችንን ታሪኮችንና መጽሐፍቶቻችንን ሁሉ አጠፏቸው፡፡ ሥዕሉ ሁሉ ከየቤተክርስቲያኑ ተላጠ። ትዕምርተ መንግሥታችንና አርማችን ሁሉ ተጣለ፡፡ ነገርግን ይህ ሁሉ ተሰብስቦ በልባችን እንደተከማቸ አሳወቁም**

መታሰቢያና ታሪክ የማይጨልም ፋና ነውና ጠላት ምንም ጥላውን ቢጥልበት ወጋገኑ መታየቱ አይቀርም። ያለፈው ዓለም ሁሉ ፍለጋውንና መታሰቢያውን ለታሪኩ እየተወ ስላለፈ በተመስጦ ሆኖ ለተመለከተው መኖሩ እንጂ ማለፉ አይታሰብም።

የታሪክ አስተዋይነት የተሰጠው ግርማዊነታቸው የዳግማዊ ምኒልክን ሐውልት ባቋቋሙበትና በመሠረቱበት በታወቀው በሚያዝያ 27 ቀን ታላቅ የታሪክ ሐውልት ግርማዊነታቸው በተናገሩት ቃል በጥልቅ መሠረት ላይ ተመሠረተ። ይኸውም የሚያመለክተው የታሪክን አለመደምሰስና የመታሰቢያን አለመማረክ ነው።

ከሦስት ሺህ ዘመን በፊት ጥንታዊ በመባልና ነፃ መንግሥት በመሆን የታወቀውና ክብሩ የላቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ከብዙ ዘመናት በኋላ ምንም በፋሽስት ቢወረር ታሪኩ አልተደመሰሰም፣ መታሰቢያው አልተወረሰም። እስከመቼም ድረስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የማይረሳው የአጼ ምኒልክ ሐውልት በአምስቱ ዓመት ውስጥ ከስፍራው ቢነቀል ከልባችን አልተቀለም።

የኢትዮጵያም የጀግንነት ታሪክ በጠላት ዘንድ የተደመሰሰ ቢመስል በሌላው ዓለም ፊት አልተደመሰሰም፡ ፡‹‹ረስቼሽ እንደሆን ቀኙ ትርሳኝ›› የተባለው ቃል መታሰቢያ የማይረሳ መሆኑ ያስታውቃል። ልብና መታሰቢያ እናትና ልጅ ናቸው። እናት የወለደችውን እንዳትረሳ ልብም የአገሩን ታሪክና የወገኑን መታሰቢያ አይረሳም።

የሰውንና የዓለምን መጠን በሚገምቱ በሊቃውንት ዘንድ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ህፀፅ ወይም ጉድለት አልተገኘበትም። ምክንያቱም ግርማዊ ጃንሆይ ‹‹ታሪክ አይደመሰስም፣ መታሰቢያ አይማረክም ›› ብለው በተናገሩት ቃል ታውቋል።

ኢጣሊያኖች ባለፈው አምስት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያን ይዘው ሳለ የቀድሞውን የዓድዋ ታሪክ ለመደምሰስና መታሰቢያውንም ለማጥፋት ጣሩ። ነገር ግን የጦርነቱ ወሬ ይቅርና የአገሩ ስም ‹‹ዓድዋ›› ተብሎ ቢጠራ ለልብ የሚታሰበው የእነሱ ድል መሆንና የእኛ ድል ማድረግ ነበር።

ከቶውንም ዓድዋ ሲነሳ ይደነግጣሉ፣ አይወዱም፣ ዝግንን፣ ዝግንን ይላቸዋል። እንዲሁም ጣሊያኖች ድል የሆኑባቸው ተራሮች ሁሉ መታሰቢያነታቸውንም አላስማረኩም። አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የቀድሞዎቹን ጋዜጦቻችንን ታሪኮችንና መጽሐፍቶቻችንን ሁሉ አጠፏቸው። ሥዕሉ ሁሉ ከየቤተክርስቲያኑ ተላጠ። ትዕምርተ መንግሥታችንና አርማችን ሁሉ ተጣለ። ነገርግን ይህ ሁሉ ተሰብስቦ በልባችን እንደተከማቸ አላወቁም።

አንበሳችን ከትዕምርተ - መንግሥታችን ላይ ቢታጣ ልባችን የአንበሳ ቦታ ሆኖ ነበር። ይህን ሁሉ ለማስረዳት ግርማዊ ጃንሆይ ባጭሩ ‹‹ታሪክ አይደመሰስም፣ መታሰቢያ አይማረክም›› ብለው ተናገሩ። የታሪክ መዝገብና የሐውልት አደባባይ ልብ ነው እንጂ ወረቀትና መሬት አይደለም። ንጉሠ ነገሥታችን ከቤተ መንግሥታችን በተሰደዱ ጊዜ እንዳልተሰደዱ ያህል ልቦናችንን ዙፋን፣ ሰውነታችንን ድንኳን አድርገው ስለነበር መታሰቢያቸው ሊማረክና ታሪካቸው ሊደመሰስ አልተቻለም።

በግዙፍነት ከሚታየው ይልቅ በአሳብ ዓይን በረቂቅነት የሚታየው ጉልህ ይሆናል። በአምስቱ ዓመቶች ውስጥ ብዙ ታላላቆች የኢጣሊያ መታሰቢያዎች በግዙፍነትና በልዩ ልዩ አሠራር በየአደባባዩ ቆመው ነበር። ነገር ግን ለዓይናችን የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እንኳን ሆኖ አይታየንም።

ካለው ይልቅ ጎልቶ የሚታየን የሌለው ነበር። ምድሩ ሁሉ ምስክርና አስታዋሽ ሆኖ የሚያሳስበን እኛኑ የቀደመውን ታሪክና ክብር እንጂ የኢጣሊያኖችን አምባገነንነትና ዘመናይነት አልነበረም። በዚህ ባለፈው በአምስት ዓመት ውስጥ የተደረገውንና ዛሬ የሚደረገውን ብናመዛዝነው የዘመን ብዛትና የትውልድ መተላለፍ ሊያስረሳው የማይቻል ነገር ነው።

‹‹ከትልቅ ወይም ከትንሽ መወለድ ሙያ አይደለም። ራስን ለታላቅ ታሪክ መውለድ ግን ሙያ ነው›› ተብሎ ከግርማዊነታቸው እንደተነገረው ኢትዮጵያ ራሷን ለታላቅ ታሪክ የወለደችው ምንም ከብዙ ሺ ዘመን በፊት ቢሆን ዛሬ ደግሞ የበለጠ አድርጋ ስለወለደችው የቀዳማዊ የታሪክ እናት መሆኗ በደኃራዊ የታሪክ እናትነቷ ታወቀ።

ከፍ ያለ ታሪካቸውን ከራሳቸው የወለዱ አርበኞች ተወልደው አዲስነቷን ሊመሰርቱላት በመቻላቸውና መታሰቢያቸውን እንደማይረሳ አድርገው በማደላደላቸው የኢትዮጵያ የክብር ስም ከስም በላይ ሆነ። ይህም በዓለም ለሚኖር ሰው ሁሉ ምንም ሊያደርገው የሚገባ ነገር ቢሆን በኢትዮጵያ በልጦ ሊገኝ ያስፈልጋል።

‹‹ሰንደቅዓላማችን›› የተሰኘው ጋዜጣ ዛሬን በህትመት ላይ የለም። በጊዜው ዘመኑን ዋጅቶ ያሰፈረው ደማቅ ታሪክ ግን ዓመታትን ተሻግሮ እንዲህ መነበብ ችሏል። ጋዜጣው በፊት ገጹ ነቅሶ ያቆየው እውነታም የኢትዮጵያን የማይፋቅ ድንቅ ታሪክ የሚያወሳ ህያው ምስክር ነው ።

# ልዩ ዕትም

# «አገራችን ለመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦችና ለተጨቆኑ በሙሉ የይቻላል መንፍስን የሰጠች ነች»

- ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን
የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት



ቤዛ እሸቱ

ዛሬ በቅኝ ያለመገዛታችን ምስጢር፤ አንገትን ቀና አድርጎ የመሄዳችን መነሻ የሆነው የዓድዋ የድል በዓል 127 ዓመቱ ነው። ስንወድ እንጂ ሁሉን ማለፋችን ስንናቅ ስንደፈር የማንወድ መሆናችንን በአገር ከመጡ ሁሉም ለመሞት ዝግጁ መሆኑን ያሳየበት ድላችን ነው። የአሁኑ ትውልድ ከቀደምት አባቶቹ ምን ይማር? ስንል የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ከሆኑት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ጋር ቆይታ አድርገናል። ያደርግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አሰናድተነዋል።።

**አዲስ ዘመን፡- የአሁኑ ትውልድ ከጥንት አርበኞች ተጋድሎና ከዓድዋ ድል ምን መማር አለበት?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** ኢትዮጵያ ብዙ ወዳጆች ያሏት፤ በዚያው ልክ ደግሞ ጠላቶችም ያሏት አገር ነች። አገራችን ነፃነቷን አስከብራ መስዋእት ሆና እንኳን ለኢትዮጵያ ለመላው ዓለም ጥቁር ሕዝብና ለተጨቆኑት በሙሉ የይቻላልን መንፈስ የሰጠች አገር ነች። ኢትዮጵያ ይሄንን የይቻላል መንፈስ ስትሰጥ፤ የይቻላል መንፈስን የተረከቡትና ያዳመጡት ሁሉም ቅኝ ተገዥዎች ነበሩ።

ኢትዮጵያ የዓድዋን ድል እንደዚህ በቀላሉ አላሸነፈችም። ብዙ መስዋእት ተከፍሏል። ብዙ ሰው ሞቷል፤ አጼ ምኒልክ ነጋሪት አስጎስመው ‹‹ወረኢሉ ላይ እንገናኝ›› ሲሉ፤ የኦሮሞው፣ የአማራው፣ የትግሬው፣ የሲዳማው፣ የከንባታው፣ የሶማሌው አገራችን ተደፈረች በሚል ስሜት በአንድ ላይ የተነሱ ናቸው። በወቅቱ ግማሹ ምኒልክ ምን እንደሚመስሉም በመልክ አያውቋቸውም ነበር። ያንን ጥሪ ተቀብለው የሄዱ ኢትዮጵያውያን ለአሁኑ ትውልድ ትልቅ ምሳሌ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ባለው ጊዜ እራሱን ለመሰዋዕት ያዘጋጀ ትውልድ ነበረ።በአሁኑ ወቅት ግን ይህ ሁኔታ ምን ቀየረው?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** በአሁኑ ወቅት የሚሰጠው ትምህርት ያልበሰለ ትውልድ እንዲፈጠር አድርጓል።ምዕራባውያን ‹‹ትንሽ እውቀት መጥፎ ነው›› የሚል አባባል አላቸው። እኛ ጋር የተፈጠረው እንደዚህ ዓይነት ትውልድ ነው። አሁን በቅርብ የተከሰተውን ብንመለከት እንኳን የዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ፈተናን ውጤት መመልከት በቂ ነው። የራሳችን ቋንቋ፣ የራሳችን ፊደል የቀረጽን፤ የራሳችን የቀን አቆጣጠር ያለን ሕዝቦች ፈተናውን ከወሰዱት ሦስት በመቶ ብቻ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባታቸው ትውልዱ ምን ያክል አለመብሰሉን ያሳየናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ውጭ አገር ለትምህርት የሚሄዱት አስፈላጊ መረጃ በእንግሊዝኛ ለመሙላት ሲቸገሩ ይስተዋላል። ትውልዱ መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር የነበረው እሴት ተሸርሽሮ አልቆ አጥንቱ ነው የቀረው።አጥንት ደግሞ ከላይ ስጋ ከሌለው ይሰበራል። ትውልዱ እንዲከፋፈል የውጭ ኃይል እጅ አለበት።ኢትዮጵያ ተወደደም ተጠላም፤ በብዙ አፍሪካ አገሮች እ ንደበላይ ነው የምትታየው። ነፃ በመሆናችን ብቻ ሳይሆን ራሱ ባህላችን ትንሽ ይለያል።

**አዲስ ዘመን፡- የእኛን ባህል ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ባህል ምን ይለየዋል?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** እርግጥ እነሱም እንደኛ የራሳቸው ባህል ነበራቸው። ግን በብዛት በቅኝ ግዛት ስለተገዙ ያን የነበራቸውን አውጥተው እንዲጥሉት ሆኗል።ስለዚህ ከነስማቸው የውጭ ስሞችን ይዘው ይኖራሉ። ወደ ኋላ ዞር ብለው የሚያዩት ነገር የለም።እነ ጋናና ማሊ የራሳቸው ግዛት የነበራቸው ትልቅ አገር ነበሩ። የእነሱ ሲጠፋ ኢትዮጵያ ግን ባህሏን ጠብቃ፤ ኖራለች። ለዚህም ሁለት ትልልቅ የውጭ ጦርነት አሳልፋለች።

የምዕራባውያን ሚዲያዎች እነ ሲኤን ኤን፣ እነ ቢቢሲ የሰነዘሩብን ቀላል አይደለም።እነሱ ያሉትን ብንሰማና መንግሥት ደንግጦ እንደ መንግሥቱ ኃይለማርያም እግሬ አውጭኝ ቢል ኖሮ አልቆልን ነበር።መጀመሪያ አዲስ አበባ ውስጥ ያለነው ሰዎች

**አጼ ምኒልክ ነጋሪት አስጎስመው «ወረኢሉ ላይ እንገናኝ»ሲሉ፤ የኦሮሞው፣ የአማራው፣ የትግሬው፣ የሲዳማው፣ የከንባታው፣ የሶማሌው አገራችን ተደፈረች በሚል ስሜት በአንድ ላይ የተነሱ ናቸው**

አንተርፍም።ምክንያቱም የመንግሥት አጋዥ ሆነን ነው የምንታየው።

ሕዝቡ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ አልደራደርም ብሏል። ድሮም ድሃው ነው የሚዘምተው፤ ሌሎቹ እኮ ፈረንጅ አገር ናቸው። ስለዚህ ከዓድዋ እየተማርን ያለነው የሕዝቡ የውስጥ ጥንካሬ ነው። ያንንም ጥንካሬ በተደጋጋሚ አሳይቷል።

**አዲስ ዘመን፡- መከባበርን በመርህ ሁሉም ይስማማበታል፤ መተግበሩ ነው ከባድ የሚል አስተያየት ይነሳልና እንዴት ይተግበር ይላሉ?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** ለዚህ የእኔ ይበልጣል የሚባል ነገር መኖር የለበትም።ሰው ከፈለገ ለራሱ ይበለው፤ ከሰው ጋር ግን እኔ ከአንተ እበልጣለሁ የሚለው አይሰራም። ምክንያቱም አሁን ዘመኑ የፉክክር ነው።ጥላቻና ቂም ቶሎ የሚበቅልበት በመሆኑ አሁን ወጣቶቻችንን እየበረዝን ነው።ስንቱ የተማረ ወጣት ዛሬ ማህበራዊ ሚድያ ላይ ያነበበውን ይሄ እኮ እንደዚህ ዓይነት ችግር ሊያመጣ ይችላል፤ ይህንን ብል ይሄን ያስከትላል፤ የሚል የለም።አንብቦ ወዲያው ስልክ ደውሎ አብሮ እንደመከረ ሰው አልሰማህም እንዴ ብሎ ያወራል።ቀስ እያለ መንፈስን የሚበጠብጥ ነገር ሲዛመት የኅብረተሰቡን ጥንካሬ ያላላዋል።

ማሰሪያ ያለው ጫማ ተጫምቶ ወደ ሜዳ የገባ ሯጭ ማሰሪያው ክር እየለቀቀ ሲሄድ ጫማው እንዳይወልቅ ሲል የሩጫውን ፍጥነት ይቀንሳል።ስለዚህ ቆሞ ማሰር ይኖርበታል፤ ቆሞ ሲያስር ከኋላው ያለው ሊቀድመው ነው። ስለዚህ ኅብረተሰቡን ጭንቀት ውስጥ እንዲኖር የሚያደርግ አነጋገር በተለይ የሚድያ ባለሙያዎችና ፖለቲከኞች ኢትዮጵያን ከመሸርሸር መቆጠብ አለባቸው።ለዚህም ወጣቶቻችን ላይ መሥራት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- የበፊቱ ትውልድ ጦርነቱ በጦር ሜዳ ነበር፤ የአሁኑ ትውልድ ጦርነቱ የልማት መሆን አለበት ይባላል።እርስዎ ምን አስተያየት አልዎት?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** አገር ልማት ከሌለው እድገት አይኖረውም።ልማቱም በአዋቂዎች የተጠና የተመረመረ ከሆነ ውጤቱ ጥሩ ይሆናል። ለፖለቲካ ፍጆታ ተደርጎ ከሆነ ጥፋቱ እጥፍ ድርብ ነው። አሁን በአገራችን በእርሻውም በየቦታው የሚሠሩትም ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችንም ሆነ የህዳሴ ግድብን ሳየው ያረካኛል። ለነገ ዛሬ ካልሰራህ፤ ነገ ልትሠራው አትችልም።ነገ የሚኖረው አስተሳሰብ፣ ሁኔታውም ሆነ ባጀቱ ሌላ ነው። ሁሉም ነገር እንደዛሬው አይሆንም። ዛሬ አጥብቆ፣ አጥንቶና አሳምኖ እስከተሠራ ድረስ ኢትዮጵያን ወደ ላይ ከፍ ያደርጋታል። ተማሪዎች ትናንት ያጠኑትን ነው ነገ ፈተና አልፈዋል ተብለው ክፍል የሚሻገሩት።እንጂ ሳያጠኑ ነገ ፈተና ላይ ቢቀመጡ ዋጋ የለውም።ልማት የሌለበት አገር፤ አገር አይሆንም።ልማት ሲባል በእርሻውም፤ በወጣቶቹም ልጆች ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአባቶቻችን ጊዜ የነበረውን አገር መውደድ እንዴት ወደዚህኛው ትውልድ እናጋባ?**

**ልጅ ዳንኤል፡-** ተጋባ እኮ፤ የፈለገ መንግሥት ቢመጣ ሽግግሩ አልተቋረጠም።ግን ሳይሞከር አልቀረም፤ በልዩ ልዩ መልኩ ተሞክሯል። ጦርነትም ገብተናል።ያ በመሆኑም ሌሎቹ አንድ ላይ መሆን እንዳለባቸው ተረድተዋል። ዛሬ እዚ ጋ የተደረገው ጦርነት ካስፈለገ ነገ ሌላም ጋር እንደሚኖር ታውቋል። ቀደም ሲል መከላከያ የንጉሡ ከዚያም የርእሰ ብሔሩ ተጠሪና ታዛዥ ነበር። አሁን የመከላከያ ታዛዥነት ለሕገመንግሥት ነው።

ዛሬ ሰላም ስላለ ነው መሪያችን የተበጠበጠው ሶማሊያ ሄደው ስለአልሻባብ የሚመክሩት፤ ሰላም ባይኖረን ከቁጥርም አንገባም ነበር።እዚሁ እራሱ እንደትል አሸባሪዎች ይፈጠሩና ኢትዮጵያ እንደማትሆን ትሆናለች። የሚያልቀው አሮጊቱ፣ ሽማግሌውና ሕፃናት ናቸው።ሌላው በእግሩም አቆራርጦ ቢሆን የጎረቤት አገራትን ጥገኝነት ይጠይቃል።በህዳሴ ግድብም

## ልዩ ዕትም



ቢሆን መብራት እየሸጥን ነው፤ ይሄ የተሸጠው እኔ ኪስ ይገባል አይገባም።ግን በሌላ መልኩ ይገባል።ወደ ፊት እየተጠናከረ በሄደ ቁጥር የመብራት ዋጋ ይቀንሳል። ያሉት ኢንዱስትሪዎች በሙሉ የኃይል ፍጆታቸው እጥረት የነበረው ይቀራል።ስለዚህ ዓለም ላይ ለምናደርገው የንግድ ልውውጥም ቢሆን ተወዳዳሪነታችን ከፍ ይላል።

ልጆቻችን ማታ ማታ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ በመብራት ማጥናት ከቻሉ ትልቅ ለውጥ ነው።ድሮ እኛ ሻማ እያበራን ነው የምናጠናው፤ እያጠናን መብራት ይጠፋብን ነበር።የኢትዮጵያ አየር መንገድን ማየት ይቻላል፤ ሰላም ስላለ አይደል ዛሬ አፍሪካ ላይ ትልቅ የሆነው፤ ስታር አሊያንስ ተብሎ በዓለም ላይ የተደነቀው፤ ሰላም ስላለ ነው። ስለዚህ ኅብረተሰቡ ሰላም በምንም ምክንያት እንዳይሸረሸር ጥረት ማድረግ አለበት።

**አዲስ ዘመን።- አሁን ያለው የአገሪቱ ሰላም እንዳይሸረሸር ምን ይደረግ?**

**ልጅ ዳንኤል።-** ሰላም እንዳይሸረሸር ማድረግ የሚቻለው በመደማመጥና በመመካከር ነው።የእኔ ይበልጣል ነው አገር ያጠፋው።ይሄ እንዳይሆን መጀመሪያ ከሁሉም የሰማነውን ማዳመጥ ያስፈልጋል።ማዳመጥና መስማት ልዩነት አለው።ያ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የጎደለው።ተማሪዎች ጋርም ክፍል ቁጭ ብሎ የሚያንቀላፋ አለ።ምናልባት አልበላ ይሆናል፤ አባቱ ኮርኩሞትም ይሆናል።ችግራችንን አስወግን መደማመጥ ከቻልን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላሊበላን፣ አክሱምን፣ የፋሲል ቤተመንግሥትና የሐረር ግንብን ያነጸ፤ የስንት ሺ ዓመት ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያ ያደረገ ትውልድ አባሎች ነን።ሩቅ ነው እንጂ ከዚያ የመጣን ነን። አሁንም በቀጣይም ተተኪው ትውልድ ተማሪው ላይ ነው መሠራት ያለበት። እኛ እንደ አባይ ግድብ ሞልቶ ግብአት እየሆንን ነው የምንሄደው የሚያዋጣው አዲሶቹ ላይ መሥራት ነው።

**አዲስ ዘመን።- እነሱ ላይ ቢሠራ ያዋጣል ላሉት ለወጣቱ ትውልድ ምን ይመክራሉ?**

**ልጅ ዳንኤል።-** የመጀመሪያው ለሚሠራው ነገር በሙሉ ትኩረት (ፎከስ) መስጠት አለበት።የተበታተነ መንፈስ እንዲኖረው አያስፈልግም።ጠመንጃውን ይዞ አደን የወጣ ሰው የፈለገው አውሬ ላይ ካነጣጠረ በኋላ ሌላ ወፈር ያለ እንስሳ አየሁ ብሎ ኢላማውን ከቀየረ ሁለቱንም ሳያገኝ ይቀራል።ወጣቶች ለሚሠሩት ሥራ ሙሉ በሙሉ ትኩረታቸውን ሊሰጡ ይገባል። የሚሰሙትን ነገር ማመዛዘን ያስፈልጋል።የድሮ አባቶቻችን የምትነግራቸውን ያዳምጣሉ፤ ይሰማሉ። ግን ለምን እንደዚህ አለኝ የሚለውን ያሰላስላሉ፤ ይህች ነገር ተንኮል አላት ይላሉ። ለቅርብ ወዳጃቸው ሄደው እከሌ እኮ እንዲህ አለኝ ይላሉ።ከሚስትህ ሊያፋታህ ነው ወይም ከንጉሡ ሊያጣላህ ነው ይለዋል። ሄዶ አካኪ ዘራፍ አይልም። ተናጋሪው ሲመጣ ከጥፋቱ እንዲማር ጥረት ያደርጋል።

ዛሬ እኔ አካኪ ዘራፍ እንዲህ አደረገኝ እልሀለሁ። እንደ በፊቶቹ ለመብሰል እድሜ ስልት ይጠይቃል።ለዛም የድሮ ታሪክ ማንበብ ያስፈልጋል።ምዕራባውያን የጻፉትን ማርክሲዝም ሌኒንዝም ብቻ ማንበብ አይደለም።ዛሬ ባንክ ቤት በብሔር ነው፤ ሁሉ ነገር በብሔር ሆነ።የፖለቲካ ፓርቲ በብሔር ነው።በእዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዴት አገር ሊኖር ይችላል። በሌላው ዓለም እኮ የሚፎካከሩት ሁለት ፓርቲዎች ናቸው።በእኛ አገር ግን ከመቶ በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ።ይሄ ስግብግብነት ነው።ለመዝረፍ ካልሆነ በስተቀር አስፈላጊነቱ እኔ አይታየኝም። ከትኩረት በተጨማሪ ወጣቱ ለአገሩ መስዋእት ለመሆን መዘጋጀት አለበት። ለዚህም ሕገ-መንግሥትና መንግሥትን ማክበር ያስፈልጋል። ይሄንን እየሸረሸረ ከሄደ እራሱም የሚቆምበትም የለም። መርከብ ላይ ነው ያለኸው ሀይቁን እየተሻገርክ ነው። የቆምክበትን መርከብ ማሾንቀር ከጀመርክ አብረህ ነው የምትሰምጠው የሚቀር ሰው የለም። ይሄንን ደግሞ በጃንሆይ ጊዜ አይተነዋል።

ተማሪ ሆነን የአባታችንን መንግሥት አብረን አካኪ ዘራፍ ስንል ነበር።የጭቃ ጅራፉ ሲመጣ ሁላችንንም እንደአውሎ ንፋስ ይዞን ሄደ።ያ ልምድ አለን፤ ዘመዶቻችን ታስረው፤ ተገድለው አይተናል። ኢትዮጵያ እንዲህ መሆን አለባት፤ ኢትዮጵያ ይሄን ማድረግ አለባት፤ ሲኖርህ እኮ ነው የሚሟላው።የተማረ ሰው እኮ አልነበረም። የውጭ ኢንቨስትመንት አልነበረም፤ ግን እንደሌላው አገር መሆን እንፈልጋለን።አባወራ ቤት ገብቶ ሚስቱን ባልሰጣት ወጪ ክትፎ አቅርቢ ይላል እንዴ፤ እኛ ግን ያንን ነበር እያደረግን የነበረው።በዚህም እናት ሚስት የሆነችው አገር አኮረፈች፤ ተቆጣች።በ17 ዓመት ብዙ የተማሩ ከአራተኛና ከስድስተኛ ክፍል እንግሊዝኛ ኮሌጅ እንዳለ ሰው የሚናገሩ በሙሉ አለቁ፤ ቀይ ሽብር ነጭ ሽብር እየተባለ።ያ እንዳይሆን ነው የምፈልገው።

አሁን ያለው ወጣት ጥፍሩ እስከሚያልቅ ድረስ እየቧጨረ አንድ ደረጃ ደርሶ ለሚመጣው ትውልድ ገመድ አቀብሎ ተሻጋገር ሊለው ይገባል።ለዚህም ሰላም ይፈልጋል፤ አስተዋይ መሪ ይፈልጋል። አባትና እናትም ከመንግሥት በላይ ነው መሆን ያለባቸው፤ ስለዚህ እኔ ትኩረት የምሰጠው ወጣቱ ላይ ነው።እነሱ ናቸው የወደፊቶቹ፤ ዛሬ ከአገራችን 70 በመቶው ወጣት ሕዝብ ነው።ከትንሽ ጊዜ በኋላ እኚህ ወጣቶች አዛውንት ይሆናሉ።አዛውንት ሲኮን አብሮት የሚመጣ ብዙ ነገር አለ።አይን፣ ጉልበት ይደክማሉ።አጠገብ የነበሩ ልጆች በየአቅጣጫው ተበትነው ብቻ መቅረት አለ።ስለዚህ ይሄንን እንዴት ነው ወደፊት የምናስተናግደው ልማቱንም ኢንዱስትሪውንም እርሻውንም ከአሁኑ ስንጀምረው ነው።ዛሬ ሶማሌ ክልል ውስጥ ዘመናዊ እርሻ ተጀምሯል፤ በፊት ሶማሌ ክልል በርሃ ነው አሸዋ ነው ሲባል ነበር።አሁን ከተሠራ መቀየር እንደሚቻል በተግባር ታየ።ነዳጅም ተገኘ፤ ይሄ ሁሉ ሀብት ያለን ሰዎች ሰላማችን አይፈለግም።

**አዲስ ዘመን።- ብዙ ጊዜ የውጭ ጣልቃ ገብነት ሲባል የማይዋጥላቸውና የፕሮፓጋንዳ ሥራ የሚመስላቸው ወገኖች አሉ፤ ሰላም ብንሆን ሌሎች አገራት ምን ይጎዳሉ?**

**ልጅ ዳንኤል።-** ሰላም ከሆንን አልፈናቸው እንሄዳለን።አሁንም አፍሪካን አልፈን ሄደናል።ሌሎች አፍሪካ አገራት ቢኬድ ኅብረተሰቡ እንደኛ አይደለም።አንድ ሰው ኬንያ ቢሄድና ጥቁርና ሕንድ አብረው ሊስተናገዱ ቢቀመጡ የአገሬው ሰው መጀመሪያ ሕንዱን ነው የሚያስተናግደው፤ ጥቁሩን ዞር ብሎ የሚያየው የለም።እኛ ጋር ፈረንጅ መጣ ማን መጣ ሁሉ እኩላችን ነው።የበላይ ነን አላልንም፤ ግን እኩል ነን ነው የምንለው።

**አዲስ ዘመን።- ብዙ ጊዜ ችግሮች ሲከሰቱ የተወሰኑ አካላት አንዴ ከደፈረሰ አይጠራም በሚል ነገሮች በእርቅ ሲፈቱ ቅር ሲሰኙ ይስተዋላል፤ እርስዎ እንዴት ያዩታል?**

**ልጅ ዳንኤል።-** እኚህ ደካማ መንፈስ ያላቸው ናቸው፤ መፍትሄ ይገኝለታል ብሎ ያላሰበ ነው።መፍትሄውን አገኛለሁ ብሎ ጊዜ ወስዶ ያልተመራመረ ነው።ልክ ‘ያበጠ ይፈንዳ’ የሚለው ዓይነት፤ ለእኔ ይሄ አጥፊ ትውልድ ነው።አባቶቻችን ማይጨው ላይ ጣሊያን በመርዝ ጭስ ሲያወድማቸው ጦሩ ፊት ለፊት ሲዋጋ፤ በመትረየስ ሰው ሲያልቅ አይተው ስልታቸውን ለወጡ።ወንድሞቻቸው ጓደኞቻቸው አልቀዋል፤ አንዳንዶቹንም ሳይቀብሩ ቀርተዋል።ስለዚህ በእኔ አስተሳሰብ ይሄ የደካማ አስተሳሰብ ነው።

ሲጀመር እንዲህ የሚሉ ሰዎች ጉዳዩንም የሚያውቁ አይመስለኝም፤ መመራመሩንም መሥራቱንም፤ ነገሩን አውጥቶ አውርዶ ምናልባት ውስኪ፣ ጠጅ ወይ ካቲካላ ሲጠጣ ጭንቅላቱ ተከፍቶለት ይነጋገራል እንጂ ነገር መሠረቱን ተረድቶ ይሄ ቢሆን እንዲህ ይሆናል፤ ይሄኛው መወሰኑ የሚያመጣውን ውጤት በትክክል ከሚያስብ ሰው ጋር የመነጋገር ችሎታው ዜሮ ነው።ለዚህ ነው ያበጠ ይፈንዳ፤ ይደፍርስ፤ የሚሉት።ደፈረሰ እኮ የንጉሡ መንግሥት ጊዜ ደፈረሰ፤ ከዚያ ምን ተፈጠረ? የበለጠ ደፈረሰ።

እኔ አንድ ጊዜ ሽጉጥ ከተኮስኩብሽ በኋላ በቃ ትሞቻለሽ። ደፈረሰ ማለት እሱ ነው። ከዚህ በኋላ አንቺ እንደፈጣሪ ተነስተሽ አታርጊም። በእኔ በኩል ይደፍረስ የሚባለው ነገር ከጭንቅላት ድክመት ከእውቀት ማነስ የመጣ ነው ብዬ ነው የማየው።ሁላችንም እኮ በፊት ብለናል፤ ይደፍርስ ቤተመንግሥቱን ንጉሡን ነው እኛን አይነካንም አልን፤ የጭቃ ጅራፉን ይዞ መጥቶ ሁሉንም ማጅራቱን ይመታው ጀመር።ማነው የተጎዳው ደሃው ሕዝብ ነው የተጎዳው፤ ደሃው ሕዝብ ነው፤ ቆሎውን እንዳይበላ፤ ልጆቹን አስተምሮ ወደፊት የሚሻሻልበትን ዕድሉን ነሱት።ከየቤቱ ሰው አልቋል ለምንድነው እኛን አይነካንም፤ የፈለገው ይሁን፤ ይፈንዳና ይተረማመስ፤ እህል ብቻ ነው በወንፊት ሲነፋ ንጹህ ነገር የሚወጣው።

**አዲስ ዘመን።- ለወጣቱ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?**

**ልጅ ዳንኤል።-** ወጣቶች በአገር ጉዳይ ላይ በምንም ዓይነት ሳያመነቱ ዘብ መቆም አለባቸው። ከዚያ ባሻገር እራሳቸውን ሁልጊዜ እኔ የበላይ ነኝ እኔ ሁሉን አውቃለሁ የሚለውን መንፈስ ትተው የሚያውቁትን እውቀት ማጋራት አለባቸው።የሌላውን እውቀት ተቀብለው አዛምደው መሄድ ሲችሉ ነው ጥሩ ዜጋ የሚሆኑትና ጥሩ አገርም መምራት የሚችሉት።ዝም ብለው የእኔ ብቻ ካልሆነ የሚለው አስተሳሰብ አገር አጥፊ ነው፤ አጥፍቷልም። አምባገነንነትም የሚመጣው በዚህ ዓይነት ነው። እኔ የምናገረውን ካልተቀበልሽ ጠላቴ የምትሆኚ ከሆነ፤ ስለዚህ የዚያን ዓይነት አስተሳሰብ እንዳይኖር መጣር ነው።

**ወጣቶች በአገር ጉዳይ ላይ በምንም ዓይነት ሳያመነቱ ዘብ መቆም አለባቸው**

**አዲስ ዘመን።- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ!**

**ልጅ ዳንኤል።-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ልዩ ዕትም

# «በዓለም ላይ የተደረጉ የጸረ ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴዎች የተስፋ ምንጫቸው ዓድዋ ነው»

ዶክተር አየለ በክሪ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)
የታሪክ ምሁር

አስቴር ኤልያስ

ከዛሬ 127 ዓመት በፊት በ1888 ዓ.ም ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመውረር መጥታ በአጼ ምኒልክ መሪነት ድባቅ ተመትታ መባረሯ ይታወሳል።በኢትዮጵያውያኑ ትንታጎች ነጮ የበላይነቱ ያበቃበት ዕለት በመሆኑም በኢትዮጵያውያኑም ሆነ በመላ ጥቁር ሕዝብ ዘንድ የሚንቦገቦግ ድል ሆኖ መመዝገብ ችሏል።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ ሲከበር የመጣው ይህ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ በሚፈጠሩ ፈተናዎች ሲዳከሙ ከደማቁ ታሪክ መዘዝ አድርገው የሚጠናከሩበት ብርታታቸው ሆኗል።በተለያዩ አጋጣሚዎች በአንዳንድ አሳዋቂዎች መገፋት በገጠማቸው ጊዜ ሁሉ የዓድዋን ድል ሳብ አድርገው ማንነታቸውን እንዲያስታውሱ የሚያደርጉበት የክታቸው ድልም ነው።በተለይም ይህ የዓድዋ ድል አፍሪካውያን እንዲሁም የቅኝ ገዥዎች ቀንበር ጫንቃቸው ላይ ተጭኗቸው አጉብጧቸው የነበሩት ሌሎች አገራትም ፓን ኢትዮጵያኒዝምን እንዲሰብኩ ያነቃቃ ጣፋጭ ስኬትም መሆን የቻለ ነው።ከዚህ ጎን ለጎን አፍሪካ በተፈጥሮ የተቸረችውን ሀብት ለመቀራመት ይከጅሉ የነበሩትን የቅኝ ገዥዎችን ጥማት ያናጠበ ብሎም የድሉ ብስራት አከርካሪያቸውን የመታ መሆኑም እሙን ነው።አዲስ ዘመን ከዚሁ ከዓድዋና ፓን አፍሪካኒዝም ጋር ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎችን አንስቶ ከታሪክ ምሁሩ ዶክተር አየለ በክሪ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅሮታል።

**አዲስ ዘመን።- ዓድዋ በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?**

**ዶክተር አየለ።-** ዓድዋ በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል።ለምሳሌ የአንድ ጭቆናን እድሜ ማራዘም የሚቻለው የሐሰት ፕሮፓጋንዳን በመንዛት ያንን ሰው ግራ እንዲገባው በማድረግ ነው።ዓድዋ የዚህ ተቃራኒ ነው።ዓድዋ ላይ ድል ሆነ፤ ድል ያደረገው ደግሞ ጥቁር ነው፤ ጥቁር ድል ያደረገው ደግሞ ነጬን ነው።ነጭ ደግሞ በወቅቱ እንደ ንጉሥ የሚታይና ከፈጣሪ ቀጥሎ ራሱን እንደ አምላክ የሚቆጥር ነው።ስለዚህ ይህ የዓድዋ ድል ለጥቁሮች ሁሉ የማያቋርጥ ተስፋ የሚሰጥ ታሪክ ነው።ስለዚህ ዓድዋ ያንን በነጮች ተይዞ የቆየውን የበላይነት ያናጋ ነው።።

በእርግጥ እያንዳንዱ የየራሱን ትግል በሚያካሂድበት ወቅት የአሸንፋለሁ መርህ በአዕምሮ ውስጥ ሊኖር የግድ ነው።ለዚህ ለአሸንፋለሁ መርህ ደግሞ ማጣቀሻው ዓድዋ ይሆናል።ለዚህም ነው በቅርቡ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተደረገው ጦርነት ላይ መላ የዓለም ሚዲያ በእኛ ላይ ዘመቻ ተያይዞ የሰነበተው።ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ ነጭን አሸንፋ የማይፋቅ ታሪክ ያስመዘገበች አገር ስለሆነች ዳግም መጥተው አፍሪካን ወርረው ፍላጎታቸውን ለማሳካት እንቅፋት ጭምር ሆኖባቸዋል።ስለዚህ የተባ የተጽዕኖ ብዕራቸውን ሲመዙባት ቆይተዋል።ምክንያቱም የሁልጊዜ ጥማታቸው አፍሪካን በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ ነው።ለዚህ ደግሞ በዋናነት እንቅፋት የሆነባቸው ዓድዋ ነው።ለዚህ ድል የበቃችው ደግሞ ኢትዮጵያ በመሆኗ ኢትዮጵያ እንቅፋታቸው ናት።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ባላትና ከታሪክ ባገኘችው ታላቅ ውርስ ያህል አፍሪካን አላስተባበረችም።አፍሪካ ወደአንድ እንዲመጣ አላደረገችም።እነ አጼ ኃይለሥላሴና እነ ከተማ ይፍሩ በጊዜያቸው የአፍሪካ ኅብረትን ከስንቱ ጋር ተነታርከው ወደኢትዮጵያ እንዲመጣ አድርገዋል። እነ ክዋሜ ንክሩማ ደግሞ ባላቸው እውቀት እና ኢትዮጵያ ባላት ታሪክ ኅብረቱ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሆን ደግፈዋል።

ይሁንና ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ የሄደችው ወደ እንቅልፍ ነው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያለው ዓመት ሲሰላ ስድስት አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል።በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ብዙ ነገር ሊደረግ ይችል ነበር።ይህ ነው ዋና ቁልፉ ነገር።ዝም ብሎ በንግግር ብቻ ፓን አፍሪካኒዝም አይመጣም።ዋና ፍልስፍናው ዓድዋ ከፓን አፍሪካኒዝም ጋር የሚያገናኘውና ያንን ግንኙነትን ሕያው የሚያደርገው በንቃት የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ናቸው።እነርሱ ግን አሁን ላይ እምብዛም እየታዩ አይደሉም።

**አዲስ ዘመን።- የዓድዋ ድል ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ለፓን አፍሪካኒዝም ያበረከተችው አስተዋጽኦ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶክተር አየለ።-** ኢትዮጵያኒዝም የፓን አፍሪካኒዝም ነጸብራቅ ነው።የጥንቷ ኢትዮጵያ ከአሁኗ ኢትዮጵያ የተለየች ናት።የጥንቷ ኢትዮጵያ ከግብጽና ከሊቢያ በስተቀር ሁሉንም አፍሪካ የምታጠቃልል ነች።አፍሪካ መባል ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራ ነበር።አትላንቲክ ውቅያኖስ ተብሎ የሚጠራው ቀደም ሲል ‹‹ኢትዮጵያ ውቅያኖስ›› ይባል ነበር።።



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**ወደ ዓድዋ ድል ስንመጣ ደግሞ በአንድ በኩል እኛ ሉዓላዊነታችንና ነፃነታችንን ያስከበርንበት ነው። እንደማኛውም አውሮፓ ውስጥ እንዳለ አገር አገር መሆናችንና መንግሥት እንዳለን እና ያልተበታተንን አገር መሆናችንን ያስመሰከርንበት ነው**

ወደቅኝ አገዛዝ ሲመጣ ደግሞ ኢትዮጵያኒዝም ወደፓን አፍሪካኒዝም ተቀይሯል።ኢትዮጵያኒዝም እምነት ተኮር ነው።ፓን አፍሪካኒዝም ደግሞ ዓለማዊ (ሴኩላር) ነው።እንዲህም ሲባል ፓን አፍሪካኒዝም ዘመናዊ አስተሳሰብ ሲሆን፣ አገር ለመፍጠር ብሎም ሕዝብ ለማስተዳደር እንዲሁም ጥቁር ከነጭ አይለይም ብሎ ለመከራከር ዕድል የሚሰጥ ነው።እንዲሁም ጥቁር በሁሉም መስክ እንዲሰማራ መታገልን ጭምር የሚያቃልል ነው።ይህም የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴም የተጀመረው እኤአ በ1900 ላይ ነው።

ወደ ዓድዋ ድል ስንመጣ ደግሞ በአንድ በኩል እኛ ሉዓላዊነታችንና ነፃነታችንን ያስከበርንበት ነው።እንደማንኛውም አውሮፓ ውስጥ እንዳለ አገር አገር መሆናችንና መንግሥት እንዳለን እና ያልተበታተንን አገር መሆናችንን ያስመሰከርንበት ነው። ለምሳሌ ብዙ ቋንቋዎችና ኃይማኖቶች አሉ፤ ነገር ግን አጼ ምኒልክ የክተት አዋጁን ካወጁ በኋላ በዘር በኃይማኖት ሳንለያይ ሁሉም ጥሪያቸውን አከብሮ አገር ከሌለ ምንም ነገር አይኖርም በሚል ከጎናቸው መሰለፍ ችሏል። ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ተቀብለውትና ለዚያ መስዋዕት መሆን ክብር ነው ብለው ተዋግተዋል።እነዚህ ኢትዮጵያውያን የዘመቱት ከሁሉም አቅጣጫ ነው፤ በዘመቱበት ወቅት የጦር ስልት ነድፈው አገራቸው ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲውም መንገድ ከሆነ እሰየው ካልሆነ ደግሞ ተዋግተው አሸንፈው ለመመለስ ነው፤ በወቅቱ ኢትዮጵያውኑ የዘመቱት መሣሪያ ገዝተውም ጭምር ነው።

ኢትዮጵያውኑ መሣሪያቸው ከጣሊያኑ የሚበልጥ እንጂ የማያንስ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፤ አንዳንዴ የኢትዮጵያ ጦር በባዶ እግሩ በጦርና በጋሻ ተዋግቶ ነው ያሸነፈው የሚባል ነገር አለ፤ እርግጥ ነው የተዋጋነው በባዶ እግራችን ነበር።ነገር ግን በባዶ እግር መንቀሳቀስ የዚያን ወቅት ባህል ነው ማለት ይቻላል፤ ሁሉም ሰው በሚያስብል ሁኔታ የሚሄደው ባዶ እግሩን ነበር።እንዲያም ሆኖ ግን ጦርነቱን በዚያ ደረጃ አሸንፈዋል።

አንዳንዶች እንደሚገምቱት ድሉን የተቀናጀው ሕዝብ የተበታተነ ሕዝብ አልነበረም።ለየብቻው ጎራ ፈጥሮ አልተንቀሳቀሰም።ያ ሕዝብ የግሉ የሆነ ባህል ብሎም እምነት ሊኖረው ይችላል፤ ነገር ግን በትብብር ለአገር ታላቅ ሥራ መሥራት ችሏል።ዓድዋ ያስመሰከረው እሱን ትብብር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በዓድዋ የተገኘው ድል በቅኝ አገዛዝ ማኅደር ያየነው እንደሆነ አሸናፊው በዘመኑ በነበረው የዘረኝነት አስተሳሰብ ጥቁር ነው፤ ተሸናፊው ደግሞ ነጭ ነው።በመጀመሪያ ደረጃ ነጭ ማለት በይበልጥ አውሮፓ የሚኖር ማለት ነው።ኤዥያም፣ አፍሪካም ሆነ ደቡብ አሜሪካ ብትኖሪ የሚባለው ነጭ ያልሆኑ ሰዎች (Non white) ነው።ለእነዚህ ሁሉ የዓድዋ ድል የማይጠፋ የችቦ መብራት ብሎም የማይጠፋ ብርሃን ሆኗል።ምናልባትም እነዚህ የተለያየ አህጉር የሚኖሩ ነጭ ያልሆኑ ሕዝቦች ሲታገሉ የራሳቸው ችቦ የሚጠፋባቸው ከሆነ ኢትዮጵያ በዓድዋ ካስመዘገበችውና ከሚንቦገቦገው ችቦ ጋር አያይዘው በእንደገና መንፈስ ትግላቸው ለማቀጣጠል የዓድዋን ድል ይጠቀሙበታል።።

በዓለም ላይ የተደረጉት ጻረ ቅኝ አገዛዝ እንቀስቃሴዎች በሙሉ የተስፋ ምንጫቸው ዓድዋ ነው።ዓድዋ እኤአ በ1896 ነው፤ ፓን አፍሪካዊነት የመጀመሪያ ጉባኤ ከተደረገበት አንስቶ ወደ አፍሪካ እስከመጣ ድረስ እስከ 1945 ድረስ ለፓን አፍሪካዊነት እንቅስቃሴ የዘወትር ማበረታቻ እና ማንቂያ እየሆነ ያለገለ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ድል የማይጠፋ ድል ነው።

የዓድዋ ድል ሌላው ቀርቶ ስንወድቅ እንድንነሳ ሊያደርግ የሚችል ብርታት ነው።

ደግሞም የዓድዋ ድል ሲባል በኢትዮጵያውያን ውስጥ ያለ ታላቅ ድል ነው።ውስጣችን ያለ ድል በመሆኑ ደግሞ ነቃ ብለን እንድንንቀሳቀስ የሚያደርገን ከመሆኑም

# ልዩ ዕትም



**የዓድዋ ድል የሁላችንም ድል ነው።የዓድዋ ድል ባለቤት አንድ አካል ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው**

በተጨማሪ አንገታችንን ሳንደፋ መሄድ እንድንችልና ክብር ያለን ሰዎች መሆናችንን የምናሳይበት ነው።ከዚሁ ጎን ለጎን የአይበገሬነትና የአሸናፊነትን መንፈስ የሚያስታጥቀን ነው።

**አዲስ ዘመን።- ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በዓድዋ ያስመዘገበችው ድል ስመሳ ጥቁር ሕዝብ የሚፈነጥቅ ብርሃን እንዳበራች ሁሉ በአሁኑ ወቅት ስፓን አፍሪካኒዝምነት ምን አዲስ አበርክቶ አሳት ይሳሉ?**

**ዶክተር አየለ።-** ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ እኤአ ከ1900 ጀምሮ ብንቆጥረው ወደ 123 ዓመት በመሆኑ ጊዜው በጣም ረጅም ነው።በዚህ እንቀስቃሴ ውስጥ ከሕዝብ ተኮርነት ወደ ተቋም ተኮርነት ነው የዞረው።ልክ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም ተቋምነትና መንግሥት ለመንግሥት ባለ ግንኙነት ብቻ ነው ፓን አፍሪካኒዝምነት እየተገለጸ ያለው እንጂ ሕዝቡን አያሳትፍም።

አንድ መጠቀስ ያለበት ነገር እንዳለ ይሰማኛል።ያንንም ነገር መጥቀስ እሻለሁ።አንደኛው በዓመት አንድ ጊዜ የአፍሪካ ሕብረት በመጣ ቁጥር እና በዓመት አንዴ ዝክረ ዓድዋ በመጣ ቁጥር ‹‹ሆሆሆ...›› እንልና ከዚያ በኋላ ሁሉ ነገር ቀጥ ይላል።በዚያ ፓን አፍሪካኒዝምን አሳደግን ብለን መፎከር አይቻልም።በእርግጥ አዲስ አበባ ላይ የተደረገው የ36ኛው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ በሚዲያም ስለጉባኤው ብቻም ሳይሆን ስለ ፓን አፍሪካኒዝም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ጨምሮ ብዙዎች በጉዳዩ ዙሪያ ተናግረዋል።ተሳታፊዎችም የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል።ይህ መልካም የሚባል ነው።ነገር ግን እቅድ በማውጣት በ5፣ 10፣ 20 ዓመት እየተባለ ይህንን እና ያንን እናሳካለን ወይም ማሳካት ተችሏል በሚል ካልተሠራ በየዓመቱ አንድ ጊዜ በሚመጣ ጉባኤ ማስተጋባት ብቻውን ትርጉም የሚሰጥ አይደለም።

ለምሳሌ በአፍሪካ አህጉር 55 አገራት አሉ።እነዚያ አገራት ለፓን አፍሪካኒዝም የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ከእነርሱ ጋር ሲተያይ እኛ በየትኛው ረድፍ ላይ ነው የምንገኘው? አስተዋጽኦ ያደረግነው በየትኛው ጉዳይ ላይ ነው? ያላደረግነውስ በየትኛው ላይ ነው? የሚለው መፈተሽ አለበት።ለምሳሌ ያህል ጋናን እንውሰድ፤ ጋና ብዙ አስተዋጽኦ አበርክታለች።የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ በግንቦት 25 ቀን 1963 ዓ.ም በተቋቋመ ጊዜ ይህን ዕለት የአገሯ ብሔራዊ በዓል አድርጋ አውጃለች። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሠረተበትን ቀን ምክንያት በማድረግ 14 የአፍሪካ አገራት እንደ ብሔራዊ በዓል አውጀውታል።ይህ የፓን አፍሪካኒዝም ጥንካሬን የሚያሳይ ነው።ኢትዮጵያ ግን እዚያ ውስጥ የለችበትም።ምክንያቱም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሰረተበትን ዕለት እንደ ብሔራዊ በዓሏ አልወሰደችውም።

**አዲስ ዘመን።- ታዲያ ኢትዮጵያ ስፓን አፍሪካኒዝም ምን አዲስ አበርክቶ አሳት?**

**ዶክተር አየለ።-** በምግብ ራስን መቻል ትልቅ ነገር ነው።በተለይ ደግሞ የምግብ ፍጆታ ከውጭ የሚገባ ከሆነ ያንን አቁሞ በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረግ ጥረት ትልቅ ነገር ነው።ግን ደግሞ በአንድ በኩል ቦረና አካባቢ የሚታየው ችግር የሚያሳስብ ነው፤ የስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚደገፍ ሆኖ ሳለ ጎን ለጎን ደግሞ የተፈጠረውን ችግር በማቃለል ረገድ ሊሠራ ይገባል።ፓን አፍሪካኒዝም ማለት የሚጀምረው ከራስ ነው። የራስን ድል የራስ ከማድረግ ባለፈ የሌሎችም ማድረግ መልካም ነው።

አንዳንዱ ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ አልነበራትም ብሎ በድፍረት የሚናገር አለ።ነገር ግን ኢትዮጵያዊነት የሚለውን በቁርጠኝነት የምንወስደው እና እኔን ከአንቺ ጋር ሊያስማማ የሚችለው ነጥብ ላይ መግባባት አለብን።ይህን ካደረግን በኋላ ወደ ጎረቤት አገሮች መሄድ እንችላለን።አሁን አሁን በአገራችን የሚታየው ነገር ግን ታሪክ እንዲሸረሸር ነው።

እንደሚታወቀው የዓድዋ ድል የሁላችንም ድል ነው።የዓድዋ ድል ባለቤት አንድ አካል ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። አንድ አካል ብቻ ባለቤት ሊሆንበት አይችልም።ይህን ሁላችንም ልናምን ይገባል። ይህ የጋራ የሆነ ድላችንን በጋራ እንዳመጣን ሁሉ ራስንም ሆነ አገርን ለማሳደግ አርዓያነት ያለው ድል ነው ብለን ካልተቀበልን ተጠቃሚ መሆን አንችልም።

አጼ ምኒልክን ብንወዳቸውም ባንወዳቸውም የዓድዋን ጦርነት የመሩት እርሳቸው ናቸው።የዓድዋ ጦርነትን መርተውም አሸንፈዋል።ይህ የዓድዋ ድልም እንዳይቀለበስ ሆኖ ተመዝግቧል።በአገር ውስጥ የቱንም ያህል አለመግባባት ቢኖር በዓድዋ ድል ግን መስማማት መኖር አለበት።ምክንያቱም ታሪክ ሊጠፋ ሊፋቅም አይችልምና ነው።ኢትዮጵያ በጣሊያን ተሸንፋ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ የሚለው ትልቁ ምስል ጠፍቶ የምንሆነው እንደቡሩንዲና ሩዋንዳ ዓይነት ትንንሽ አገር ነበር።

እሱ እንዳይሆን ነው አጼ ምኒልክ አንድነትን ማምጣትና በአንድነት መኖር አለብን ብለው የታገሉት፤ ይህ ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት አንድ መሆን አለበት ሲሉ እንቅስቃሴውን የጀመሩት።በዚህ መልኩ ኢትዮጵያ በቅኝ ገዥዎች ዘንድ የተፈራች እንድትሆን አስችሏታል።

ስለዚህ ፓን አፍሪካኒዝም ዝም ብሎ በምኞት የሚመጣ አይደለም። አሁንም ቢሆን አውሮፓውያን አፍሪካን መቆጣጠር ይፈልጋሉ።አፍሪካን መቆጣጠር የሚፈልጉት ደግሞ በተፈጥሮ ሀብታም ስለሆነች ነው።የማዕድን፣ የነዳጅ ብሎም የሌሎችም የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት በመሆኗ ነው።ይሁንና ለራሷ አልተጠቀመችም።እነዚሁ አውሮፓውያን በተዘዋዋሪ መንገድ እየከፋፈሉ መቆጣጠር ይፈልጋሉ።።

እንዲያውም የአፍሪካውያን ስምምነት ቢኖር የአህጉሪቷን አገሮች ለማስተዳደር 55 መሪም አያስፈልግም ነበር።ልክ እንደ አሜሪካ ያውም የአሜሪካ ግዛት ትልቅ ግዛት ነው፤ ነገር ግን አሜሪካ በአንድ ፕሬዚዳንት በመተዳደር ላይ ናት። በተመሳሳይ ቻይና በሕዝብ ብዛትም በቆዳ ስፋትም ትልቅ አገር ሆና የምትተዳደረው በአንድ ፕሬዚዳንት ነው።ወደእዚያ ለመድረስ ግን የአስተሳሰብ መጣጣምና ውህደት ያስፈልጋል።እኛ ግን እዚህ ደረጃ ላይ ገና አልደረስንም።

**አዲስ ዘመን።- በፓን አፍሪካኒዝም የአፍሪካ አገሮች ሚና ምን ይመስላል?**

**ዶክተር አየለ።-**ቅኝ ገዥዎች ከአፍሪካ ሲወጡ ሙሉ በሙሉ ጓዛቸውን ጠቅልለው አልወጡም።ከመሄዳቸው በፊት ያደረጉት ነገር ቢኖር አንደኛ ያቆዩልን ቅርስ የተከፋፈለ አፍሪካን ነው።የተከፋፈለ አፍሪካን ይዞን ነው ስለ ፓን አፍሪካኒዝም፣ ስለአንድነት ስናስብ የነበረው። ዋናው ነጥብ በዚያ ምክንያት አፍሪካ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አገሮች ለፓን አፍሪካኒዝም ያላቸው ቁርጠኝነት መለያየቱ ነው።አንዳንዱ በጣም ቁርጠኛ ሲሆን፣ አንዳንዱ ደግሞ ከበፊት ቅኝ ገዥዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት አሁንም አጠናክሮ በምንም ዓይነት ሁኔታ በፓን አፍሪካኒዝም ዙሪያ መሳተፍ እንኳ አይፈልግም።።

በእርግጥ ሁሉም አፍሪካ ውስጥ ያሉ አገሮች የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ናቸው።እሱ መሆኑ መልካም ነው። በተለይ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ አፍሪካ ኅብረት ሲሸጋገር በዚያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጣልቃ ገብነት አይፈቀድም የሚል ሕግ ስለነበር ኩዴታ ሲካሄድም ሆነ ሕዝብ መብቱ ሲጣስ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በወቅቱ የአገራቱን ሉዓላዊነት አልደፍርም በሚል እሳቤ ምንም አይልም ነበር።በአፍሪካ ኅብረት ደረጃ እሱ አሁን ቀርቷል።ለምሳሌ መንግሥት ከተገለበጠ መንግሥት ገልባጭ ወታደር ቶሎ ብሎ በሕጋዊ መሠረት መንግሥት እንዲቋቋም ካልተደረገ እገዳ ይደረግበታል።ለምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ ሱዳን፣ ኒጀር፣ እነ ቡርኪና ፋሶ እገዳ ተደርጎባቸዋል።በእርግጥ በዚህ የፓን አፍሪካኒዝም መንፈሱ ማንጸባረቂያ ነው ሊባል ይችላል።

አንዳንድ አገሮች ፓን አፍሪካኒዝምን በኃይል እየገፉበት ነው። ለምሳሌ እንደ ጋና፣ ሴኔጋል ብሎም ደቡብ አፍሪካ ዓይነት አገሮች እያጠናከሩት ይገኛሉ፤ ምክንያቱም ደቡብ አፍሪካውያን በፓን አፍሪካኒዝም በማመናቸው ነው የእኛን የእርስ በእርስ ጥል እኛ ማቆም ስላልቻልን ወደእነርሱ አምርተን እንድንታረቅ የተደረገው።ደቡብ አፍሪካውያን ስንት ዓመት ሙሉ በዘረኝነት ሲሰቃዩ የነበሩ ሕዝቦች አሁን ላይ በስለው የራሳቸውን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካንም ጉዳይ ጉዳዬ ነው ብለው አጋርነታቸውን ሲገልጹ ቆይተዋል።ይህ ደግሞ ለፓን አፍሪካኒዝም ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል።በዚህ መልኩ በፓን አፍሪካኒዝም መንፈስ ጥቅምን ማስከበር በአፍሪካውያን ላይ ይታያል ማለት ነው። ለምሳሌ ዩክሬንና ሩሲያ በሚያካሂዱት ጦርነት ላይ ሲገቡ በዓለም ላይ ሁለት ጎራ ተፈጠረ፤ አብዛኛው የአፍሪካ አገር ገለልተኛ ነበር፤ ይህ የሚያሳየው እድገት ብሎም መብሰልን ሲሆን፣ የሚያሳየውም ፓን አፍሪካኒዝም የሚለው አስተሳሰብ ቀስ እያለ በአዕምሯቸው እየሰረጸ መምጣቱን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዱ የአፍሪካ አገር ከሌላው የአፍሪካ አገር ጋር ወደጦርነት የመግባቱ ነገር እንደቀድሞ የለም፤ ቢታይም ወደ ምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ነው። ለምሳሌ አልጄሪያና ግብጽ በብዙ ነገር አይስማሙም፤ ይሁንና ወደ ግጭት ሲገቡ አይታዩም።ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ሰሜን አፍሪካ ዴሞክራሲያዊ አገራት ናቸው ማለት ይቻላል።ትንሽ ኩዴታ የሚበዛው ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ነው። ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ለምንድን ነው ቢባል የውጭ ጣልቃ ገብነት ስላለ ነው።ለምሳሌ ኮንጎ ነፃነቷ ካገኘች ጀምሮ እስካሁን ሰላሟን አግኝታ አታውቅም።ለምን ቢባል ኮንጎ 24 ትሪሊዮን ዶላር የሚገመት የማዕድን ሀብት አላት።ሁሉም ጣልቃ ገብ፤ አጣልቶ ያንን አብቷን ወደውጭ መውሰድ ይፈልጋል።ስለዚህ የአፍሪካ ኅብረት የፓን አፍሪካኒዝም የተቋም መገለጫ ነው።ነገር ግን ልክ እንደ አውሮፓ ኅብረት ዓይነት ልንሆን የምንችለው እሱ በተቋም ደረጃ ያለ ፓን አፍሪካኒዝም በሕዝብ ተኮር ተስፋፍቶ አንድ ላይ በጥምር መሆን ሲቻል ነው።

**አዲስ ዘመን።- ስአፍሪካ ትንሳኤ የኢትዮጵያ አሁናዊ ድርሻ እንዴት ይገስጻል? ምን መሆን አስበት?**

**ዶክተር አየለ።-** ዋናው ቁም ነገር ራሳችን ተነሳሽነቱን መውሰድ አለብን የሚለው ነው።ለምሳሌ በብዙ ዓይነት መንገድ ሊገለጽ ይችላል።አንዱ መሠረተ ልማት ሲሆን፣ መንገድ በመሥራት ሊሆን ይችላል፤ አሊያም የአየር ግንኙነት በማስፋፋት እንዲሁም ንግድ በማሳለጥ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ ምሳሌ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሀብቱ አፍሪካውያኑን ከቦታ ቦታ ማዘዋወር ነው።በተለይ ከአፍሪካ ወደአውሮፓና አሜሪካ በመውሰድ እና በመመለስ ነው።ልክ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ ድርጅት ሊሆን እንደቻለ እና በጣም የተሳካለት ተቋም መሆን እንደቻለ ሁሉ በዚያ ደረጃ በሕዝብ ለሕዝብም ቢሆን እንዲሁም በንግድም ሆነ መንገድ ሥራም ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት ራሳችን ተነሳሽነቱን ወስደን ማጠናከርና ማስፋፋት አለብን።

ኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ስላለ 800 የሚሆኑ የዓለም ቋንቋዎች በኒውዮርክ ውስጥ አሉ።በኒውዮርክ ሰበብ እየመጣ የተለያየ አገር ዜጋ በከተማዋ እየተቀመጠ በመሄዱ አንድ ሰው በኒውዮርክ ውስጥ እውቀት እስካለው ድረስ የሚወስዱት ለምነውት ነው።ብዙ የዓለም ሕዝብ በኒውዮርክ በመኖሩ ኒውዮርክን ታላቅ አድርገዋታል።

በመጨረሻ ማለት የምፈልገው እኛ ኢትዮጵያውያኑም ሆንን አፍሪካውያን የሚያኮራ ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን። ከዚህ ውስጥ አንዱ ደግሞ የዘመን መፈራረቅ የማያደበዝዘው እና ለመላ ጥቁር ሕዝብ ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል ነው።አፍሪካ ብዙ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አህጉር ናት።ይህን ሀብቷን ለራሷ ጥቅም የምታውልበት ጊዜ ሳይዘገይ ይመጣል።ከ70 በመቶ በላይ በአህጉሪቱ ያለው ወጣት ደግሞ ሥራ የለውም።ለተሻለ ኑሮ እያለ ባሕር እያቋረጠ የሚሄድበት ምክንያት ከዚህ በኋላ ስለማይኖር ባለው ሀብት መጠቀም እንጂ የአገሩ ሀብት በአውሮፓያውኑ መበዝበዝ የለበትም።

**አዲስ ዘመን።- ስሰጡን ማብራሪያ በጣም አመሰግናስሁ።**

**ዶክተር አየለ።-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።።

ልዩ ዕትም

# በድሉ ልክ ያልተዘከረው የዓድዋ ድል

**ስምስም መንግሥቱ**

የአልደፈርም ባይነት፣ የነፃነት፣ የአንድነት፣ የእኩልነት ተምሳሌት፣ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነው የዛሬ 127 ዓመት በቅኝ ግዛት ናፋቂ ጣሊያኖች ላይ ኢትዮጵያውያን የተቀዳጁት ታላቅ ድል፤ የዓድዋ ድል።

ድሉ ኢትዮጵያውያንን፣ አፍሪካውያንን ብቻ ሳይሆን መላ ዓለምን በእጅጉ አስደምሟል፤ እውቅ የውጭ ሀገር የታሪክ እና ሌሎች ጸሐፊዎች በብዕራቸው ስለታሪኩ መስክረውለታል፤ ባለቅኔዎች፣ ደራሲዎች፣ ሰዓሊዎችና ሌሎችም ብዙ ብለውለታል።

ይህ ታላቅ ድል ከኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ መቼም ቢሆን የማይጠፋ፣በትውልድ ቅብብሎሽ ሲታወስ የሚኖርም ነው፤ ዓድዋ! እነሆ መላ ኢትዮጵያውያን አሻራቸውን ያኖሩበት ታላቁ የዓድዋ ድል ዛሬ 127ኛ ዓመት በዓሉ በድምቀት እየተከበረ ይገኛል።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለማንበርከክ ያደረገችውን ወረራ ተከትሎ ኢትዮጵያውያን የዛሬ 127 ዓመት በዛሬው ዕለት ዓድዋ ላይ ጣሊያኖችን ድል በማድረግ የጻፉት ደማቅ ታሪክ፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በየዓመቱ በአደባባይ፣ በውይይት፣ በኤግዚቢሽን፣ በስዕልና በሌሎች የሥነጥበብ ዘርፎች ሲዘከር ኖሯል፤ እየተዘከረም ይገኛል።

በዚህ ጦርነት ያልተሳተፈ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ለእዚህም ነው ድሉ የጋራ ነው የሚባለው። የወቅቱ የሀገሪቱ መሪ ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ጣሊያኖች የሀገር ሉዓላዊነትን መዳፈራቸውን በመጥቀስ፣ ይህን ወረራ ለመቀልበስ ጉልበት ያለው በጉልበቱ፣ አቅም የሌለው ደግሞ በፀሎቱ ከጎናቸው በመሰለፍ እንዲከተላቸው ያደረጉትን ጥሪ ተከትሎ ኢትዮጵያውያን ከየአቅጣጫው ወደ ጦር ሜዳው ተመሙ። ጡት የሚጠባ ሕጻንና አረጋዊ ካልሆኑ በስተቀር በዚህ ጦርነት ያልተሳተፈ አልነበረም። የፆታ፣ ዘርና ኃይማኖት ልዩነት ያልታየበት ሁሌም በተሳተፈበት ጦርነት፣ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን ገብረው የታፈረችና የተከበረች ሀገር አቆይተዋል። በመስዋዕትነቱ በተገኘው ድልም ብቸኛዋ በቅኝ ያልተገዛች የጥቁር ሕዝብ ሀገር ኢትዮጵያን ለዛሬው ትውልድ ማቆየት ተችሏል።

ድሉ ጠላትን አሳፍሮ ከመመለስም በላይ ትርጉሙ ሰፊ ነው ሲሉ ምሑራን፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ወዘተ ይገልጻሉ። በእጅጉ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ፣ በጦር ስልቱም ቢሆን ተወዳዳሪ የለውም ከተባለ ኃይል ጋር በመፋለም ነው ድሉ የተገኘ ድል እንደመሆኑም በእርግጥም ታላቅ ድል ነው።

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት፤ ‹እምቢ ለነፃነቴና ለሀገሬ ክብር› ብሎ ወደ ፍልሚያው የገባው ኢትዮጵያዊ ለእግሩ ጫማ አልነበረውም፤ ጥሻና ገደሉን በባዶ እግሩ በመውጣትና በመውረድ ነው የተዋጋው። በእጁ የያዘው መሣሪያም የጠላትን ጦር ይመክታል ብሎ የሚገመትም አልነበረም። ኢትዮጵያውያን ኋላቀር የሚባለውን መሣሪያ ሊያውም በበቂ ሁኔታ ሳያገኙ፣ ጦርና ጋሻ ይዘው፣ ታላቅ ወኔ ተላብሰው፣ የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒሊክና የእቴጌ ጣይቱን የጦርነት ስልት ተጠቅመው በመዋጋት ጠላትን መግቢያና መውጫ አሳጥተው ነው ዓድዋን ያህል ታላቅ ድል መቀዳጀት የተቻለው።

በጦርነቱ የሴቶች ሚና ከፍተኛ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። እቴጌ ጣይቱ በዚህ ጦርነት በሰጡት አመራር ሁሌም ይጠቀሳሉ። ቁስለኛን በመንከባከብ፣ ውሃና ስንቅ በማቀበል፣ የደከመን በማበረታታት በአጠቃላይ ሴቶች ለድሉ መገኘት ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። ድሉ የመላው ኢትዮጵያውያን ነው የሚያሰኘውም ከዚህ ከዚህ በመነጨ ነው።

ከሰፊው የዓድዋ ድል ታሪክ ውስጥ ጥቂቱን እንኳን ሰምተው ብዙዎች ለዓድዋው ድል ጀግኖች አድናቆታቸውንና አግራሞታቸውን ይገልጻሉ። የዓድዋ ድል በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሄዱ ኢትዮጵያውያን በልበ ሙሉነት የሚናገሩት የሚያኮራ ታሪክ ነው።

ይሁን እንጂ ይህን ታላቅ ታሪክ ለትውልድ በማሸጋገር በኩል ፣ዓመት ጠብቆ በማክበር ቀኑን ለመዘከር ከሚደረግ ጥረት ባለፈ የዓድዋ ድልን ታላቅነት የሚመጥን የታሪክ ማስታወሻ በማኖር በኩል ብዙ አለመሠራቱ ብዙዎችን በእጅጉ ሲያነጋግር ቆይቷል።

በዓድዋ ስም የሚጠሩ አንዳንድ ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል። ጦርነቱን የመሩት የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ አደባባይ አንዱ ዓድዋ የሚዘከርበት ታላቅ ስፍራ ነው፤ የዓድዋ ዘማቾች የተሻገሩበት በቀበና ወንዝ ላይ የተሠራ ድልድይ በዓድዋ ስም ይጠራል። በአዲስ አበባ በዓድዋ ስም በቅርቡ አንድ ትምህርት ቤት ተሰይሟል። በዓድዋ ጀግኖች ስም የተሰየሙ ድልድይ ፣ትምህርት ቤት የተሰየመበት ሁኔታም ይስተዋላል።

የዓድዋ መቶኛ ዓመት በ1988 በተከበረበት ወቅት የዱር እንስሳት ጭምር እንዲኖሩት የሚደረግ ዙ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቦታ ተከልሎ እንደነበርም ይነገራል። ይህ ፓርክ ግን ዛሬም ድረስ አልተገነባም።

ሁሉም ግን ከድሉ ታላቅነት አኳያ ሲታይ እንደሚያንሱ በመጥቀስ ጭምር ነው ትችቱ ሲሰነዘር የቆየው። የዓድዋን ታሪክ በሰው ልብ ውስጥ ሊያስቀሩ በሚችሉ መልኩ ማስታወሻዎች ሊኖሩ እንደሚገባ ይገለጻል።

ከዚህ ሁሉ ትችት በኋዋላ እርግጥ ነው ቆይቶም ቢሆን ጥያቄውን መመለስ የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ተይተዋል። የዓድዋ ድል ለፓንአፍሪካኒዝም ንቅናቄ ይበልጥ መቀጣጠል ጉልህ አስተዋፅዖ እንዳበረከተ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህን ታሳቢ ያደረገ የፓንአፍሪካ ዩኒቨርስቲ በዓድዋ ከተማ ለመገንባት ሥራዎች ተጀምረውም ነበር።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ዓድዋን በሚገባ ይዘክራል የተባለ ታላቅ ሙዚየም በመሐል ፒያሳ እያስገነባ ነው። ሙዚየሙ በውስጡ ይይዛቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ጉዳዮች በእርግጥም ሙዚየሙ የዓድዋን ድል ይመጥናል ብሎ መናገር የሚያስችሉ ናቸው።

እኛም የድሉን ያህል የገዘፈ፣ ሁሌም ሊታሰብ በሚችል ደረጃ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መታሰቢያ ሊገነባ አለመቻሉ ያሳሰባቸውን ኢትዮጵያውያንን አስተያየት ለታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አየለ በከሪ አንስተንላቸው ሙያዊ ሀሳባቸውን ሰጥተውናል።

ፕሮፌሰር አየለ በከሬ የካቲት 23 ቀን በ1888 ዓም ዓድዋ ላይ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት አሰፍስፎ ከመጣው የጣሊያን ሠራዊት ጋር በተካሄደው ጦርነት ኢትዮጵያውያን የተቀዳጁት ድል ብስራት በዓለም መሰማቱን፣ ሕዝብንም በእጅጉ ማስደመሙን ይገልጻሉ።

በአንድነትና በሀገር ፍቅር ስሜት የተነሳሳ ሕዝብ ያስመዘገበው ድል መሆኑም ታሪኩን ያጎለዋል ያሉት ፕሮፌሰሩ፣ በጦርነቱ ቁጥሩ እስከ ሰባት ሺ የሚደርስ የኢትዮጵያ ጦር መሰዋቱንም ነው የተናገሩት። የዓለምን ቀልብ የሳበ ግዙፍ ታሪክ የያዘው የዓድዋ ድል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን መላው ጥቁር ሕዝብ የሚዘነጋው አይደለም ብለዋል።

ይህ ታላቅ ገድል የተፈፀመበትን ቦታ ለማየት የረጅም ጊዜ ምኞትና ፍላጎት እንደነበራቸው የሚናገሩት ፕሮፌሰር አየለ፤ ተሳክቶላቸው በአንድ ወቅት ለማየት ወደ ሥፍራው መሄዳቸውን ይገልጻሉ። በስፍራው ታሪኩን የሚያስታውስ አሻራ አለማግኘታቸውን፣ በዚህም በጣም ማዘናቸውን ተናግረዋል። ዓድዋ በውስጡ የሰውና የተለያየ ታሪክ መያዙን ፕሮፌሰር አየለ ገልጸው፣ ዓድዋ ጦርነት ጀብድ የፈፀሙትን ጨምሮ እያንዳንዱን ክስተት በታሪክ ሰንዶ የክብር ማስታወሻ በማስቀመጥ ትውልድ እንዲቀባበለው ማድረግ ያስፈልግ እንደነበርም ነው የተናገሩት።

እንደ ፕሮፌሰር አየለ ገለፃ፤ አብዛኞቹ የአውሮፓ ሀገሮችም ሆኑ አሜሪካ ከተሞቻቸውን ያደመቁት በክብር ለሀገራቸው የተሰው ዜጎቻቸውንና የተለያየ ታሪክ የያዙ ማስታወሻ ሐውልቶች በማኖርና መናፈሻ(ፓርክ) በመሥራት ነው። በመናፈሻ ውስጥ የሚዝናኑም ሆኑ ሐውልት የሚጎበኙ እግረ መንገዳቸውን ታሪኩን እንዲያስታውሱ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

በኢትዮጵያ በዓድዋ ድል መታሰቢያነት የዓድዋ ድልድይ ይጠቀሳል። ጄኔራሎች በውስጡ እንደሚይዝ የተነገረለትና በፒያሳ ግንባታው እየተካሄደ ያለው የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት የሚበረታታ ተግባር መሆኑን ተናግረዋል። ፕሮፌሰር አየለ ዓድዋ ግዙፍ ታሪክ ያለው ከመሆኑ አኳያ አሁንም ቢሆን የተሠራው ሥራ በቂ ነው የሚል እምነት የላቸውም።

ዶጋሊ ላይ ከጣሊያኖች ጋር በተካሄደ ጦርነት 500 የጣሊያን ወታደሮች ማለቃቸውን ጠቅሰው፣ ይህን ጦርነት ለመሩት ራስ አሉላ አባ ነጋ ጣሊያን ሀገር ትልቅ የማስታወሻ ሐውልት መሠራቱን ገልጸዋል። በጦርነቱ ላይ የተሳተፉ ጄኔራሎች ሳይቀሩ ነው በሀገራቸው ሐውልት የተሠራላቸው። ጣሊያኖቹ አሸንፈው ሳይሆን ተሸንፈው ነው ማስታወሻ ሐውልት ያቆሙት። ኢትዮጵያ ግን ዓድዋ ላይ አኩሪ ገድል ፈጽማ የዓድዋን ድል የሚዘክር ማስታወሻ በማቆየት በኩል የተሠራው በቂ ነው ብዬ አላምንም›› ሲሉ አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር አየለ ኢትዮጵያ ግን ከራስዋ አልፎ ለሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች የሚተርፍ ታሪክ መሥራቷን ጠቅሰው፣ በዚህ ልክ ሰዎች ታሪኩን በየጊዜው እንዲያስታውሱት የሚያደርግ ሥራ ተሠርቷል የሚል እምነት እንደሌላቸው ይናገራሉ።

መንግሥት የሳይንስ ሙዚየምን ጨምሮ በተለያየ አካባቢ የሠራቸውን እንደ ሕዝብ መናፈሻዎች (ፓርኮች)፣ አብርኆት ቤተመጽሐፍት አይነት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የዓድዋ ድልን የሚዘክር ፓርክ ቢሠራ ሰዎች ታሪኩን በየእለቱ የማየት እድል እንደሚያገኙና ታሪኩንም ለማወቅ እንደሚያግዛቸው ጠቁመዋል።

ዓድዋን የቱሪስት መዳረሻ ማድረግም እንደሚቻል ነው የጠቆሙት። በጦርነቱ ላይ ተሳትፎ የነበራቸውን ሰዎችና የፈፀሙትን ገድል በሚያስታውስ መልኩ ፓርኩ ቢዘጋጅ ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት የጎላ ፋይዳ እንደሚኖረውም ነው የተናገሩት።

ጦርነቱ ተደርጎ ድሉ በተገኘበት የዓድዋ ከተማ ፓንአፍሪካን ዩኒቨርስቲ ለማቋቋም በመንግሥት እንቅስቃሴ ተጀምሮ በነበረበት ወቅት እርሳቸውም የዚህ እቅድ አስፈጻሚ አካል ሆነው እንደነበር የጠቆሙት ፕሮፌሰር አየለ፣ ለዩኒቨርስቲው መሥሪያ 150 ሄክታር መሬት የትግራይ ክልል መንግሥት ሰጥቶ እንደነበርም ያስታውሳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለዩኒቨርስቲው ግንባታ ወደ 250 ሚሊዮን ብር በጀትም ተመድቦ ነበር፣ከሌላው አፍሪካ ሀገር ጋር በባህልና በተለያየ መንገድ መተሳሰር በሚችልበት ሁኔታ ላይም የታሪክ ምሑራን የሚጠበቅባቸውን ዝግጅት አድርገውም ነበር፤ የዩኒቨርስቲው መገንባት ዓድዋን እንደሚያጎላ ተስፋ ተጥሎበት ነበር።

በዚህ መንገድ ሦስት ዓመታት የተደከመበት ፕሮጀክት የታለመለትን ዓላማ አሳክቶ ለውጤት አለመብቃቱ እንዳስቆጫቸውም ፕሮፌሰር አየለ ይገልጻሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ ሀሳብ ተፈጥሮ ወደ እንቅስቃሴ ከተገባ በኃላ ዳር ሳይደርስ የመቅረት ጉዳይ ያልተቀረፈ ችግር እንደሆነም ነው ያመለከቱት።

ዓድዋ በሁሉም ልብ ውስጥ በሚቀርና ሁሌም በሚታወስ መልኩ እንዲታሰብ ለማስቻል እንደ አንድ ታሪክ ተመራማሪ ከእርሳቸው የሚጠበቀውን አስመልክቶ ፕሮፌሰር አየለ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ከሌሎች የሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ዓድዋ ፓንአፍሪካ ዩኒቨርሲቲ እንዲመሠረት ከማድረግ ጀምሮ ያላቸውን እውቀት በተለያየ መንገድ በማካፈል በበጎ ፈቃደኝነት እንዲሁም ጽሑፍ በማበርከት የሚጠበቅባቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

እነዚህ እንቅስቃሴዎች ደግሞ ተተኪው ትውልድ ዓድዋን እያቀነቀነ እንዲያስቀጥል የሚያግዙ ይሆናሉ ነው ያሉት። ዓድዋ በትልቁ ጎልቶ እንዲነሳና ተምሳሌትም ይሆናል ብለው የሚያስቡት ከፍጻሜ ያልደረሰውን የዓድዋ ፓንአፍሪካ ዩኒቨርስቲ የማቋቋም እቅድ ፕሮጀክትን ነው።

ስለ ዓድዋ ያለው ትውስታና ምልከታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካልሆነ በስተቀር ተረስቶ ነበር ማለት ይቻላል ያሉት ፕሮፌሰር አየለ፤ የካቲት 23 ቀን ከተከበረ በኃላ እንቅስቃሴውም አለመኖሩንና እንደማይታወስ ነው የገለጹት። ወደፊት ግን የዓድዋ ድል በድሉ ልክ የሚዘከርበት ሁኔታ በተሻለ ጎልቶ ይወጣል የሚል እምነት አላቸው።

በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለዓድዋ ያለው ግንዛቤ ቀደም ካለው ጊዜ እየተለወጠና እየተሻሻለ መምጣቱን መረዳታቸውን ጠቅሰው፣ ይህም የተሻለ ነገር እንደሚመጣ ተስፋ አሳድሮባቸዋል። ታሪክን ጠንቅቆ አለመረዳት መሠራት የሚፈለገውን ሥራ ላለመሥራት እንቅፋት እንደሚሆን በመጠቆም፤ በዚህ ረገድም መሠራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

እንኳን ለ127ኛው ዓመት የአንድነት፣ የጀግንነት እና የፅናት ተምሳሌት ለሆነው የዓድዋ የድል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ለዘመናት እናንተን ስናገለግል ቆይተናል፤ ወደፊትም አገልግሎታችንን በተሻለ ጥራት፣ ተወዳዳሪና ደንበኛ ተኮር እንዲሆን ተግተን እየሠራን እንገኛለን።

ውድ የድህረ-ክፍያ አገልግሎት ደንበኞቻችን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳባችሁን በቴሌ ብር፣ በሲቢኢ ብር፣ በሞባይልና በኢንተርኔት ባንኪንግ አማካኝነት ሲከፍሉ ጊዜዎትንና ገንዘቦትን ይቆጥባሉ።

በተጨማሪ የቅድመ ክፍያ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞቻችንም ሳትዘናጉ በወቅቱ የሚበቃችሁን መጠን ኃይል ካርዳችሁን በማስሞላት እንድትጠቀሙ እያሳወቅን፣ ካርዳችሁን በወቅቱ ሳትሞሉ ኃይል የምትጠቀሙ ከሆነ በአቅራቢያችሁ የሚገኝ የአገልግሎት መስጫ ማዕከልን በማናገር መፍትሄ ያግኙ ያቅሉ! በወቅቱም የፍጆታ ሒሳብዎንም በመፈፀም ከተጠያቂነት ይዳኑ።




የዘመናዊ የክፍያ አማራጭ ምርጫዎ ይሁን! ኑሮዎንም ያቅሉ! በወቅቱም የፍጆታ ሒሳብዎንም በመፈፀም ከተጠያቂነት ይዳኑ።

መልካም የነፃነት በዓል፤ ዓድዋ!

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

Ahri
...for better health

## ከአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አህሪና ችግር ፈቺ ምርምሮቹ

የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት (አህሪ) በርካታ ችግር ፈቺ ምርምሮችን እያከናወነ በውጤቱም ማህበረሰቡንና ሀገርን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል። እኛም ለዛሬው ዝግጅታችን በተቋሙ በሳንባ በሽታ ህክምናና በወባ በሽታ ላይ የተደረጉ ምርምሮችና የተገኙ ውጤቶችን እንደሚከተለው ይዘንላችሁ ቀርበናል።

የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት የሳንባ በሽታ ህክምናን ቀላልና የበለጠ ፍቱን ለማድረግ ባካሄዳቸው የምርምር ሥራዎች በጣም ብዙ አስተዋጽኦዎችን ማድረግ ችሏል። ከዚህ ቀደም እንደዛሬው የሳንባ በሽታ (ቲቢ) ምርመራ ባልነበረበት ወቅት የበሽታው አምጪ ተህዋስ የሚመረመረው በአጉሊ መነጽር ነበር። በዚህ ምርመራ በጣም በርካታ ሰዎች የቲቢ በሽታ እያለባቸው የምርመራ ውጤታቸው በሽታው እንደሌለባቸው የሚያሳይ ነበር። በአጉሊ መነጽር ይደረግ የነበረውን የሳንባ በሽታ ምርምራን ለማስቀረት ኢንስቲትዩቱ በጣም ወጪ ቆጣቢ የሆነውን ፈሳሽ የንጽህና መጠበቂያ በረኪናን በመጠቀም ለረጅም አመታት የመመርመሪያ ስልት አድርጎ ተጠቅሞበታል። ይህ የመመርመሪያ ዘዴ አክታ ውስጥ ያውን የሳንባ በሽታ አምጪ ተህዋስ አንድ ላይ እንዲጠራቀም በማድረግ አንድ ላይ የተሰበሰበውን ባክቴሪያ በአጉሊ መነጽር ለመመርመር አስችሏል።

በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ እጢዎቻችን በተለይ አንገት ላይ የሚገኘው እጢ በሳንባ በሽታ ይጠቃል። ይህ በአንገት እጢ ላይ የሚከሰተው የሳንባ በሽታ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሌሎች ሀገራት በተለየ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። እንዴት በዚህ ደረጃ ተገኘ የሚለው ግን በምርምር አልተረጋገጠም። በሽታውን ለማከም ይደረግ የነበረው ምርመራም የሚካሄደው ናሙና ካበጠው እጢ ቆርጦ በመውሰድ ነበር። ይህ ደግሞ በታካሚው ላይ ከፍተኛ ስቃይን ያደርሳል። ለዚህ መፍትሄ ለመፈለግም የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች በሰሩት ስራ ለምርመራ የሚወሰደው ናሙና ካበጠው እጢ ላይ በመርፌ ተወስዶ መመርመር እንደሚቻል አረጋግጠዋል። ይህ በመርፌ የሚወሰደው ናሙና ትክክለኛና አዋጭ በመሆኑ እስካሁን ድረስ በሽታውን ለማከም ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።

ከዚህም ባሻገር ኢንስቲትዩቱ መሠረታዊ የባዮሜዲካል ምርምር የሚባሉት በሽታ አምጪ ተህዋስያን ከሰው ጋር ያላቸው መስተጋብር ምን ይመስላል የሚለውን ለማወቅ በርካታ ምርምሮችን አከናውኗል። ከእነዚህም ምርምሮች ውስጥ የተላመደው የቲቢ ባክቴሪያ የተነሳው ከኢትዮጵያ እንደሆነ በዘረመል ምርመራ ያሳየበት አንዱ ነው። ለዚህ ምክንያቱም ሌላ ሀገር በሄደ ቁጥር ሀገሩንና እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ለመልመድና ለመላመድ ራሱን ይቀይራል። በኢትዮጵያ ያልተቀየረ ብዙ ዓይነት የቲቢ ባክቴርያ ዝርያ እንዳለም በዘረመል ምርመራው ማሳየት ተችሏል። የዚህ ምርመራ ጠቀሜታ የህክምናው ዓይነት ምን መሆን አለበት? የበሽታው የመከላከል ዘዴውስ ምን ይመስላል የሚለውንም የሚናገር ይሆናል።

በተመሳሳይ በኢንስቲትዩቱ በወባ በሽታ ላይ በተደረጉ ምርምሮችም እንደ አርማወር ሀንሰን ኢንስቲትዩት የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እስካሁን በርካታ ምርምሮች ተከናውነዋል። ምርምሮቹ የተካሄዱትም በወባ አምጪ ተህዋስ ላይ ነው። የወባ በሽታ በወባ ትንኝ አማካይነት የሚመጣ ሲሆን ለበሽታው መዛመት ተህዋሱም ትንኟም ሲኖሩ ነው። በወባ በሽታ ላይ የተካሄዱ ምርምሮች ውጤቶች ምልክት ሳያሳዩ የወባ አምጪ ተህዋስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ በርካታ ሰዎች አሉ። በመሆኑም ምልክት የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ምልክቱ የማይታይባቸውም ተመርምረው ሊታከሙ እንደሚገባ በምርምር የተደገፈ መረጃ ለጤና ሚኒስቴር ቀርቧል። ይህ ከተደረገ የሚታከሙት ሰዎች ቁጥር በርካታ ስለሚሆን በቂ በጀት የሚያስፈልግ በመሆኑ የጤና ሚኒስቴርም እነዚህን ሰዎች ማከም ይቻላል ወይንስ አይቻልም የሚለውን እየፈተሸ ይገኛል። ይህም ሆኖ እነዚህ ሰዎች በወቅቱ ካልታከሙ የወባ በሽታ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚተላለፍ የሚያሳይ ውጤት በመገኘቱ በተመረጡ 240 ወረዳዎች የወባ በሽታን ለማጥፋት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል።

በሌላ በኩል ኢንስቲትዩቱ አዲስ የወባ በሽታ አምጪ ተህዋስ አስተላላፊ ትንኝ በኢትዮጵያ የተለያዩ ከተሞች መገኘቷን በምርምር አረጋግጧል። ይህቺ የወባ ትንኝ ብዙውን ጊዜ በደቡብ የእስያ ሀገሮች በህንድ በፓኪስታንና በኢራን በከፍተኛ ሁኔታ በከተሞች የወባ በሽታን የምታስተላልፍ ነች። ወደ ኢትዮጵያ የገባችው በጅቡቲ በኩል ሲሆን መጀመሪያ የተገኘችው በሶማሌ ብሔራዊ ክልል ነው። አሁን ላይ እስከ መካከለኛውና ሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ተሰራጭታለች። በተጨማሪ በኢትዮጵያ የሚገኙ የወባ በሽታዎችንም እንደምታስተላልፍ ኢንስቲትዩቱ በቤተ ሙከራ ባደረገው ምርመራ አረጋግጧል። ቀደም ሲል የነበሩት የወባ በሽታ ተህዋስ አስተላላፊ ትንኞች በሽታውን የሚያስተላልፉት ከከተሞች ውጪ ነበር። ይቺኛዋ ግን በከተሞች ብቻ የምታስተላልፍ ነች።

ኢንስቲትዩቱ ለጤና ሚኒስቴር ጠቃሚ የመፍትሄ ሀሳብ አቅርቦ በዚች የወባ በሽታ ተህዋስ አስተላላፊ ትንኝ ሳቢያ የሚመጣውን የወባ በሽታ የመከላከያ ዘዴና የመቆጣጠሪያ መንገድ እንዲዘጋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶት የመጀመሪያውን ረቂቅ አዘጋጅቶ አቅርቧል። ጤና ሚኒስቴርም ትንኟ በከፍተኛ ሁኔታ ሳትስፋፋና ሳትሰራጭ መቆጣጠር የሚቻልበትን መመሪያ እንደሚያዘጋጅ ይጠበቃል። ይህቺ የወባ በሽታ አስተላላፊ ትንኝ «አኖፌለስ ስቴፈንሳይ» ትባላለች። ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ተባባሪ አካላት ጋር ባካሄደው ጥናት ትንኟ በኢትዮጵያ በሶማሌ በአፋር በአማራና በምሥራቅ ኦሮሚያ ክልሎች በመስፋፋት ላይ ስትሆን በ13 ከተሞች ተሰራጭታለች። ከእነዚህም መካከል ሰመራ፤ ገዋኔ፤ አዋሽ፤ ኤረር፤ ጅግ ጅጋ፤ ቀብሪደሃር፤ ጎዴ፤ ደጋሀቡር፤ ድሬዳዋ፤ መተሀራ ባቱ፤ መቂና ሞጆ ይጠቀሳሉ። «አኖፌለስ ስቴፈንሳይ» ትንኝ ዝርያዋ ከቅርብ አመታት ወዲህ የተገኘው በምሥራቅ የአረብ ልሳነ ምድርና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ነው።


የትንኟ ዝርያ በኢትዮጵያ የታየው በ2008 ኣ.ም ነው። ከዚያ ቀደም ባሉት ጊዜያት በምሥራቅ አረብ ፔንሱላ ይታይ ነበር በአፍሪካ ቀንድ ለመጀመሪያ ጊዜ በጅቡቲ በ2004 ኣ.ም ተገኝቷል። የምትራባው ለውሃ ማጠራቀሚያ በሚዘጋጁ የተጣሉ ጎማዎች፤ የፕላስቲክ እቃዎች የተለያዩ ስሪት ያላቸው የውሃ ማጠራቀሚያዎች ሲሆን አብዛኛውን የጸረ- ወባ ትንኝ መድኃኒት መቋቋም መቻሏ መገለጫዋ ነው። ጥናቱ በኢንስቲትዩቱ በዩ.ኤስ.አይ.ዲ ቪክቶርሊንክ የኢትዮጵያ ፕሮጀክት፤ በኔዘርላንድስ ሬድቦርድ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ማእከልና በብሪታኒያ የለንደን ስኩል ኦፍ ሀይጂን ኤንድ ትሮፒካል መወዲስን ትብብር የተካሄደ ነው።

# የኢትዮጵያውያን የጦር ሜዳ ውሎና የአሸናፊነት ምስጢር

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



ብርጋዴር ጄነራል ውበቱ ጸጋዬ



ብርጋዴር ጄነራል ዋሲሁን ንጋቱ

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ጊዜያት በበርካታ የጦር አውድማዎች ተፈትነዋል። ከአውሮፓ እስከ አፍሪካ ያሉ ወራሪዎችና ቀኝ ገዢዎች አቅማችን በረታ አልያም ኢትዮጵያ ደከመች ብለው ሲያስሰቡ መድፍና ጥይቶቻቸውን ሰብስበው በወረራ ለማንበርከክ ሞክረዋል። ነገር ግን እነዚህ ወራሪዎች በለስ ቀንቷቸው እንደ ሌሎች አገራት የቅኝ ግዛት ቀንበራቸውን ለመጫን የሞከሯቸው ሙከራዎች ሁሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች በከፈሏቸው አነጋጋሪ ተጋድሎዎች መክነው ቀርተዋል። ለመሆኑ ይህ በዓለም የጀግንነት መዝገብ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ያስመዘገበ፤ በትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ የደረሰ ለአገርና ለሕዝብ የሚከፈል መስዋእትነት እንዴት ጸንቶ ኖረ፤ ስንል በቀድሞ የኢትየጵያ ጦር ሰራዊት ውስጥ ለረጅም ዘመናት ያገለገሉ የጦር መኮንኖችን አነጋግረን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

የመጀመሪያው እንግዳችን በኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ውስጥ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር ለሰላሳ አመታት ያህል ሕዝባቸውን ሲያገለግሉና አገራቸውን ከወራሪና አፍራሽ ሲጠብቁ የኖሩት ብርጋዴር ጄኔራል ውበቱ ጸጋዬ ናቸው። እሳቸው እንደሚያብራሩት፤ ዛሬ የምንኖርባት ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት የነፃነት ተምሳሌትነት ለመገኘት በርካታ ኢትዮጵያውያን ዘመን የማይሽራቸውን መስዋእትነትን ከፍለዋል። አገሪቱ የቅኝ ግዛት ተስፋፊዎች ቀዳሚ ዓይን ማረፊያ የነበረች ቢሆንም በልጆቿ ህብረትና የአገር ፍቅር እንደተመኙት ሳትሆንላቸው ቀርታለች። ይህ ታሪክ ደግሞ ተረት ወይንም አፈታሪክ ሳይሆን ተሸናፊዎች ሳይቀር የዘገቡት እውነተኛ ተጋድሎ ነው። ለዚህ ደግሞ ብልሀት ከተሞላበት አመራር ባሻገር በዘመኑ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በመሉ የሚጠበቅባቸው ሲወጡ የቆዩ ሲሆን ይህንንም ተግባራቸውን ለትውልድ ሲያስተላልፉ ነበር።

እስከ ቅርብ ጊዜ አባቶች እንኳን በቁም ነገር መሀል በቀልድ ውስጥ ሳይቀር ስለአገር ፍቅርና ለሕዝብና ለአገር የሚከፈል መስዋእትነት ምን ያህል የሚያኮራ እንደነበር ሲተርኩ ሲያስተምሩ ኖረዋል። በየቀኑ በየምክንያቱ የሚነገሩ የጦር ሜዳ ተጋድሎዎችና ጀብዱዎች ቀጣዩ ትውልድ ለአገሩ ምን ማድረግ እንዳለበት የሚያስተምሩ ነበሩ። ቀደምት ኢትዮጵያውያን ይህንን ያደርጉ የነበሩት በዋናነት ያለፈ ታሪካቸው ተወስቶ እንዲወደሱ እንዲመሰገኑ በማሰብ ሳይሆን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያና መቼም የማይተኙላቸው ምቹ ቀን የሚጠብቁላቸው ጠላቶች እንዳሉባቸው በማስታወስ ትውልዱን ለማዘጋጀት ነበር። የአገር ሉአላዊነት የሰንደቅ አላማ ክብር ሁሉ ሲወሳ ሲዘከር የኖረው ከትውልድ ወደ ትውልድ አገርን ብቻ ሳይሆን ነፃነትንም ማስተላለፍ እንደሚቻል በማመንም ጭምር ነው። ከቀልድ እስከ ኪነጥበባዊ ሥራዎች በሚስትና ባገር ቀልድ የለም እየተባለ በለጋ ዕድሜው እየተነገረው ያደገ ትልውድ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው። ይህም በመደረጉ በትውልዱ ውስጥ የወራሪዎች ፍላጎትና አላማ ኢትዮጵያን በመበታተን ኢትዮጵያውያንን ማዋረድ እርስ በእርስ በማበላላት ሀብትኗ የዜጎቿን ጉልበት መዝረፍ መሆኑን ሁሉም ሲገነዘበው ኖሯል።

በአገር ጉዳይ የሃይማኖት አባቶች አስተምህሮ ሳይቀር ለአገር መሞት ለጽድቅ የሚያበቃ እንደሆነ የሚነግር ተመሳሳይ ነበር። ይህ በመሠራቱም ነው ዛሬም ድረስ ስለ ኢትዮጵያ ሲባል ለመሰዋት የማይሳሳ በደሙ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን የያዘ ትውልድ ለመፍጠር የተቻለው። በዚህም ኢትዮጵያ በታሪኳ በሁሉም ዘመን ከውጭ ወራሪዎች ጋር ባደረገቻቸው ጦርነቶች ተሸንፋ በቀኝ ግዛት ስር ወድቃ አታውቅም፤ ወራሪዎችም እንደተመኟት ተበታትና አልፈራረሰችም። ይልቁንም ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ በኢትዮጵያዊነት መደራደርን የቁም ሞት ያህል የሚጸየፍ ትውልድ እየተፈጠረ ዛሬ ላይ ለመድረስ በቅተናል። ዛሬም ድረስ ሕዝቡ ለአገሩና ለሰንደቅ አላማው ቀናኢ ሆኖ የሚያስደምሙ መስዋእትነቶችን ሲከፍል እየተመለከትን እንገኛለን።

አንድ ሰራዊት በጦርነት አሸንፎ ለመውጣት በየትኛውም ቦታ ከሁሉም ነገር በላይ መሟላት ካለባቸው ነገሮች መካከል ሥነሥርዓት፤ ስልጠና ወይንም ትምህርትና ሞራል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። በተለይም ሞራልን በተመለከተ ናፖሊዮን በጦር ሜዳ ውሎ አሸናፊ ለመሆን ሦስት አራተኛውን ድርሻ የሚይዘው ሞራል እንደሆነ ያስቀምጣል። የኢትዮጵያ ሰራዊትም በጦር ሜዳው ውሎው ዘመኑን የሚመጥን በቂ የጦር መሳሪያ ያልነበረው ቢሆንም በነበረው ጠንካራ ሞራልና አይደፈሬነት ወራሪዎችን አንገት ሲያስደፉ ቆይቷል።

አገር ከጥቅም በላይ ከማንነት በላይ ናት በየትም አገር የውትድርና ሕይወት መጨረሻው ነፍስን አሳልፎ እስከ መስጠት በደረሰ መስዋእትነት ሕዝብን በመታደግ አገርን ማስቀጠል ነው። ይህንን ደግሞ ኢትዮጵያውያን በትውልድ ቅብብሎሽ ሲከውኑት ኖረዋል። ወደፊትም ይህንን ለማስቀጠል እንደ ዓድዋ ያሉ የድል በዓላትን ስናስብ በአንድ ወገን ቀድሞ ለአገራቸው መስዋእትነት ከፍለው አገር ያቆዩትን በክብር እያዘከርን፤ በሌላ በኩል ዛሬም በዱር በገደሉ ለአገርና ለሕዝብ ሲሉ እየተዋደቁ ላሉትም ተገቢውን ክብርና እንክብካቤ በማድረግ ሊሆን ይገባል። በአንዳንድ አገራት ወታደሮች በመንገድ ሲንቀሳቀሱ የአገሩ ዜጎች ላደረጉት አስተዋጽኦ ምስጋና ሲያቀርቡ ይታያሉ። የዚህ ዓይነት ልምዶች በኢትዮጵያም መስፋፋት አለባቸው።

ይህም ሆኖ እስከ ዛሬ ያለውን የአገር ፍቅር ስሜት በወታደሩም በሕዝቡም ዘንድ እንዲቀጥል ብዙ መሥራት ይጠበቃል። ለወታደሩ የአካል ብቻ ሳይሆን ጠንካራ የሥነ ልቦና ስልጠናም መስጠት ይጠበቃል። በአንዳንድ አገራት ረጅም አመት ያገለገሉና በጡረታ የተገለሉ የጦር መኮንኖችንና በዘርፉ ጥሩ ልምድና ትምህርት ተሞክሮ ያላቸውን እየጋበዙ አዲስ የሚመለመሉ ሰራዊቶቻቸውን እንዲያሰለጥኑላቸው ያደርጋሉ። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ለሰራዊቱ የልምድ ልውውጥና እውቀት ከማሸጋገሩ ባለፈ የዛሬዎቹ ወጣት ወታደሮች ነገ አገራቸው ተጠቅማ እንዳማትጥላቸው መንግሥትና ሕዝቡም ከጎናቸው እንደሚሆን ማሳያ ነው። በኢትዮጵያም በተመሳሳይ ከውትድርና ሙያ ጋር በተለያየ ዘርፍ እውቀት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በመሰብሰብ ሰራዊቱን እንዲያስተምሩና የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ ይጠበቃል።

በየትኛውም ዓለም አገር በወታደር አልያም በከፍተኛ የፖለቲካ አመራሮች ብቻ አትጠበቅም አገር በነፃነት ተጠብቃ ታፍራና ተከብራ ልትኖር የምትችለው ከኋላ ሆኖ በሚደግፈው ደጀን በሚሆነው ሕዝብ አለሁ ባይነት ነው። ሁሉም እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ አንድ ሉአላዊት አገር ብትሆንም በውስጧ የተለያዩ ማንነት ያላቸውን ሕዝቦች ያቀፈች ናት። በዘመናት ሂደት እነዚህን ሕዝቦች በቀዳሚነት በአንድነት ሲያንቀሳቅሳቸው የነበረ ጉዳይ ቢኖር በህብረት የሚኖሩባትን አገራቸውን ኢትዮጵያን የሚነካ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ከወራሪዎች ጋር ባደረገቻቸው ተጋድሎዎች በሙሉ ከደጀንነት እስከ ከጦር ሜዳ ተጋድሎ መስዋእትነት ያልከፈለ አጥንቱን ያልከሰከሰ ደሙን ያላፈሰሰ ሕዝብ የለም።

ይህም ሆኖ ኢትዮጵያውያን በየጦር አውድማዎች በርካታ ተጋድሎዎችን በማከናወን ዘመን የማይሽረው የታሪክ ድል አስመዝገበው ቢያልፉም በተገቢው ደረጃ አልተመዘገበም። የቆየው ቢቀር የቅርብ ጊዜውን የታሪክ ባለሙያዎች በማጥራት በመዘገብ ለትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያን በጠላትነት ፈርጀው ውድቀቷን የሚመኙላት ዛሬም አልተኙም። በመሆኑም እኛ ቀኝ ያልተገዛን ነን.. ጀግኖችና የማንደፈር ነን.. የሚለውን ለትውልድ በማስተማር የኖረውን ጀግንነት ማስቀጠል ይጠበቃል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በዚህ ዘመን የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጠላቶች እንደቀደመው ዘመን መድፍና ታንክ ይዘው የሚመጡበት ሁኔታ እምብዛም ይኖራል ተብሎ አይገመትም። ይልቁንም በአገሪቱ በውስጥ ጉዳይ በመግባት እርስ በእርስ በማነካከስ ድብቅ አላማቸውን ሊያሳኩ መሞከራቸው አይቀርም። በመሆኑም ዘወትር የአባቶቹን ህብረትና ጀግንነት እያሰበ የሚኖር ትውልድ ለመፍጠር ሊሠራ ይገባል ሲሉ ብርጋዴር ጄነራል ውበቱ አሳስበዋል።

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ ለሰላሳ አምስት አመታት ያህል ያገለገሉት ብርጋዴር ጄነራል ዋሲሁን ንጋቱ የኢትዮጵያን የጦር ሜዳ ውሎዎችና የአሸናፊነት ስነልቦና እንዲህ ይገልጹታል። ከመቶ አመታት በፊት በዛ ለመላው አፍሪካና እስያ ጨለማ በነበረበት ዘመን ኢትዮጵያውያን ከወራሪዎች ለመታደግ ሲዘምቱ የነበራቸው ትልቁ ትጥቅና ስንቅ ኢትዮጵያዊነትንና የሕዝብ ፍቅር ብቻ ነበር። ይህ ስነልቦና በየዘመናቱ ከየአቅጣጫው የተሞከሩ ወረራዎችን በጀግንነት ለመመለስ አስችሏቸዋል። ዛሬ ሲደጋገምብን እንደ ለቀልድ የምንሰማው ቀኝ ያልተገዛንበት ታሪክ ብዙዎች ያልሞከሩትና መቼም የማያገኙት የጀግንነት ውጤት ነው። ዛሬ የምናያትን ኢትዮጵያም አሁን ባለችበት ሁኔታ ማለትም ከባህል ከቋንቋ ከማንነት ወረራ የጸዳ ሕዝብ ያለባትን ልናገኝ የቻልነው በሕዝብ የጀርባ ደጀንነት በየወቅቱ በተነሱ በጀግኖች ኢትዮጵያውያን በተከፈለ መስዋእትነት ነው።

በየትኛውም አገር ውስጥ ለአገሩ ሉአላዊነትና ለሕዝቡ የሚሰዋ ጀግና ወታደር አለ ስንል ከጀርባው ደጀን የሚሆነው የሚወደው ጀግና ሕዝብ እንዳለ ያመለክታል። ለዚህም ነው አገር ለእያንዳንዱ ወታደር ሁለተኛ እናቱ ናት የሚባለው። ኢትዮጵያዊ ወታደር በመንግሥትና በአስተዳደር አኩርፎ አገሩንና ሕዝቡን አሳልፎ የሚሰጥ አይደለም። ለዚህ ማሳያው ወራሪዎች ከኢትዮጵያውያን ባንዳ ለማግኘት ብዙ መቸገራቸው ብቻ ሳይሆን ወራሪዎች በገንዘብና በስልጣን አማለው ሰላይ ብለው ያስቀመጧቸው እነሱኑ ሰልለው ታሪክ ሲሠሩ ማየታችን ነው። ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሞክረው ያልተሳካላቸውም ወታደርም ሕዝቡም ከጀግነነት ባሻገር ለአገር ቅድሚያ ስለሚሰጥ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ለውጭ ወራሪዎች ብቻ ሳይሆን አገር ውስጥ ላሉ አገር አፍራሾችም የማይሳካላቸው በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር ትውልድ የሚፈጥር ሕዝብ በመኖሩ ነው። የተጠነሰሰውን የመቶ አመት የማፈራረስ ቀጠሮ ማፍረሻውና የነበረውን ታሪክ ማደሻው ጊዜ አሁን ነው።

እንደ ማንኛውም አገር በውስጥ ጉዳይ ልዩነት ሊኖር ይችላል። ይህ ልዩነት በቀደሙት ዘመናትም የነበረ ነበር። ነገር ግን አያቶቻችንና አባቶቻችን በአገር ጉዳይ ሲሆን በመካከላቸው የነበረው ልዩነት ሳይገድባቸው ለአንድ አላማ ለዚያውም የነፍስ መስዋእትነት ለሚያስከፍል አብረው በመሰለፍ በመተማመን ይዋደቁ ነበር። ይህ የአንድነት የህብረት ጥንካሬያቸውም ለወራሪዎች የሽንፈትን ጽዋ ሲያጎናጽፍ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ በየሄድንበት አንገታችነን ቀና አድርገን ለመሄድ ያስቻለ ነው። ዛሬም አብዲሳ አጋ፣ በላይ ዘለቀና አሊ በርኪን ለመፍጠር የሚያችል መሠረት ተቀምጦልናል።

ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያዊ የተባለ ሰራዊት እንኳን ለአገሩና ለሕዝብ ይቅርና አገርና ሕዝቡን ለሚወክለው ሰንደቅ አላማው ትልቅ ክብርም ፍቅርም እንዳለው እያየን ነው። ይህ በአንድ ቀን ጀንበር የተከሰተ ሳይሆን በአልነኬ ሕዝብ በትውልድ ቅብብሎሽ በመስዋእትነት የተገኘ አኩሪ ማንነት ነው። ሰራዊቱ በቂ ስልጠና የሚባል ባላገኘበት በኢትዮ ሱማሊያ ጦርነት ወቅት እንኳን የሚነገረውን በመስማትና በጀግንነት በመተግበር ረገድ የሚስተካከለው አልነበረም። ግዳጁን በተገቢው መንገድ ካልተወጣ አገሩን ሕዝቡን አሳልፎ ለጠላት እንደሚሰጥ ለስቃይ እንደሚዳርግ የሚረዳ ከመንግሥትና ከሕዝብ የተጣለበትን አደራ የሚረዳ ነው። ይህ ዘመን የተሻገረ ጀግንነት ዛሬ ላይ የደረሰው ሰራዊቱ ሥነሥርዓት ስለሚያከብር ነበር። እስከ ዛሬ ድረስ በሰላም አስከባሪነት ወታደሮቻችንን ለመላክ ተመራጭ እያደረገን ያለው ከስልጠናው ባሻገር ባለን የውትድርና ሥነ ምግባርም ነው።

በአሁኑ ወቅትም ያለው ሰራዊት የአያቶቹን ታሪክ እንዲደግም እያደረጉ መቅረጽ፤ ለቀጣይም ኢትዮጵያ አገር የማያስደፍሩ ለሕዝብ የሚሞቱ ጀግኖችን ማፍራት ይጠበቃል ያሉት ብርጋዴር ጄነራል ዋሲሁን፤ በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ወደፊትም የሚመጣ መንግሥት በዋናነት ሊሠራ ከሚገባው ጉዳይ መካከል በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ በአገሩ ጉዳይ የማይደራደር ሕዝቡን አሳልፎ የማይሰጥ የጀግኖች አባቶቹ ልጆች የሆነ ትውልድ መፍጠር ላይ ነው። በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን ያላቸውን የአሸናፊነት ታሪክ እየሰነዱ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቃል ሲሉ አደራቸውን አስተላልፈዋል።




# እንኳን ለ127ኛው ዓድዋ ድል

መታሰቢያ በዓል አደረሰን!

# ዓድዋ

የነጻነታችን የማእዘን ድንጋይ!

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብር እንድትጎናጸፍ ካደረጉ ወሳኝ የታሪክ ክስተቶች አንዱ ቅድመ አያቶቻችን በጣልያን ቅኝ ገዢ ወራሪ ኃይሎች ላይ የተጎናጸፉት የዓድዋ ድል ነው፡፡ መላው ኢትዮጵያውያን የነጻነትና የሀገር ሉዓላዊነት ትርጉም የተረዱ ለዚህም የሚያስፈልገውን የሕይወት መሥዋዕትነት የሚከፍሉ መሆኑን ያስመሰከሩበት ታላቅ ድል ነው፡፡ ዓድዋ ነጻነትና ክብር ነው፡፡ ዓድዋ አርማ ነው፡፡ ዓድዋ ተምሳሌት ነው፡፡

ድሉ ዛሬም ድረስ በየትውልዱ ነጻነትን የማስጠበቅ ወኔ የሚያላብስ ሆኗል፡፡ የዓድዋ ድል ከፖለቲካ ነጻነት ባሻገር የኢኮኖሚ ነጻነትን ለማረጋገጥ ለሚደረጉ ጥረቶች ተምሳሌት ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የምሥረታ ታሪክ የሚያሳየን ይህንን ነው፡፡ የባንካችን የምሥረታ ታሪክ የዓድዋ ጀግኖች አሻራ ያለበት ነው፡፡ የባንኩ መሥራቾች የዓድዋ ድል የተገኘበትን ዘመቻ የመሩ፣ መሥዋዕትነትን የከፈሉ ድል አድርገው ለእኛም የድሉን ክብር ያወረሱን አባቶችና እናቶች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሲመሠረት በጦር ሜዳ ድል የተገኘውን ሉዓላዊነት በኢኮኖሚም ለመድገም በጊዜው ተቋቁመው ከነበሩት የውጪ ሀገር ባንኮች ተጽዕኖ ነጻ ለመውጣት በነበራቸው ቁርጠኝነት ነበር፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የነጻነት ባንክ ነው የምንለው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መላው ኢትዮጵያውያንን እንኳን ለ127ኛ የዓድዋ የድል በዓል አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡

የዓድዋ ድል የሉዓላዊነትና የነጻነት አርማ እንደሆነ ሁሉ ዛሬም ለምናደርገው በኢኮኖሚ ራስን መቻል ከሌሎች ተጽእኖ ነጻ ለመውጣት ለሚደረግ ጥረት መስፈንጠሪያ ሊሆን የሚችል ገድላችን ነው፡፡ በመሆኑም ባንካችን ለመላው ኢትዮጵያውያን የተከበረ ሀገር ይዞ ከመገኘት አንጻር ያለብንን ትልቅ አደራ የኢኮኖሚ ነጻነት የተጎናጸፈች፣ ለዜጎቿ ምቹ የሆነች ሀገር አድርጎ ለቀጣይ ትውልድ የማስረከብ ተጋድሎ ላይ እንረባረብ ይላል፡፡

## ክብርና ምስጋና ለዓድዋ ጀግኖች

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

የልማት አጋርዎ!

ESL

# የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ




ETHIOPIAN SHIPPING & LOGISTICS

BEYOND THE SEA

ልዩ ዕትም

# የዓድዋ ድል - የአንድነት ተምሳሌት

ወርቅነሽ ደምሰው

ኢትዮጵያውያን የዛሬ 127 ዓመት በጣሊያን ሠራዊት ላይ የተቀዳጁት የዓድዋ ድል የሁሉም ኢትዮጵያዊ አሻራ ያረፈበት በደማቁ የተጻፈ ታሪክ ነው። በበርካታ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት የተገኘው የዓድዋ ድል ሲወሳ ሁልጊዜም የማይረሳውና ኃያልነቱ ምስክር የማይሻው የአንድነትና ተባብሮ የመሥራት ውጤት መሆኑ ነው። አሁንም ድረስ በኢትዮጵያውያን አንድነትና መተባበር ታላቅ ሀገራዊ ሥራዎች መሥራት ሲታቀድ የዓድዋ ድል በተምሳሌትነት ይጠቀሳል።

በዓድዋ አንጸባራቂ ድል እንዲመዘገብ ያስቻለው የአንድነትና ተባብሮ የመሥራት ስሜት ሁሌም በታላላቅ የልማት እቅዶች፣ በሀገር ሉዓላዊነት ማስከበርና በመሳሰሉት ሀገራዊ አጀንዳዎች መድገም እንደሚያስፈልግ ፓለቲከኞች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የታሪክ አጽንኦት ሰጥተው ሲያስገነዝቡ መስማት ተለምዷል።

በተለይ የታሪክ ምሑራን በዚህ ላይ አጽንዖት ሰጥተው ብዙ ይላሉ። በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ መምህር አቶ ዳንኤል ወርቁ እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል በኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ በአፍሪካ ታሪክ እንዲሁም ደግሞ በመላው ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ላይ እጅግ ወሳኝ የሚባል አሻራ አሳርፏል። ጣሊያኖች የኢትዮጵያውያን ቆራጥነት፣ ሀገር ወዳድነት፣ አንድነትና ታላቅ ትብብር በታየበት የዓድዋ ጦርነት ሊንበረከኩ የቻሉበት ምስጢር አንድነት ነው።

“በወቅቱ ኢትዮጵያም ልክ እንደሌሎቹ የአፍሪካ ሀገሮች በሃይማኖት፣ በዘርና በቋንቋ የተለያዩ ሕዝቦች ያሉባት ሀገር ነበረች” የሚሉት ምሑሩ፣ ኢትዮጵያውያን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ ቢለያዩም ፣ ከነበረው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የተነሳ፣ ለነጻነታቸውና ለሀገራቸው ባላቸው ቀናዒነት ሁሉም በአንድነት ተሰልፈው የሀገርን ሉዓላዊነት ሊዳፈር የመጣውን ጠላት በመመከት ማሸነፍ መቻላቸውን ያመለክታሉ። ያ የጣሊያን ጦር ዘመናዊ በሆነ አደረጃጀት የተዋቀረ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያውያን፣ በመሪዎችና በጦር አመራሮች መካከል የነበረውን አንድነትና በሕዝቦች መካከል የታየውን ጠንካራ የተሳሰረ የአንድነት መንፈስ ፈጽሞ ሊሰብረው እንዳልቻለ ያስረዳሉ።

በዓድዋ ያ ታላቅ ድል የተዘመገበው በኢትዮጵያውያን መካከል ቀደም ሲል ምንም አይነት ልዩነቶች ስለሌሉ የሆነ አይደለም የሚሉት መምህር ዳንኤል፤ ጠላት ሲመጣ ግን ኢትዮጵያውያኑ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው ለሀገራቸው ሉዓላዊነት፣ ለነጻነት ያሳዩት እጅግ በጣም የሚደንቅ አንድነትና ቆራጥነት ለድል እንዳበቃቸው ይናገራሉ። ለድሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከተው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ባለው የኅብረተሰብ ክፍል መካከል የታየው አንድነት፣ የአመራር ብቃት፣ ችሎታና ጠንካራ የሆነ ቁርጠኝነት መሆኑን ይጠቅሳሉ። የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የተጠበቀው ኢትዮጵያውያን ባሳዩት አንድነትና የዓላማ ጽናት ነው ማለት እንደሚቻልም ያብራራሉ።

መምህር ዳንኤል፤ ኢትዮጵያ በፊትም ሆነ አሁን የተለያየ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ እና አመለካከት ያላቸው ዜጎች በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር ናት ሲሉ ጠቅሰው፣ «ልዩነታችን ውበታችን ነው ብለን አምነን ከተቀበልን በልዩነታችን ውስጥ ምንም አይነት ልዩነታችንን ሊያሰፋ የሚችል ነገር ሳይኖር አንድነታችን ጠበቀን ትላላቅ ድሎችን መፈጸም እንችላለን» ይላሉ።

ዓድዋ ላይ የተገኘው ለጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት የሆነው ድል በሁሉም ነገር አንድ ስለሆንን የተገኘ አይደለም የሚሉት መምህር ዳንኤል፤ ሆኖም ግን ልዩነቶችን ወደ አንድነት በማምጣት ተባብሮ መሥራት ለድል እንደሚያበቃ መመልከት ችለናል ይላሉ። ከዓድዋ ድል የምናገኘው ትልቅ ትምህርት አንድነታችንን ብንጠብቅ ልክ እንደ ዓድዋ ሉዓላዊነታችንን የሚዳፈር አንዳች ጠላት በሚመጣበት ጊዜ ሉዓላዊነታችን አስጠብቀን ለትውልድ ማስተላለፍ እንደምንችል ነው ሲሉም ያስገነዝባሉ።

ምሑሩ እንዳሉት፤ በዓድዋ ድል የተመሰከረለትን የኢትዮጵያውያን አንድነት ሁሌም ለሀገር ልማት እድገት መጠቀም ቢቻል ትላላቅ ታሪኮችን ሠርቶ ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል። ኢትዮጵያ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሊሠሩ ያልቻሉን ታሪክ ልትሠራ የቻለችው ዜጎቿ በነበራቸው ጽናትና አንድነት ነው ።

ከጣሊያኖች ስትራቴጂ አንደኛው የኢትዮጵያውያንን አንድነት ሊቦረቡር በሚችል መልኩ የተለያዩ ሀገር ገዢዎችን በጥቅማጥቅም ማማለል አንዱ እንደነበር ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያኑ በሀገር ጉዳይ ምንም አይነት ድርድር አያውቁምና ይህን ስትራቴጂም ማክሸፋቸውን ይናገራሉ።

«ዛሬም አንድነታችን የሚበትን እንዲሁም የሚከፋፍሉ ነገሮች ሊገጥሙን ይችላሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች ከሀገር ሉዓላዊነት እንደማይበልጡ ተረድተን ከሀገራችን ጎን መቆም ይገባናል» ሲሉም ያስገነዝባሉ።

«አንድነታችንንና ተባብሮ መሥራታችንን ብናስከብር ውጤታማ ብቻ መሆን ሳይሆን ታምራትን መሥራት እንችላለን» የሚሉት መምህር ዳንኤል፤ ድህነትን በማሸነፍ ለሌሎች አፍሪካ ሕዝቦች ሊነገሩ የሚችሉ ሌሎች ታሪኮችን ሠርተን ማለፍ እንችላለን ይላሉ። የአሁኑ ትውልድም እንደ ቀደምቱ ትውልድ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ደረጃ የሚጋጥሙትን ተግዳሮቶች በማሸነፍ ድህነትን ታሪክ በማድረግ ለልማትና ለእድገት መሥራት እንዳለበት ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በዓድዋ የታየው አንድነትና ተባብሮ መሥራት በአንዳንድ ታላላቅ የሀገር ሉዓላዊነት የማስጠበቅና የልማት ገድሎች እየተደገመ ነው። ለአብነትም የዓባይ ግድብን መጥቀስ ይቻላል። ግንባታው እየተጠናቀቀ ያለው ታላቅ ግድብ የኢትዮጵያውያን የአንድነታቸውና ተባብሮ የመሥራታቸው ውጤት የታየበት፣ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበት ነው።

የዓድዋ ድል የተወሰኑ ሰዎች ድል ብቻ አይደለም። ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ በመሪዎቹ ብቃትና ብስለት የመጣው ድል ነው። ዓድዋን ልዩ የሚያደርገው በዓድዋ ያልተባበረ የሰው ልጅ ባለመኖሩ ነው። በዓባይ ግድብ ግንባታ ከትንሽ እስከ ትልቅ ድረስ ያልተሳተፈ የኅብረተሰብ ክፍል አለ ማለት አይቻልም። መሪዎች ባሳዩት ቁርጠኝነት ግድቡ ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ግንባታ እስከሚጠናቀቅም ተሳትፎው ይቀጥላል።

ከዚህ በላይም ድህነታችንን ሊያስወግዱ የሚችሉ ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶችን በመሥራት አሻራችንን ማስቀመጥ እንችላለን ያሉት ምሑሩ፣ የዓድዋ ድልና በእሱ ተምሳሌትነት የተከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ ታላላቅ ተግባሮች ትልቅ ሀገር እንደነበርን፣ አሁንም ትልቅ ሀገር እንደሆንን ማሳየት የምንችልባቸው ናቸው ሲሉ ያብራራሉ።

በስፖርቱ፣ በዲፕሎማሲውና በሌሎችም መስኮች ሁላችንም በምንችለው አቅም ድል ማስመዝገብ እንደምንችል የገለጹት መምህር ዳንኤል፤ አንድነታችንን፣ ክህሎታችንን፣ ብቃታችንን ኢንቨስት በማድረግ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሌሎች መስኮች የምንችለውን ሁሉ በማድረግ ለሀገራችን መቆማችንን ማሳየት ከሁላችንም ይጠበቃል ብለዋል።

መምህር ዳንኤል እንደሚሉት፤የዓድዋን ድል ለትውልዱ ለማስተላለፍ ሁልጊዜ ታሪክን መለስ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። ታሪክ መነቃቃትን ይፈጥራል፤ ታሪክ ለመሥራት ታሪክን ማወቅ ይገባል።

ይህም ትውልድ መሪ ትውልድ ሆኖ እንዲያልፍ ማድረግ ይገባል፤ታላቅ ድል ማስመዝገብ የሚችለው ደግሞ ታሪክን በአግባቡ ሰንዶ አነቃቂ በሆነ መልኩ ማቅረብ ሲቻል ነው። ትውልዱ ታሪክ እንዲያውቅ መደረግ አለበት፤ ታሪክ ለመማር የተዘጋጀ ትውልድ መገንባት ያስፈልጋል።

ታሪክ ወጣቱ ትውልድ አዲስ ታሪክ እንዲሠራ የማነቃቃትና የማበረታታት ትልቅ አቅም አለው። ሌሎች አጭር ታሪክ ያላቸው ሀገራት እንኳን ትውልዱን ለማነቃቃት ታሪክን ለመፍጠር ሲጥሩ እናያለን የሚሉት ምሑሩ፣ እኛ እንደሌሎች ሀገራት ታሪክ መፍጠር አይጠበቅብንም። የተሠራ ትልቅ ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን ይላሉ። እነዚህን ታሪኮች በተለያየ መንገድ እያጎላን ብናወጣቸው ታሪክን የሚያውቅና ታሪክን የሚሠራ ትውልድ መፍጠር ይቻላል ብለዋል።

ታሪክ በታሪክነቱ የሚቀር ብቻ ሳይሆን አሁን ላለንበት እንዲሁም ለወደፊቱ ነባራዊ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችልም ይጠቁማሉ። ታሪክ እኔስ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ የሚል ጥያቄ የሚያጭር መሆን መቻል እንዳለበትም ያስገነዝባሉ። አባቶቻችን ታሪክ ሠርተው አልፈዋል፤ እኛም ታሪክ ሠርተን ማለፍ አለብን ብለን እንድንነሳ ያስፈልጋል ያሉት ምሑሩ፣ በአንድም ሆነ በሌላ ታሪክ ሲነገር የምንሰማ ሰዎች ደግሞ እኛም ታሪክ ለመሥራት የተዘጋጀን መሆን አለብን ይላሉ።

«ልዩነታችን ውበታችን ነው ብለን አምነን ከተቀበልን በልዩነታችን ውስጥ ምንም አይነት ልዩነታችንን ሊያሰፋ የሚችል ነገር ሳይኖር አንድነታችን ጠበቀን ትላላቅ ድሎችን መፈጸም እንችላለን»

አባቶቻችን በጣም በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው ታሪክ ሠርተው የዓድዋን ድል አስመዝገበዋል ያሉት ምሑሩ፣ በሚመች ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በጣም በማይመች ሁኔታ ውስጥም ሆነን ለመጪው ትውልድ ሊተርፍ የሚችል ታሪክ መሥራት አለብን ይላሉ። ለእዚህም ሀገራዊ በራስ መተማመን ሊኖረን ይገባልም ነው የሚሉት።

የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ዶክተር መሐመድ ሐሰን በበኩላቸው እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ከላይ እስከ ታች በአንድነት ተነስተው የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የቋንቋ እና የአመለካከት ልዩነት ሳይገድባቸው ከደቡብ እስከ ሰሜን፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ “ሆ” ብለው ወጥተው የጣሊያንን የቅኝ ግዛት ሕልም ያከሸፉበት፣ መመከት ብቻ ሳይሆን አንጸባራቂ ድል ያስመዘገቡበት ነው። የዓድዋ ድል ትልቅና ለአፍሪካ ነጸብራቅ የሆነ ድል ነው።

የዓድዋ ድል በየዓመቱ በኢትዮጵያ ብቻ ይከበራል ያሉት ዶክተር መሐመድ፣ ድሉ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካውያን እንዲሁም የመላው የጥቁር ሕዝቦች ድል መሆኑን ይገልጻሉ። በዓሉም በየዓመቱ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላ አፍሪካም ደረጃ መከበር ነበረበት ሲሉ ይገልጻሉ።

ትውልዱ ከዓድዋ ሊማር የሚገባቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ የሚሉት ዶክተር መሐመድ፤ የኢትዮጵያውያን አንድነት ከዓድዋ በላይ በምንም ሊገለጽ እንደማይችል ነው ያስገነዘቡት። ኢትዮጵያውያን የጣሊያን ጦር ላይ ድል እንዲጎናጸፉ ያደረጋቸው የነበራቸው አንድነት መሆኑን በመጥቀስ፣በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ከየአካባቢያቸው እንደ አንድ ሆነው “ሆ” ብለው በመዝመት ጠላትን ድል ያደረጉበትና አንድነታቸው በሚገባ የተንጸባረቀበት መሆኑን ያመለክታሉ። የዓድዋ ድል አንድነትን ብቻ ሳይሆን አብሮነትንና ጽናትንም በደንብ አድርጎ የሚያንጸባርቅ ነው። የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያንን የነጻነት ናፍቂነት በደንብ አድርጎ የሚያሳይ ታሪካዊ ድል መሆኑን ይገልጻሉ።

ዶክተር መሐመድ ወጣቱ ትውልድ ከዓድዋ መማር የሚገባው የአንድነትን ፋይዳ መሆኑን ያስገነዝባሉ። በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የቋንቋና ሌሎች ልዩነቶች ቢኖሩም፣ የሀገር ጉዳይ ከሁሉም በላይ ነውና ሀገር የሁሉም ምልክትና መገለጫ ናትና በሀገር ጉዳይ ወደኋላ አይባልም ያሉት ዶክተር መሐመድ፣ ወጣቱ ትውልድ በሀገር ጉዳይ በማያወላውል መንገድ በቁርጠኝነት በታማኝነት የዓድዋ ድል መድገፍ እንደሚጠበቅበት አስገንዝበዋል።

እንደ ሀገር እኛ ማሸነፍ ያልቻልነው ትልቁ ጠላታችን ድህነት መሆኑን ነው ሲሉ ጠቅሰው፣ ወጣቱ ትውልድ የዓድዋ ድልን ከመዘከር ባሻገር ድህነትንም ለማሸነፍ በተቀናጀ መልኩ በጋራ በመሥራት በአብሮነት በአንድነት “ሆ” ብሎ በመነሳት መሥራት አለበት ይላሉ። የዓድዋን ድል ለመቀዳጀት በአንድነት እንደተሠራ ሁሉ ኢትዮጵያን ካስቸገራት አስከፊ ድህነት ለማላቀቅ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚታዩትን የእድገት ማነቆዎች በጋራ ለመፍታት በአንድነት መሥራት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ። ወጣቱ ትውልድ በአንድነት የዘመኑ ጠላታችን የሆነውን ድህነት ማሸነፍ እንደሚጠበቅበት አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ማኅበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች አሉባት ያሉት ዶክተር መሐመድ፤ እነዚህን ችግሮች መፍታት የሚቻለው ኅብረተሰቡ ልክ እንደዓድዋ ድል በአንድነት በአንድ ልብ ሆኖ መክሮ በአንድ መቆም ሲችል መሆኑንም ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንዳሉት ኢትዮጵያውያን የዓድዋን ድል በዓልም በየዓመቱ በደማቅ ሥነሥርዓት ያከብሩታል። በዓሉ ከዚህም በላይ መከበር ይኖርበታል። ኢትዮጵያን በሚጠቅም መልኩ በዓሉን ሰፋ አድርጎ ማክበር ያስፈልጋል። ድሉን አጎልቶ በማሳየት በተለይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን በሚያመጣ መልኩ ለማክበር መሥራት ይኖርበታል። ድሉን ለቱሪዝም መስህብም ሆነ ለሌላም ነገር መጠቀም ይገባል። በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚወራለት ሁነት ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም።

ዶክተር መሐመድ የዓድዋ ድል አከባበር ከዚህም በላይ እንዲሻገርም ይፈልጋሉ። የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካውያንም ትልቅ ድል መሆኑን ይጠቅሳሉ። እንደ ሀገር በዓሉ በተለያየ መልኩ መከበሩን አንድ ነገር ሆኖ ከዚህም በሰፋ መልኩ አህጉራዊ ገጽታ እንዲላበስ ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል። ከኢትዮጵያ ገጽታ ከፍ ባለ መልኩ አፍሪካዊ ገጽታ እንዲኖረው ማድረግ፣የተጨቆኑ የአፍሪካ ሕዝቦች ድል ተምሳሌት በሚሆን መልኩ ማክበር እንደሚገባም ያመለክታሉ።

# ዓድዋ እና ኪነ ጥበብ

ዋለልኝ አየለ

በኪነ ጥበብ ውስጥ የአንዲት አገር ምንነት ይታያል።ምክንያቱም ኪነ ጥበብ የገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ ነው። ኃያል የሚባሉ አገራት ገናናነትን ያገኙት በኪነ ጥበብ ነው።ለምሳሌ አሜሪካና ሕንድን የምናደንቃቸው ሁላችንም አሜሪካም ሆነ ሕንድ ሄደን አይደለም። የአገራቸውን ባህልና ታሪክ በመኖር አውቀነው አይደለም፤ በኪነ ጥበብ ሥራዎቻቸው (በተለይም በፊልሞቻቸው) ነው።

ወደ ኢትዮጵያ እንምጣ።በኢትዮጵያ ውስጥ ከአርሶ አደር እስከ ወታደር፣ ከዘፈን እስከ ለቅሶ.... ነገሮች ሁሉ በኪነ ጥበብ ይገለጻሉ።አርሶ አደሩ የሥራ እንቅስቃሴዎቹን ሁሉ የሚገልጸው በኪናዊ ለዛ ነው።ብሶትና ደስታውን የሚገልጸው በጥበባዊ እንጉርጉሮዎች ነው። ለዚህም ነው ኪነ ጥበብ የአንድን ማህበረሰብ ሥነ ልቦናዊ ምንነት ይገልጻል የሚባለው።።

ለዛሬው የምናወራው በጀግንነት ላይ ስለሚያተኩሩ የጥበብ ሥራዎች ነው። ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ የኖረች አገር መሆኗን ዓለም ያውቃል። ከእነዚህ የጀግንነት መገለጫዎቿ አንዱ ደግሞ የዓድዋ ድል ነው። ዓድዋን ምክንያት አድርገን የኢትዮጵያውያንን የጀግንነት ሥነ ልቦና ከኪነ ጥበብ ሥራዎች እናያለን።።

የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ጀግንነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ ከመጡ የሥነ ቃል ትውፊቶች መረዳት እንችላለን።ይህ ከዓድዋ በፊትም ሆነ ከዓድዋ በኋላ የነበረና ያለ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው።።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ግን የምናተኩረው ዓድዋ ላይ ትኩረት አድርገው የተሰነኙ ስንኞች ላይ ነው።ስንኞቹ አንዳንዶቹ ማን እንዳላቸው የማይታወቁ (የሕዝብ) እና በጦርነቱ የተሳተፉ ሰዎች የፎከሩበት፣ በዘመኑ የነበሩ ፀሐፊዎች ሰንደው ያኖሯቸው ናቸው።

የዓድዋን ድል የተመለከቱ በርካታ የኪነ ጥበብ ሥራዎች አሉ።የመድረክ ቴአትሮች አሉ፤ ፊልሞች ውስጥ የዓድዋ ታሪክ ይካተታል።በአብዛኛው ደግሞ የቃል ግጥሞችና የመድብል ግጥሞች ናቸው።ከሁሉም እናያለን። እነዚህ ዓድዋን የተመለከቱ የኪነ ጥበብ ሥራዎች በዓድዋ ጦርነት ወቅትና ከጦርነቱ በኋላ ኩራትን ለመግለጽ የተሰነኙ ናቸው። አንዳንዶቹ በጦርነቱ ወቅት የጦርነቱ ተሳታፊዎች የገጠሟቸው ናቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በዚያው በጦርነቱ ወቅት ሕዝቡ አርበኞችን ለማበረታታትና የደስታ ስሜቱን ለመግለጽ የገጠሟቸው ናቸው። ሌሎች ደግሞ ታዋቂ ድምጻውያን የዓድዋን ድል ለማወደስ የዘፈኗቸው ናቸው። በወቅቱ ከነበሩት እንጀምር።

አንዳንዶቹ በቅኔ የሚነገሩ ናቸው።ለምሳሌ አንዱ ቅኔ እንዲህ የሚል ነበር።።

**እስኪ ስጣሊያኖች መድኃኒት ስጧቸው**
**የሚያስቀምጥ ሳይሆን የሚያስመልሳቸው**

የዚህን ግጥም ትርጉም በወቅቱ ዓውድ እንረዳው።ዘመናዊ ሕክምና ባልነበረበት በዚያ ዘመን ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉት ከቅጠላቅጠልና ሥራሥር የሚዘጋጁት የባህል መድኃኒቶች ናቸው።እነዚህ መድኃኒቶች ህመምን የሚፈውሱት ወደታች (በዓይነ ምድር መልክ ማለት ነው) እና ወደላይ (በማስመለስ) ነው።

የዚህ ግጥም ሰም ጣሊያኖች ታመዋልና መድኃኒት ስጧቸው ነው።መድኃኒቱ ግን በመቀመጥ (በዓይነ ምድር ማለት ነው) መልክ ሳይሆን በማስመለስ (በአፍ) የሚፈውስ መሆን አለበት የሚል ነው።ዋናው ትርጉም ያለው ግን ወርቁ ላይ ነው።።

ጣሊያኖች ታመዋል።ጤነኛ ቢሆኑ ኖሮ እንደ ኢትዮጵያውያን ዓይነት ጀግና ሕዝብ እንወራለን ብለው አያስቡትም ነበር።የእነዚህ ሰዎች መድኃኒት ቅጠላቅጠልና ሥራሥር ሳይሆን፣ ጎራዴና ጥይት ነው።ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀመጡ ሳይሆን በመጡበት እግራቸው ወደ አገራቸው የሚመልስ መሆን አለበት።።

ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ያሻትን በመኪና ያሻትን በፈረስ እየሄደች ነበር።የጣሊያን ወታደሮችም ሰውነታቸው ከኢትዮጵያ ተዋጊዎች ጋር ሲነጻጸር የለሰለሰና ያማረባቸው ናቸው።ዳሩ ግን ምን ዋጋ አለው እንዲህ ሆነ!

**የሞሶሎኒ አሽከሮች ሁሉም ሎጋ ሎጋ**
**ሲመጡ በፈረስ ሲመለሱ በአልጋ**

እንግዲህ በፈረስ ሲንሸራሸር የነበረ ሸበላ የጣሊያን ጦረኛ ፈረሱን መቀማቱ ሳያንስ በእግሩ እንኳን እንዳይሄድ በጥይት አንካሳ አደረጉት ማለት ነው።የሞተው ሞቶ የቆሰለውም በአልጋ እንዲወሰድ ተደረገ ማለት ነው።።

የዓድዋ ድል አስገራሚ ታሪክ የሆነው ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ያላት ጣሊያን «ኋላ ቀር» እያሉ በሚሳለቁባት ኢትዮጵያ መሸነፏ ነው።ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ ወታደር ባህላዊ ጎራዴና ጋሻ በያዘ ወታደር መማረኩ ነው።ጣሊያን በራሱ መሳሪያ መወጋቱ ነው።ራሱ ይዞት በመጣው መሳሪያ ተገደለ።ለዚህም ነው የወቅቱ ከያኒያን እንዲህ ያሉት።

**በሰራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ**
**ተፈፀመ ጣሊያን ሐበሻ እንዳይደርስ**

በዓድዋ ጦርነት ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ጀግኖች ተወድሰዋል።እነዚህን ጀግኖች በማወደስ ለሌሎች ጀግኖች ተጨማሪ ሞራል መስጠት ተችሏል።ከእነዚህም አንዱ ራስ አሉላ አባ ነጋ ናቸው።ራስ አሉላ አባ ነጋ በርካታ የጦር ገድል ነው ያላቸው።በኩፊት፣ በዶጋሊ፣ በጉንደት፣ በጉርዓ፣ በሰሀጢ፣ በመተማ እና በዓድዋ ከወራሪዎች ጋር ተፋልመው አንፀባራቂ ድሎችን ያስመዘገቡ ናቸው።በዚህ ጀግንነታቸው እንዲህ ተብሎላቸዋል።

ጣሊያን ሰሀጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ እንደ ገብስ ቆላው አሉላ አባ ነጋ ይቺኛዋ ስንኝ ዓድዋ በመጣ ቁጥር በየመድረኩና በየመገናኛ ብዙኃኑ ተደጋግማ ትነገር እንጂ ስለአሉላ አባ ነጋ ሌሎች የውዳሴ ግጥሞችም አሉ።

**ዮሐንስ መብቱን ሳሉሳ ቢሰጠው**
**እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው**
**ጣልያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው**
**አጭዶና ከምሮ እንደ ገብስ አሰጣው!**
**አሉላ አባነጋ የደጋ ሳይ ኮሶ**
**በጥሳው ያደክማል እንኳንስ ተኩሶ!**
**አሉላ አባነጋ ካስመራ ቢነሳ**
**ቢችግረው ጣሊያን አለ ፎርሳ ፎርሳ። ።**
**ጣሊያን በሀገርህ አልሰማህም ወሬ?**
**የበዝብዞች አሽከር የነ ሞት አይፈሬ**
**ዘለው ጉብ ይሳሉ እንደ ጎፈር አውሬ!**

ሌላኛው ጀግና ደግሞ ፊት አውራሪ ገበየሁ ናቸው።ፊት አውራሪ ገበየሁ በጦርነት መሃል እየገቡ የሚፎክሩ ነበሩ።በዚህ ጀግንነታቸው ጣሊያንን ሲያርበደብዱ ነበርና እንዲህ ተባለላቸው።።

**የዓድዋ ሥሳሴን ጠላት አረከሰው**
**ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው!**

ፊት አውራሪ ገበየሁ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ ገብተው ሲዋጉ በጣሊያን መድፍ ተገደሉ።ዳሩ ግን ጣሊያን ኢትዮጵያውያንን ማሸነፍ አልቻለም።ቆራጥ ጀግኖች እነ ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ) ኃይለኛ የመድፍ ተኳሽ ሆነው ጣሊያንን አጥረገረጉት።ወዲያውም እንዲህ ተባለ።።

**ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ**
**መድፍ አገሳባጭ ብቻ ለብቻ!**

የዓድዋ በዓል በመጣ ቁጥር የሚታወሱት ሌሎች ግጥሞች ደግሞ ራሳቸው ንጉሡን አጼ ምኒልክን የተመለከቱት ናቸው።ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በብልህነታቸው፣ በጀግንነታቸው፣ በአጠቃላይ በነበራቸው የአመራር ብቃት ኢትዮጵያን ከጣሊያን ወረራ ታድገዋል።እነሆ ብቸኛዋ በቅኝ ያልተገዛች የአፍሪካ ነፃ አገር እየተባለች እንድትጠራ አደረጉ።ሕዝቦቿ በራሳቸው ባህልና ወግ እንዲኮሩ አደረጉ። ለዚህም ነው እንዲህ የተባለው።።

**ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ**
**ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ጊዜ ሐበሻ**

እስኪ አሁን ደግሞ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ ከመጡት እንውጣና ወደ ሌሎች ሥራዎች እንሂድ። እነዚህኞቹ ባለቤት ያላቸው ናቸው።በዓድዋ ታሪክ ውስጣቸው ሀሴት ያደረገ ከያኒያን የሰሯቸው ናቸው።ገጣሚያንና ድምጻውያን ማለት ነው።ከእነዚህም ውስጥ የዓድዋ በዓል በመጣ ቁጥር ሁላችንም የምናውቃት ድምጻዊት እጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) ናት።።

የጂጂ የዓድዋ ዘፈን እያንዳንዱ ስንኝ የምትተነተን ናት።ጥልቅ መልዕክት ያለው ነው።«ምን ማለት ይሆን?» ብለን ስናስብ እያደር እየተገለጠልን የሚሄድና የሚመስጥ መልዕክት ያለው ነው።እስኪ ከስንኞቹ ውስጥ «ሰው ሞቷል ሰው ሊያድን» የሚለውን ቃል እንውሰድ።አንድ ጀግና ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ አልሞትም ብሎ አይደለም።የሚሄደው ወገኑን ለማዳን ነው።ራሱ ሞቶ ሌላውን ማዳን ማለት ነው።

**ሰው ሞቷል ሰው ሊያድን**
**ሰውን ሊያከብር**
**በደህንነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ**
**በክብር ይሄዳል ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ**
**የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነፃነት**
**ሰው ተከፍሎበታል ከደም እና ከአጥንት**
**ዓድዋ ዛሬ ናት ዓድዋ ትናንት**
**መቼ ተነሱና የወዳደቁት።**

«ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት» አዎ! ይህ የዓድዋ ድል የተገኘው በልመና ወይም በግዥ አይደለም።በሰው ሕይወት ነው የተገኘው፤ የብዙዎች አጥንት ተከስክሶበትና ደም ፈሶበት ነው።ይህ የድል ታሪክ ዛሬም ነገም ይወደሳል፤ የጀግኖቻችን ውለታ ነውና! መቼ ተነሱና ነው የምንተወው?

እነዚህ ተወዳጅ አርቲስቶች በዘመን ተሻጋሪ ሥራዎቻቸው ጀግኖቻችን እንዳይረሱ አድርገዋል። ሥራዎቻቸውን ለትውልድ አስተላልፈዋል። ከእነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ድምጻውያን አንዱ ተሾመ አሰግድ ነው። «እንዲያው ዘራፌዋ» በሚለው ዜማው ጀግኖችን እንዲህ ያስታውሳል።

**መቅደላ አፋፉ ላይ ጎበዝ ወንድ ሆነበት**
**በመተማም ጎራ ጀግኖች አንድ ሆኑበት**
**እንዳይሞት ሆነ እንጂ ስሙን እንዳይቀብሩት**
**የመቅደላን መንደር የዶጋሊን ሜዳ**
**የማይጨው ዓድዋን የመተማን ሜዳ**
**ተዳኘበት እንጂ መች ዋኘበት ባንዳ**
**አፄ ቴዎድሮስ አባ ታጠቅ ካሳ**
**እምዬ ምኒልክ ጥራኝ የእኔ አንበሳ**
**በደም ታዋጋለህ በአካል ባትነሳ!**

ተሾመ አሰግድ በዚህ ዜማው ኢትዮጵያ ጥንትም የጀግኖች አገር እንደሆነች ይናገራል።አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ እና የጦር አርበኞችን ያወድሳል። ድል ያደረጉባቸውን ቦታዎች ይጠቅሳል። ጠላት ከእነዚህ ድሎች መማር እንዳለበት ይነግረናል።።

ሌላኛዋ ከያኒ ራሄል ዮሐንስ ናት።«ምኒልክ» በሚለው ዜማዋ እንዲህ ትላለች።።

**ብወጣው በእግሬ እንጦጦን**
**አላገኝም ወይ ጣይቱን**
**ፍቅሩን አብዝቶ ያለ ልክ**
**ዛሬም ይባላል ምኒልክ**
**እስኪ ወደ አንኮበር ተነሱ እንዝለቀው**
**እኛ አናየውም ወይ ምኒልክ ቢለቀው**
**የጣይቱን ማጀት ቢፈልጉት እዛ**
**አይጠፋም እስከ አሁን የጥጃ መዓዛ**

**እስኪ አንተ ሰውዩ እንደ አባትህ ሥራ**
**ከቻዳ እንድትቀዳው ወተቱን በእንስራ**
**ያገኘህ እንደሆን ግቢን ከአዲስ አባ**
**የደግ አደራሽ ነው ሰተት ብለህ ግባ**
**አይቆረቁረውም እንግዳ ደጁን**
**ገብቶ ይጥገብ እንጂ ሥጋና ጠጁን**

**ያ ሁሉ ደስታ ፊቴ ይደቀናል**
**ሰው እንዴት በሄደው ባለፈው ይቀናል**
**ያ የፍቅር ጊዜ ያ የደስታ ቀን**
**ደግሞ በአይኔ መጥቷል እፊቴ ሲደቀን**

ይህ የራሄል ዮሐንስ ዘፈን የአጼ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ዘመን ያሳየናል።ደግነታቸውን ይነግረናል።ይሄን ደግነታቸውን ልናስታውስላቸው እንደሚገባ ይገልጻል።።

«አንኮበር» በሚለው የገነት ማስረሻ ዜማ ውስጥ ደግሞ ይሄን እናገኛለን።።

**እሱማ መቼ ጠፋው ብልሃቱ**
**ከበስተግራው አለች ፀሐይቱ**
**ደግ ሰው ነበር አመለ ምቹ**
**ፍቅር መጋቢ ለወገኖቹ**
**ከእንጦጦ ጋራ ዓድዋ ድረስ**
**ሰራዊት ይዞ በእግር በፈረስ**
**ስንት ቀን ይሆን የፈጀበት**
**ስንት በጋና ስንት ክረምት**

**ቀና ነው ልበ ቀና**
**የወገን ቤት ያቀና**
**አዛኝ ነው አመዛዛኝ**
**ሃቀኛ ብርቱ መዛኝ**
**እምየ አባ ዳኛው**
**በፍቅር የተቃኘው**

**ቋንቋ ሃይማኖት ሳያግደው**
**መሃሉን ከዳር ያገናኘው**
**ሕዝቡን አንድ አርጎ ሄደ ስምሪት**
**በአንድ ባንዲራ በአንድ ነጋሪት**
**እምየ ዳኛው ልበ ተራራው**
**በከዘራ ነው ጦሩን የመራው**

**ምን ቢባል ምን ቢወራ**
**ህያው ነው የሱ ሥራ**
**ያ ቢሄድ ያ ቢመጣ**
**እሱስ ከልቤ አይወጣ**
**የጎራደው ብልጭታ**
**ጠላትን ድባቅ መታ**
**አንኮበር ላይ ደገሰው**
**ዓድዋ ላይ ለኮሰው!**

«እሱማ መቼ ጠፋው ብልሃቱ፤ ከበስተግራው አለች ፀሐይቱ» ይላል የገነት ማስረሻ ዘፈን።ከበስተግራው ማለት እቴጌ ጣይቱ የአጼ ምኒልክ ሚስት መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፤ በልማድ ሚስት ግራ ጎን ተብላ ትጠራለች።ለአጼ ምኒልክ ስኬት ሁሉ የእቴጌ ጣይቱ ብልህነት እንዳለበት ይነገራል።

«ቋንቋ ሃይማኖት ሳያግደው መሃሉን ከዳር ያገናኘው»፤ የዓድዋ ድል የተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጠራርተው በመሄድ ነው።አንድ ልብ፣ አንድ ሀሳብ ሆነው፤ ለአንድ ዓላማ ከአራቱም አቅጣጫ እየተመሙ ሄደው ጠላትን ድባቅ አድርገው መጡ። አንኮበር ላይ የተደገሰው የዓድዋ ጦርነት ዓድዋ ላይ ተለኮሰ፤ ዓድዋ ላይ የተለኮሰው እሳት ጠላትን ለብልቦ መለሰ።።

ሁለት መልዕክት ባለው ሀሳብ እንሰናበት።ዛሬ የዓድዋ ድል በዓል ነው።በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ ዓለም አቀፉ የሴቶች ቀን ይከበራል። ስለሴቶች ሲነሳ ደግሞ እቴጌ ጣይቴን አለማስታወስ አይቻልም። የሴትን ብልህነትና ጀግንነት ያስመሰከሩ ጀግና ናቸዋ!

እቴጌ ጣይቱ ጀግንነትን ከብልህነት ጋር የያዙ ናቸው። በጦርነት ጊዜ ቁጣና ችኩልነት ብቻ እንደማያዋጣ፤ ይልቁንም ብልህነት መኖር እንዳለበት አሳይተዋል። ይህን የእቴጌ ጣይቱን ብልህነትና ጀግንነት የሚገልጸውን የቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ስንኝ መሰናበቻ አድርገነዋል።ክብር ለጀግኖቻችን!

**የቀፎው ንብ ሲቆጣ ስሜቱ**
**ከፊት ሆና መራችው ንግስቲቱ!**

## ልዩ ዕትም

# ዳግማዊ ዓድዋ በልማቱ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



ኢትዮጵያ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ከዓለም ኃያላን አገሮች መካከል አንዷ ነበረች። ኢትዮጵያን የሚያነሱ ድርሳናት ከምሥራቅና ምዕራብ ዓረቢያን አገሮች ጋር ከፍተኛ የባሕር ላይ ንግድ የምታካሄድ ሀገር እንደነበረችም ይመሰክራሉ። ይህ ጊዜ የኢትዮጵያውያን የሥነ ጥበብ ቀደምት ስልጣኔ ማሳያ የሆነበት ነበር። በኢኮኖሚም ቢሆን የተሻለች እንደነበረች የሚያመላክቱ ብዙ ሰነዶች አሉ።

ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት ጃፓንንን ሳይቀር የረዳች ሀገር ነበረች። የመሬት መንቀጥቀጥ ተከስቶ ለደረሰው ጉዳት በኢኮኖሚ ደካማ የነበረችው የዚያን ጊዜይቱ ጃፓን ችግሩን መቋቋም ተስኗት ስለነበር ሀገሮች ለጃፓን ሕዝብ ርዳታ አድርገዋል። ኢትዮጵያም 7ሺህ ፓውንድ ከራሷ በማውጣት አግዛለች(“ጃፓን እንደምን ሰለጠነች “ ገፅ 36)።

ወደ አፍሪካ ሻገር ስንል ደግሞ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲል እንደነበረች ማንም አይክደውም። ዓድዋ ሲታሰብም ይህ ማንነቷ ነው አብሮ ብቅ የሚለው። ወራሪን ድል ነስታ ሌሎች ጥቁር ሕዝቦች እንዲነሳሱና ነጻነታቸውን እንዲያስከብሩ መሪ ሆናለች። በተምሳሌትነቷ አልችልምን ከአዕምሯቸው አውጥተው በእችላለሁ መንፈስ እንዲራመዱ አድርጋለች። በራስ መኩራት እንደሚቻልም አሳይታለች።

በዘመነ ቅኝ ግዛት ወቅት አፍሪካውያን የእኔ የሚሉት ባሕል ፤ወግ ፤ሃይማኖት እና ሀገርም አልነበራቸውም። እሴትና ባሕልም እንዲሁ። ገጽታቸውን ለዘመናት አጥተው ኖረዋል። ማራኪ መልክዓ ምድራቸውንና የተፈጥሮ ሀብታቸውን ጥቅም ላይ ማዋልም አልተፈቀደላቸውም። በዚህም የበይ ተመልካች ብቻ ነበሩ። የሕዝባቸው ሕልውና ሳይረጋገጥ የብጥብጥና ጦርነት እንዲሁም የባርነትና የስደት ተምሳሌት ሆነው እንዲቆዩም ተደርገዋል። ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ በቅኝ ግዛት ሰበብ የተቀራመቷቸው ምዕራባውያን የቻሉትን ያህል መመዝበራቸው ነው። ዜጎቻቸውን ከመግዛትና ከመሸጥ ባለፈ ዕንቁዎቻቸውን እየተሸጡ በምዕራባውያን የተፈበረኩ ገዳይ የጦር መሣሪያዎች እየገዙ እንዲቀጥሉም መገደዳቸው ነው። ይህ ደግሞ አፍሪካውያን ሁል ጊዜም በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲኖሩ እና ከእድገት ይልቅ የቁልቁለት ጉዞን እንዲለምዱት አድርገዋቸዋል።

ቅኝ ግዛትና ቅኝ ገዢዎች አለመግባባቶች፣ ጦርነት ያውም የእርስ በእርስ እንዲኖር ታትረው ሠርተዋል። ወንድም በወንድሙ ላይ እንዲነሳ፣ ሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ሕልም እንዲሆን መርዛቸውን ረጭተዋል። አፍሪካ ገፅታዋ ጥላሸት የተቀባ፣ እሴቷም ሰላም ያጣ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሆኖም ይህ የጨለማ ዘመን በብርሃን የሚለውጠው የዓድዋ ድል አፍሪካውያን እንዲነቁ፤ለነጻነታቸው እንዲዋደቁና በራሳቸው ባሕልና ወግ እንዲኮሩ መሠረት ጥሏል።

እንደሚታወቀው ነጻነት በአንድ መልኩ ብቻ የሚታይና የሚረጋገጥ አይደለም። ብዙ መልክና ልዩ ገጽታ አለው። በማኅበራዊ ሥራ፣ በፖለቲካ ሥራ እንዲሁም በኢኮኖሚው ሥራ ይገለጣል። በእርግጥ አንዱ ከአንዱ ጋር ተነጣጥሎ ላይሄድና ላይታይ ይችላል። ምክንያቱም ፖለቲካው የተሳለጠ ሲሆን፤ ማኅበራዊ ጉዳዮች አብረው ከፍታቸውን ያሳያሉ።

ኢኮኖሚውም ቢሆን እንደዚያው የእድገት ማማ ላይ ይደርሳል። ኢኮኖሚ ሲያድግም እንዲሁ በዚያው ልክ ማኅበራዊና ፖለቲካው የተሻለ አማራጭን ያገኛል። ስለዚህም ሁሉም የየራሳቸው ድርሻና ውጤት እንዲሁም ተያያዥ ነገር አላቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል። እናም እኛ ለዛሬ ዓድዋን ከኢኮኖሚ ነጻነት አንጻር እናነሳዋለን። በተለይም የአፍሪካ ኩራትና ተምሳሌት ከመሆን አኳያ።

ኢትዮጵያ ትናንት በጦር ሜዳው ያውም በጨበጣ ተዋግታ አፍሪካን በዓድዋ ነጻ እንዳወጣችና ለአፍሪካውያን ኩራት እንደሆነች ሁሉ ዛሬም በልማቱ ይህንኑ ለመድገም ደፋ ቀና እያለች ትገኛለች። ለዚህም ማሳያው አፍሪካ በመላው ዓለም ተደማጭ እንድትሆን በርካታ ሥራዎችን እያከናወነች መሆኑ ነው። አንዱ በአየር ንብረት ለውጥ አማካኝነት አፍሪካውያን እየተጎዱ መሆናቸውን በማስታወቅ የአፍሪካ ድምፅ መሆኗ ነው።

ወታደራዊ ጥቃቱን በወታደራዊ መንገድ ትናንት መክታ እንዳሸነፈች ሁሉ ዛሬም በልማቱ ለመድገም እርስ በእርስ የሚተሳሰሩበትን ምሕዳር እያሰፋች ትገኛለች። ለአብነትም የምናነሳው ነጻ የንግድ ቀጠና ትስስሩን ነው። አፍሪካውያን እርስ በእርሳቸው ተረዳድተው ያላቸውን ሀብት ተጠቅመው መለወጥ እንደሚችሉ የሚያሳይ እንደሆነም ታምኖበታል።

የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ቀጣናዊ ትስስር የንግድ ዳይሬክተር እና የምጣኔ ሃብት ባለሙያ ስቴፈን ካሪንጊ በአንድ ወቅት ከጋዜጠኞች ጋር በኢንተርኔት (ዌቢናር) ውይይት ባደረጉበት ወቅት እንዳሉት፤በአፍሪካ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ትስስር የሀገራትን የኢኮኖሚ አማራጮች የሚፈጥር ነው። በተጨማሪም የንግድ ቀጠናው የአፍሪካ ኢኮኖሚ በኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግም የሚያግዝ ነው። በዚህም የንግድ ትስስሩን ማሳደግ ለሥራ ፈጠራ፣ ለውጭ ምንዛሪ፣ ለኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ እድገት የማነቃቂያ ማዕቀፍ ይሆናል።

የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ጨምሮ ሌሎች ስምምነቶችና የትብብር ማዕቀፎችን አፍሪካ ተግባራዊ ብታደርግ በመድኃኒት ማምረት፣ በግብርና በኢንዲስትሪ ልማት ያቀደቻቸው መርሐ ግብሮች ውጤታማ እንዲሆን ያደርግ ነበርም ብለዋል። የአፍሪካ ኢኮኖሚ ይበልጥ ብዝኃነት ኖሮት ቢሆን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የሚደርስበት ጉዳት ዝቅተኛ ይሆን እንደነበረም ነው ሚስ ስቴፈን ያመለከቱት። ይህ ሁኔታ አፍሪካውያን የአየር ንብረት ተጽዕኖና ወደ ፊት የሚገጥሟትን ቀውሶች ለመቋቋም የሚችሉበትን እድል የሚፈጥር እንደሆነም ተናግረዋል።

የአፍሪካ የንግድ ፖሊሲ ማዕከል አስተባባሪ ሚስ ዴቪድ ሉክ በበኩላቸው፤ አፍሪካ የንግድ ሰንሰለት ምንጮቿን ባለማስፋቷ ኮቪድ-19 ብዙ ጉዳት አድርሶባታል። እናም አፍሪካ የንግድ ሰንሰለት ምንጮቿን ማስፋቷ ብዙ ችግሮችን በቀላሉ እንድታከም ያስችላታል። በተለይም ከያዘችው በኢንዱስትሪ የማደግ አጀንዳ ጋር እጅጉን የሚጣጣም ነውና እዚህ ላይ አተኩራ መስራት አለባትም ሲሉ አብራርተዋል።

አገልግሎቶችን ነጻ በማድረግና እርስ በርስ የንግድ ልውውጥ ሂደት የሚታዩ ሌሎች መሰናክሎችን በማስወገድ በተለይም በድንበር ላይ የሚደረገውን አሰልቺ ቁጥጥር በማሳጠር ሀገራቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሆነ የተነገረለት ይህ ነጻ የንግድ ትስስር፤ በኢትዮጵያ እውን የሆነ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉት፤ በይፋ የተጀመረው የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና አካባቢያዊ ትስስር እንደሚፈጥር፤የንግድ ሀሳቦች የሚፈጠሩበት እንዲሁም ለንግድ ክፍት የሆነ ገበያ የሚተገበርበት ነው። የተሳለጡ ግንኙነቶች እንዲኖሩ እና በገበያ መተሳሰሩ ደግሞ ብልጽግና ያመጣል።

አንዴ ከምዕራቡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከምሥራቁ ርዕዮተ ዓለም ጋር ስትላተም በፊውዳልና አምባገነን አገዛዝ ስትወዘወዝ እዚህ ግባ የሚባል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ሳታስመዘግብ የኖረችው አፍሪካ በእነዚህ አይነት መልካም ሥራዎች እድገቷን ወደፊት ታስኬዳለች። ስለዚህም አፍሪካውያንን ከኮሎኒያሊዝምና ከአፓርታይድ የግፍ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ፣ ጉዳያቸውን በጋራ እንዲያዩ፣ የሚወስኑበትና የሚታገሉበት መድረክ እንዲፈጠር እንዲሁም እንዲጠናከርና ለኅብረቱ መደላደል እንዲፈጠር ሁሉም የበኩሉን ማበርከት ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ደግሞ ይህንን በስፋት እያከናወነች መሆኑን ጥቂቶቹን ሥራዎቿን በመጥቀስ እናውሳ።



በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ይህ ነው የሚሉት ሀገራዊ የሰላም፣ የልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ ፖሊሲና እስትራቴጂ አልነበራቸውም። ከገዢዎቻቸው የወረሱት የኒዮ ሊበራሊዝም የፖለቲካ-ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ብቻ ነው ሲያኖራቸው የቆየው። ሕዝቦቻቸውንም ከበይ ተመልካችነት አላዳናቸውም። ፖለቲካዊ ነፃነቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት አላስቻለውምም። ኢትዮጵያ ይህንን የተረዳች ሀገር በመሆኗም የነፃነት ተምሳሌትነት ከእቅድ ጀምራ መተግበር ላይ ተጠምዳለች።

ከንጉሡ ዘመን እንኳን ብንነሳ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረት ከፍተኛውን ሚና ተጫውታለች። ይህ ማለት ደግሞ አፍሪካውያን በጋራ የሚለሙበትን መንገድ ታስቦ የተደረገ ነው። ምክንያቱም ጊዜው ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት የታሪካቸውን ያህል የገዘፈ ስምና ዝና ሳይኖራቸው የቆዩበት ፤የረሃብና ስደት ተምሳሌት የሆኑበት ነበር። በተጨማሪም ተለያይተው መታገልን እንጂ በአንድነት መብታቸውን የሚታገሉበት አልነበረም። እናም በእርሳቸው ተስፋ ሰጪነት ልማት እንዲፋጠን ሆነዋል።

አፍሪካ እንደ ውስብስነቷና መለያየቷ ሁሉ ዕድገቷም አንድ ወጥ ሆኖ አይገኝም። የልማቱ ዕርምጃ ጠንከር ብሎ የሚታየው በጥቂት ሀገሮች፤ ለዚያውም በተወሰኑ ዘርፎች ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ የግል ባለሃብቶችን በመሳቡና ሰፊውን ሕዝብ የዕድገት ተጠቃሚ በማድረጉ በኩል ገና ብዙ ሥራ ስለሚቀር ነው። በሌላ በኩል እስካሁን ቀጥተኛ ዓለምአቀፍ መዋዕለ-ንዋይን መሳብ የተቻለው በጥቂት ሀገራት ብቻ መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ ለዚሁ አንዷ ማሳያ ስትሆን የያዝነውን ዓመት እንደ ምሳሌ ብንወስድ እንኳን ከአፍሪካ በአራተኛ ደረጃ በምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያ ደረጃ በመያዝ የውጭ መዋዕለ ንዋይን መሳብ ችላለች።

በኢትዮጵያ ብዙ የለውጥ ትሩፋቶች እየታዩ ነው። አንዱ በአረንጓዴ አሻራ ዙሪያ የተሠራው ሥራ ሲሆን፤ አፍሪካ ብቻ ሳትሆን ዓለም ጉድ ያለበት እንደነበር ነጋሪ አያሻንም። ይህ ሥራቸው ደግሞ በዓለም ጭምር እውቅናን ያስገኘላቸው እንደነበርም ይታወሳል።

በተመሳሳይ ለውጥ ላይ በሚመክረው 15ኛው የአቡ ዳቢ ዓለም አቀፍ “ሰስቴኔቢሊቲ” ጉባዔ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች እያከናወነች ትገኛለች። የታዳሽ ኃይሎች ባለቤት በመሆኗም ከውሃ፣ ከነፋስ፣ ከፀሐይ እና ከእንፋሎት ኃይል ኃይልን በማመንጨት እምቅ ሃብቷን እየተጠቀመች ነው። በዚህም በፈረንጆቹ 2050 የካርበን ልቀትን ዜሮ ለማድረስ ግብ አስቀምጣለች›› ብለዋል። ለማሳካትም የማይቆፈር ድንጋይ እንዳልነበረ እየተመለከትን ነው።

በእርሻ፤ በኃይል አቅርቦት፤በአረንጓዴ ልማት፤ በቱሪዝም፤ ዓለምን ያስደመሙ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ኢትዮጵያ ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ለም መሬት፤ምቹ የአየር ጸባይ፤ሰፊ የሰው ኃይልና በርካታ እንስሳት ያላት ሀገር ብትሆንም ስንዴ ለማኝ ሆና ዘመናትን ተሻግራለች። አሁን ግን ታሪክ ተቀይሯል። ግብርና ከእራስ አልፎ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል አቅም እንዳለው ተረጋግጧል። በሀገሪቱ ጠቅላላ ለእርሻ የሚውለውን መሬትን ከ33 በመቶ ወደ መቶ በመቶ ከፍ የማድረግ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። ይህም ደግሞ ዝቅተኛና ቆላማ ቦታዎችን ጭምር ለምርት በማዘጋጀት በምርት ከራሷ አልፋ አፍሪካን ብሎም ዓለምን ለማጥለቅለቅ እየሠራች ነው።

ረባዳ መሬቶች ለረጅም ዓመታት ሳይነኩ እና ለእርሻ ሳይሞከሩ የቆዩ ስፍራዎች ናቸው። እነዚህ ስፍራዎች የእንስሳት መኖ እና ስንዴ እንዲመረትባቸው ሆነዋል። በተለይም በአፋር እና በሶማሌ ክልል ላይ የተመረተው ስንዴ ሁሉንም ያስገረመ ነበር። በተመሳሳይ ከታዳሽ ኃይል በተለይም ከውሃ ኃይልን በማመንጨት በተነጻጻሪ ከሌሎች ሀገራት ቀድማ አረንጓዴ ልማትን መተግበር የጀመረችው ኢትዮጵያ ነች። አሁንም ይህንን በማስቀጠል ለሌሎች የነጻነት አውራ መሆኗን ቀጥላለች። ከእርሻ ውጤቶች ስንዴን ከኃይል አማራጮች ደግሞ ከህዳሴ ግድብ የሚገኘውን ኤሌትሪክ ወደ ጎረቤት በመላክ አፍሪካን የማስተሳሰር ጉዞዋን ጀምራለች።

# እቴጌ ጣይቱ እና ጀግኖች እናቶቻችን በዓድዋ ድል የነበራቸው ሚና

**አስመረት ብስራት**

**መስከረም 17/ 1888 ወረ-ኢሉ እንዲከት የተደረገለትን ጥሪ፤**

‹‹እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላትን አጥፍቶ ሀገርን አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደ ፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።

‹‹አሁንም ሀገር የሚያጠፉ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቶአል። እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ፣ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው፤ ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም፤ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለሚሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፤ አልተውህም፤ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ።›› (ጳውሎስ ኞኞ፣ ፻፺፮-፻፺፱)።

ጥሪውን ተቀብሎ የዘመተው ሠራዊት ስፍር ቁጥር አልነበረውም። አብዛኛው ዘማች የእምዬ ምኒልክን ጥሪ ተቀብሎ ጨርቄን፣ ማቄን ሳይል፤ ልጆቹንና ሚስቱን አስከትሎ ተመመ። በዓድዋ ዘመቻም ከሀያ እስከ ሠላሳ ሺህ ሴቶች ዘምተው እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ። በሀገራችን "ጦር ሜዳ" ሲባል የወንዶች መዋያ ብቻ ተደርጎ የሚወሰደውን ነባር አስተሳሰብ ወደ ጎን በመተው፤ ከእያንዳንዱ ድል በስተጀርባ ሴቶች መኖራቸውን ያሳየ ታላቅ ድል ነው - የዓድዋ ድል። እዚህ ጋ "ጀርባ" ሲባል እንደ አባባል ሊወሰድ እንጂ እያወራን ያለነው ሴቶች ከወንዶች ተርታ ስለ መሰለፋቸው መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በአንድ ወቅት በዕውቀቱ ሥዩም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ አስፍሮት የነበረውን ሀሳብ ስንመለከት ሴቶች በአዋላጅነት ከነበራቸው ሚና የማይተናነስ በጦር ሜዳ መጫወታቸውን እንመለከታለን። "ሴቶች በጦርነት ወቅት መዛሪያ ያቀርቡ ነበር፤ ምግብ ያቀርቡ ነበር፤ ሀሳብ ያቀርቡ ነበር፤ ወኔን ያቀርቡ ነበር፤ ደስታን ያቀርቡ ነበር" ይላል።

ሴት ጥበበኛ ናት ቢባልም ከጥበበኞችም ጥበበኛ የሆነች፤ ከዘመኗ ቀድማ የበራች የአልማዝ ፈርጥ፤ ንግስት ጣይቱን ያህል ጥበበኛ ስለመኖሩ ግን መጠየቅን ግድ ይላል። እቴጌዋ ለዓድዋ ድል አንፀባራቂ ሚና ተጫውተዋል። እቴጌይቱ ወደ ዓድዋ የዘመቱት አምስት ሺህ እግረኛና ስድስት መቶ ፈረሰኛ ጦራቸውን አስከትለው ነበር። የእቴጌ ጣይቱ የዓድዋ ገድል የሚጀምረው ለዓድዋ ጦርነት መነሻ ከሆነው ከውጫሌ ስምምነት ነው፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው፤ ኮንት አንቶኔሊ የውጫሌ ውል እርሱ እንደፈለገው እንደማይሆን እና 17ኛዋ አንቀፅ እንደተሰረዘ በሰማ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ እና አጤ ምኒልክ በተቀመጡበት እልፍኝ ገብቶ 'የአንቀፁ 17ተኛው ክፍል ተሰርዟል ተብሎ ለምን ተፃፈ?" በማለት አጤ ምኒልክን ይጠይቃል። አጤ ምኒልክም "ሁለታችን፣ አንተና እኔ ተነጋግረን፣ አንተ ወደህና ፈቅደህ የተፃፈ ቃል ነው። ሌላ አልታከለበትም፤ ባስተርጓሚህ የተናገርከው ነው" አሉት።

ከዛ ኮንት አንቶኔሊ እንዳልተሳካለት አውቆ የውሉን ወረቀት በጫጨቀውና ጦርነቱ እንደማይቀር ተናግሮ ከእልፍኝ እየወጣ እያለ "እቴጌ ጣይቱ ከት ብለው በመሳቅ የዛሬ ሳምንት አድርገው። በዚህ የሚደነግጥ የለም። ሂድ፣ የፎከርከበትን አድርግ። እኛም የመጣውን እናነሳዋለን። እግሩን ለጠጠር፤ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ ሀገሩን የማያድን ሰው ከዚህ የሌለ አይምሰልህ። የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ ሀገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጂ ሞት አይደለም። አሁንም ሂድ፣ አይምሽብህ። የፎከርከበትን በፈቀደህ ጊዜ አድርገው። እኛም ከዚሁ እንቆይሃለን። ያንተ ፍላጐት ኢትዮጵያ በሌላ መንግሥት ፊት የኢጣሊያ ጥገኛ መሆኗን ለማሳወቅ ነው። ነገር ግን ይህን የመሰለው የምኞች ሃሳብ አይሞከርም!! እኔ ራሴ ሴት ነኝ። ጦርነት አልፈልግም። ነገር ግን ይህን ውል ብሎ ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ።" በማለት ፈጽሞ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እንደማይደራደሩ መናገራቸውን ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" በሚለው መጽሐፉ ላይ አስፍሮት ይገኛል።

ከእያንዳንዷ የእቴጌ ቃል በስተጀርባ ቆራጥነትን ያዘለ መልክ ይታያል። ጀግንነት ይንፀባረቃል። 'ከሀገር በላይ ምንም ነገር የለም' የሚል መልዕክት በግልፅ ይነበባል። ታዲያ ይህን የቆራጥነት፣ የጀግንነት ወኔ፣ የመሪነትና አዋጊነት ጥበብና ብቃት ወዘተ ወደ እኔ፤ ወደ አሁን ዘመኗ እንስት ቢጋባብኝ



**ሴት ጥበበኛ ናት ቢባልም ከጥበበኞችም ጥበበኛ የሆነች፤ ከዘመኗ ቀድማ የበራች የአልማዝ ፈርጥ፤ ንግስት ጣይቱን ያህል ጥበበኛ ስለመኖሩ ግን መጠየቅን ግድ ይላል። እቴጌዋ ለዓድዋ ድል አንፀባራቂ ሚና ተጫውተዋል**

ብሎ የማይመኝ ማን አለ? ማንም። የእልፍኟ ንግሥት፣ ማጀቷ በባለሙያ እጇቿ በተቃኙ ቁሶች የሞሉላት፤ በአደባባይ ከነገሥታት በላይ የንግሥተ ነገሥት ብርታትና ጥንካሬ የሚታይባት፤ የሴቶች ሁሉ ቁንጮ እቴጌ ጣይቱን ያህል ሴት ዛሬ ብትወለድ ብሎ የማይመኝስ ማን አለ? ማንም።

ከማጀት እስከ አደባባይ የደመቁቱ እቴጌ ጣይቱ (ብርሃን ዘኢትዮጵያ) ሴቶችን በማስተባበር ትልቅ ሥራም ሠርተዋል፡፡ እቴጌ ጣይቱ በዓድዋ ዘመቻ ወቅትም የራሳቸውን ጦር እየመሩ ዘምተዋል፤ ተዋግተው አዋግተዋል፡፡ ከጦርነቱ አስቀድሞ ሀገራችን ከ1880 እስከ 1884 ዓ.ም በነበሩት አምስት ዓመታት የከብት በሽታ ገብቶ ከብቶችና ሌሎች እንስሳት በማለቃቸው ምክንያት ገበሬው አርሶ ለማምረት ባለመቻሉ ሀገራችን ከፍተኛ የረሃብ ችግር ውስጥ መሆኗን ጣሊያን የኢትዮጵያ ሠራዊት በረሀብ ምክንያት እንደሚበተን ትልቅ ተስፋን አንግቦ እንደነበርም ጳውሎስ ኞኞ ከላይ በገለጽነው ሥራው ውስጥ ለንባብ አብቅቷል፡፡

ጥበበኛይቱ ጣይቱ ቀድመው በጠጅ ቤት፤ እንጀራ ቤት፤ ጠላ ቤትና ገንቦኛ በማድረግ ከፋፍለው የመጀመሪያው ስንቅ የማቀበሉ ስራ በአግባቡ እንዲከናወን ሴቶችን አሰናድተው ሠራዊቱ በረሃብ ምክንያት እንዳይበተን ማድረግ መቻላቸው ከዋናው የጀግንነት ግርማ ሞገሳቸው አንዱ ሆኖ በደማቅ ቀለም ተፅፎላቸዋል፡፡

ጦርነቱ በተለያዩ አቅጣጫዎች ይደረግ ስለነበር፤ በአንዱ አቅጣጫ የዘመተው ዘማች ድል አድርጐ እና ምርኮ ይዞ በመመለስ ሲፎክርና ሲሸልል ‹‹ድሉ ገና ንጉሡ ሣይመለሱ እዚህ ሆኖ መፎከሩ ምንድነው?›› በማለት እየተቆጡ ሲያበረታቱ እና ሌሎቹን ዓውደውጊያዎች እንዲያግዙ ሲያደርጉ ነበር፡፡

ከሁሉ ደግሞ የሚደንቀው ጣሊያኖች በመቀሌው ምሽግ በተሸሸጉ ጊዜም፤ ይህን ሁኔታ በልዩ ትኩረት ይከታተሉት የነበሩት እቴጌ ጣይቱ የጣሊያኖችን የውኃ ምንጭ በራሳቸው ጦር በማስከበብ እና ምንጩን በማሳገድ ውሃ ሲጠማቸው ሽንፈታቸውን እንዲጎነጩ አድርገዋል፡፡ ጦር ሳይሰበቅ በውሃ ጥም ብቻ እስከ አፍንጫው የታጠቀን ሠራዊት ትጥቅ የማስፈታትን ጥበብ ያህል ከወዴት ይገኛል?

ይህ መቀሌ የሚገኘው ምንጭም እስከ ዛሬ ድረስ ውሃ የሚያፈልቅ በመሆኑ ለንግሥቲቱ መታሰቢያነት ይሆን ዘንድ የአካባቢው ሰዎች ‹‹ማይ እንሽቲ›› በማለት ሰይመውታል፤ ትርጓሜውም "የሴት ውሃ" ማለት ነው፡፡

እቴጌ ጣይቱ በዓድዋው ድል የማይተካ ሚና ይኑራቸው እንጂ፤ በጦርነቱ ወቅት በሥራቸው ያስተባበሯቸው የነበሩ ወደ 3ሺህ የሚሆኑ ሴቶችም በጦርነቱ ጉዞ ላይም ሆነ በጦርነት ጊዜ በየቀኑ ሰባትም ስምንትም ምጣድ እየጣዱ እንጀራ ይጋግራሉ፤ ጠላና ጠጅ ይጠምቃሉ፤ ወጥ ይሠራሉ፤ ግብር ያበላሉ፤ ቁስለኛ ያክማሉ፤ ውሃ ያጠጣሉ፤ በፉከራና በእልልታ ተዋጊውን ሠራዊት ያበረታቱም ነበር፡፡





በዓድዋው ጦርነት የኢትዮጵያ ሴቶች በአዋጊነት ተሳትፈዋል። ምግብ ከማብሰልም አልፈው ጥይት ከሚያፏጭበት ውጊያ መካከል እየተሽሎኮሎኩ ጥይት አቀብለዋል። የቆሰለን አክመዋል። ጦር መርተው መድፍ አስተኩሰው . . .፤ ቀን በውጊያ፣ ማታ ከስንቅ ዝግጅት ሳይነጠሉ ረጅሙን የውጊያ ወራት ከሠራዊቱ ሳይለዩ፣ ከጎኑ ሳይርቁ አሳልፈዋል።

የታሪክ መዛግብት እንደሚያትቱት የዓድዋ ጦርነት ጾታ አልለየም። በዓድዋው ጦርነት ከየግዛቱ የተሰበሰቡ ሴቶች ከንጉሡ ነገሥቱ እስከ ታችኛው ድረስ ያሉት የፋሺስትን ጦር መውጫ መግቢያ በማሳጣት ተዋግተዋል፤ ማታም ስንቅ በማዘጋጀት የሁለትዮሽ አስተዋጽዖ ነበራቸው።

ከጦርነት በፊትም ሴቶቹ ከእቴጌዪቱ ጋር ወደ ዘመቻው የሚጓጓዝ ሸክላ፣ ምጣድ፣ አክንባሎ፣ ድስት፣ ቋንጣውን፣ በሶውን፣ ደረቅ ምግቦቹን በብዛት በማዘጋጀት፣ በጦርነቱም ሜዳ ባደሩባቸው ድንኳኖችም ሴቶች በዝግጅታቸው ከስንቅና የዕለት ምግብ በተጓዳኝ ለወጥ ቅቤው፣ ለበርበሬው፣ ለቅመሙ፣ ለዕለት ምግብ ማዘጋጃ ድልሁን፣ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ለግብር የሚሆነውን በሙሉ እያዘጋጁ፣ ድፍድፉን ለጠላ፣ ለጠጅ የሚሆነውን ማር በማዘጋጀት ድርብ ተግባር ነበራቸው። በትጋትም ተወጥተውታል።

ማታ እንጀራ ሲጋግሩ አድረው የጋገሩትን እንጀራ ያስጭናሉ። ከመኳንንቱም ጋር ለድርጎኛውም ለሠራዊቱም የዘማቹ ስንቅ የሚሆነውን ምግብ ሠርተው ግብር ያዘጋጃሉ። ጠላ ቤቶችም በእንስራ ጠላቸውንና ጠጃቸውን ያቀርባሉ። እቴጌና ዘውዲቱም ለተጠማውና ለቆሰለው ውሃ ያጠጡ (በእቴጌዪቱ የሚመራ፣ ወደ አምስት ሺህ ገደማ የሚሆን ሠራዊት ነበራቸውና) ጦሩንም እያበረታቱ ነበር። በዓድዋው ጦርነት ሴቶች "ምንም ሴት ብሆን በዛሬ ቀን በድንኳን ውስጥ ተቀምጬ አልውልም" ብለው፤ በሰልፉ መካከል ሆነው ጦሩን "አይዞህ በርታ" ይሉ ነበር። በዓድዋ ጦርነት ላይ የሴቶች ሚና በጥበብ ዘርፉም የጎላ ነው። በኪነ ጥበቡ ዘርፍም በሰፊው ተሳትፈው የነበረ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል የአዝማሪ ጣዲቄ ሥራዎች ይጠቀሳሉ። የዓድዋ ድል የሕጻን፣ የአዋቂው፣ የሴቱም፣ የወንዱም የመላው ኢትዮጵያዊ ድል ነው።

የምናለ አዱን "Women and Warfare in Ethiopia" ጥናት ዋቢ በማድረግ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የሴቶችን ሚና እንዲህ አስቀምጦታል። ጣይቱ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶችን እያንቀሳቀሱ፣ ለቆሰሉት ሕክምና እንዲሰጡ፣ ከ10 እስከ 12ሺህ የሚሆኑ ሴቶች ውሀ የተሞላ ኮዳ አስይዘው ወደ ተጠማው ተዋጊ በማሠማራት ለሠራዊቱ ውሃ እንዲቀዱ አድርገዋል።

የአዲግራት ሴቶች የጣሊያንን ቴሌግራፍ መስመር በጣጥሰው በመጣል ከስራ ውጪ አድርገዋል። ኢንጅነሮቻቸው ሲጠግኑ ፣ ሴቶች መልሰው ይበጣጥሱት ነበር። በዚህ ግዳጅ ላይ ሁለቱ እጅ ከፍንጅ ሲያዙ፤አንድ ሴት ጠብ-መንጃ ይዛ እንደተኮሰችባቸው በግርምት ተሞልተው ገልጸዋል። በሦሥት ሺህ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ የእናቶች-እህቶች ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ . . . ብቃት ለበርካታ ሀገራት ያልተለመደ ክስተት ነው።

ጊዜው ሆነና ከላይ ስለ ዓድዋ፣ የሴቶች ሚናና የተገኘው ድል አወራን እንጂ፣ ዛሬም ኢትዮጵያ እንደ ዓድዋው ዘመን ሁሉ፣ ጀግና ሴቶችን የምትሻበት አስቻጋሪ ጊዜ ላይ ትገኛለች። በርካታ ጣይቱዎችን (በነገራችን ላይ፣ እቴጌ ጣይቱ ቢቢሲ "የሚሊኒየሙ ምርጥ ሰብዕናዎች" ካላቸው የዓለም ምርጦች መካከል በቀዳሚነት የተጠቀሱ ስለመሆናቸው ያውቃሉ? በአፍሪካ ኅብረትስ ስለመመረጣቸው) እጅጉን ትሻለች። ኢትዮጵያ እንደ ዓድዋዎቹ፣ ቆራጥ ማንነትን እንደያዙት የእዚያኛው ትውልድ ሴቶች፣ በአገር ሉዓላዊነት ላይ የማይደራደሩ ሴቶችን፣ የጦር ሜዳ ባለሚሎችን . . . ለኢትዮጵያ ሰላምና ደጀንነት፣ ለሕዝቧ መብትና ብልጽግና የሚታገሉ ጀግኒቶችን በእጅጉ ትፈልጋለች። እኛም ይህ ይሆን ዘንድ፣ ጀግኒቶቹ ከያሉበት ይወጡ፣ ሌሎችም ይፈጠሩ ዘንድ ተመኘን።

"ቆማ ከነገረችው እናቱ፣ ተኝታ የነገረችው ሚስቱ" ነውና ነገሩ ጥፋት ከጉያችን ከጓዳችን እየወጣ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። እናት ያልወለደችው አጥፊ ጎዳና ላይ አናይም። እናትም ልጇቿን በወግ በሥርዓት ሀገር ወዳድነትን አስተምራ፤ ጥላቻን ከውስጡ ነቅላ ማሳደግ ይኖርባታል። ሚስቲትም አዋቂ፣ ጥበበኛ በመሆን ለሀገር ሰላም የበኩሏን አስተዋፅዖ ልታደርግ ይገባል።

ሲብስ ደግሞ ከማጀት እስከ አደባባይ መቆም የማያቅታት ጀግኒት የሰላም ጦሩን መርታ ዳግም የዓድዋን ድል በመሥራት ለሀገር አንድነት የምትታትር፤ ቋሚ ምስክር ልትሆን ይገባታል እንላለን፤ የከርሞ ሰው ይበለን።

**ዘላለማዊ ክብር ለዓድዋ አርበኞቻችን!!!**

## ልዩ ዕትም

# «እኔ ከዓድዋ ድል የተማርኩት...»

**ዳግም ከበደ**

በመዝገባችን ላይ ደጋግመን ብንከትባቸው ልንማርባቸው እንጂ ሊሰለቹን የማይችሉ በርካታ ክስተቶች አሉ። በየአመቱ ብናሞግሳቸው ቢያንስባቸው እንጂ የማይበዛባቸው ታላላቅ የአገር ታሪኮች ሞልተውናል። ከእነዚህ አንፀባራቂ ታሪኮች መካከል ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከዳር ተመው በወራሪው የጣሊያን ሰራዊት ላይ የተጎናጸፉት የዓድዋ ድል በቀዳሚነት ይጠቀሳል።

ይህ ታላቅ ድል የተመዘገበው ልክ የዛሬ 127 አመት በዛሬው ዕለት የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ነው።በዚያ ታላቅ ጦርነት ጣሊያን በኢትዮጵያ ከፉኛ ተደቁሳ ሽንፈት ደረሰባት። አፍሪካ በአጠቃላይ በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ በወደቀችበት በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞቿ ተጋድሎ ነፃነቷን እና ሉዓላዊነቷን ያስጠበቀችበት ልዩ ታሪክ ተመዘገበ። የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያንን በአንድነት አሰባስቦ ለታላቅ ድል ማብቃቱ በአውሮፓውያን የታሪክ ተመራማሪዎች እና አገር አሳሾች ጭምር በተለያየ ጊዜያት ተመሰክሮለታል።

ይህ ድል ለመላ የአፍሪካ ሕዝቦች ጭምር የተረፉ ሁለት ውጤቶችን አስከተሏል፤ አንደኛ ሰሜን አፍሪካ ላይ አውሮፓዊ ክብርን ትልቅ ውርደት አከናነበው። ሁለተኛ በአውሮፓ ፖለቲካ ማንነት ረገድ የጣሊያን ዋጋ ቁልቁል ወረደ።

ጥቁር ከሰው በታች ነው የሚል አስተሳሰብ በነገሰበት በዚያ ዘመን፤ ጥቁር የማይታሰበውን ማድረግ እንደሚችል ያሳየበት የዓድዋ ድል የዓለምን ታሪክ በሚደንቅ ሁኔታ ቀይሮታል። ኢትዮጵያውያን እንደ ሌሎች በቅኝ ግዛት ስር የተላቀቁበትን ቀን «ነፃ የወጣንበት» ብለው እንደሚያከብሩት ሳይሆን በኩራት የድል ቀናችን እያሉ በልዩ ሁኔታ የሚያከብሩት ታላቅ ቀን ነው።


የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተመው በንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ አመራር ስር በአንድ ጥላ ተሰባስበው ባደረጉት ተጋድሎ የተመዘገበ ታሪካዊ ክስተት ነው።

ዛሬ እየተከበረ ካለው ከ127ኛው የዓድዋ ድል ብዙ እንማራለን። ለመሆኑ ታዋቂና ተፅእኖ ፈጣሪ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ድል ምን ትምህርት ወሰዱ? አምስት ሰዓት ከፈጀው የድል ጦርነት ታሪክ ውስጥ የትኛው ንዑስ ታሪክ በይበልጥ ይስባቸዋል? ይህ ትውልድስ እነርሱ ካገኙት የሕይወት ተሞክሮ ምን ሊማር ይችላል? የዝግጅት ክፍላችን ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ በድል ሲከበር የኖረውን «የዓድዋ ድል» ከመዘከር ባለፈ በአነሳናቸው ጥያቄዎች ላይ ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች የሰጡንን አስተያየት አሰናድቶ የሚከተለውን ጽሑፍ አዘጋጅቶላችኋል።

ገጣሚ ጸሐፊ ተውኔትና ባለቅኔ አያልነህ ሙላቱ እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል ዘመናዊና የሰለጠነ ጦር በጦርና በጋሻ ድል የተደረገበት ነው። ከዚያም ባለፈ የኢትዮጵያ አንድነት መሠረት የተጣለበት መሆኑን ገጣሚ ጸሐፊ ተውኔትና ባለቅኔው ያምናሉ። ይህ ጥቁር ማንነቱን ያስመሰከረበት ድል እንደ አንድ ዜጋ ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ደራሲ ትርጉም እንዳለውም ነው ያመለከቱት።

ጋሽ አያልነህ ሙላቱ የዓድዋ ድል ሲነሳ ሁሌም ካነበቡትና ከሰሙት ታሪክ በልዩነት ሁለት ነገሮችን ያስታውሳሉ። የመጀመሪያው ኢትዮጵያን ለመውረር ከተላኩ የጣሊያን ወታደሮች መካከል የአንደኛው ሚስት ከጣሊያን ጦርነቱን አስመልክቶ ለምኒልክ የፃፈችው ደብዳቤ ነው። የዚህ ደብዳቤ ይዘትም «እኔ የልጆች እናት ነኝ። ሠርቼ ልጆቼን የማስተዳድርበት ንብረትም ሆነ ሀብት የለኝም። ባለቤቴ በጦርነት ውስጥ ነው። ስለዚህ ምንም ሳይሆን ወደ አገሩ በሰላም እንዲመጣ እፀልያለሁ» የሚል ነበር። በዚህ ወቅት ምኒልክ ደብዳቤውን አግኝተው ኖሮ ከተማረኩ የጣሊያን ወታደሮች መካከል አስፈልገው በአጋጣሚ ያገኙታል። በባለቤቱ መልዕክት አዝነው ኖሮ አስቀድመው ወደ አገሩ በመላክ ከቤተሰቡ ጋር እንዲቀላቀል ፈቅደዋል። ይህ ታሪክ ለጸሐፊ ተውኔት ጋሽ አያልነህ ትልቅ ቦታ አለው።

በሁለተኛነትና በዋናነት ከዓድዋ ድል ጦርነት እርሳቸውን የሚያስደንቃቸው ታሪክ እቴጌ ጣይቱ በመቀሌ ከተማ አርበኞችን ጣሊያን ለመጠጥነት ይጠቀምበት የነበረውን «የማይ ንሽተይ» ምንጭ አስገድበው ጣሊያኖች በውሃ ጥም ምክንያት እጃቸውን ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ ማስገደዳቸውና የጦርነቱን የመጀመሪያ የድል ምዕራፍ ማብሰራቸው ነው። ያንን ተከትሎ የጣሊያን ሰራዊት ምርኮኞችን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ምህረትን አግኝተው በበቅሎ፣ ግመልና ፈረስ ሸኝተዋቸዋል። በዚህ ታሪክ ውስጥ ጸሐፊ ተውኔትና ባለቅኔ አያልነህ የእቴጌ ጣይቱን የውጊያ ጥበብ የምኒልክን ስልጡን ምርኮኛ አያያዝና ምህረት መረዳታቸውን ይናገራሉ።


ገጣሚ ጸሐፊ ተውኔትና ባለቅኔ አያልነህ ሙላቱ

«ኢትዮጵያን ለማሰልጠን ነው የምንመጣው ያለው የጣሊያን ምርኮ ምህረት አድርጌልሃለሁ ወደቤት ሂድ። አሊያም ከወገኔ ጋር ተመልሼ መጥቼ እወጋሃለሁ ካልክ ደግሞ መምጣት ትችላለህ እገጥምሃለሁ ያሉት ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው» የሚሉት ባለቅኔው አያልነህ፤ ጀግንነታቸውና በጊዜው ለምርኮኛ ምህረት የማድረግ የአስተሳሰብ ስልጣኔያቸው አስደናቂና በታሪክ ሲወሳ የኖረ መሆኑን ይገልፃሉ። ከሁሉም በላይ ግን ሰልጥነናል ያሉትን የዘመኑን ምዕራባውያን ያሳፈረና ግዙፍ ዲፕሎማሲያዊ ድል ያቀዳጀ መሆኑን ያነሳሉ።


ጸሐፊ ተውኔት ጋሽ አያልነህ፣ በዓድዋ ድል ታሪክ ኢትዮጵያ ታላቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል መቀዳጀቷን ጠቅሰው፣ ጣሊያን ግን ዳግም ኢትዮጵያን ከ40 ዓመት በኋላ በበቀል ሲወርር ከዚያ ተፃራሪ በሆነ መልኩ ግፍ መፈፀሙን ይናገራሉ። በአዲስ አበባ የካቲት 12 «ግራዚያኒ ላይ የግድያ ሙከራ ተደርጓል» በሚል 30 ሺህ ኢትዮጵያውያንን በነጋታውም 1 ሺህ 400 የሚደርሱ ተጨማሪ ዜጎችን በግፍ እንደጨፈጨፈ ይጠቅሳሉ።

ከ40 ዓመት በፊት ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለመዳፈር የመጡ የጣሊያን ወታደሮችን በክብርና በምህረት ሲለቁ፤ ጣሊያን ግን ከ40 ዓመት በኋላ ግራዚያኒ ቆሰለ በሚል ምንም የማያውቁ ዜጎችን በግፍ መጨፍጨፉን ያመለክታሉ። የኢትዮጵያውያን የሞራል ልዕልና ለባለቅኔ አያልነህ ሙላቱ ትምህርት የሰጠ ነው።

ይህ ትውልድም እርሳቸው ከታሪክ እንደተማሩትና ኢትዮጵያውያን ለግፍ የማይበገሩ፣ ምህረት ማድረግ የሚያውቁና ስልጡንነት የተሠሩበት ማንነት እንደሆነ መገንዘብ እንዳለበት አስገንዝበዋል። ስልጡንነትም ልክ እንደ እቴጌ ጣይቱና ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ምኒልክ ከአገር በቀል እውቀት ጋር የተዋሃደ ሊሆን እንደሚገባ ትውልዱ ልብ ሊልና ሊገነዘብ ይገባል በማለት ሃሳባቸውን ይቋጫሉ።

ሌላው የዝክረ ዓድዋ ድልን በማስመልከት የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው ተፅእኖ ፈጣሪ አንጋፋው ሰዓሊ ልዑልሰገድ ረታ ናቸው። ሰአሊ ልዑልሰገድ ከዚህ ታላቅ የክፍለ ዘመናችን ድል እና ከተከሰቱ ታሪኮች ውስጥ በርካታ ጉዳዮችን አንስቶ መማር ይቻላል ይላሉ።

«ዓድዋ ሲነሳ እምዬ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ እንዲሁም ሃይማኖትና በጦርነቱ ወቅት ይዘዋቸው የዘመቱት ታቦታት በምንም መልኩ የሚረሱ አይደለም» የሚሉት አንጋፋው ሰዓሊ ልዑልሰገድ፤ ይህንን በልዩ ልዩ መልኩ ማየትና ከዚያም መማር እንደሚቻልም ይናገራሉ።


ሰዓሊ ልዑልሰገድ ረታ

በምሳሌ ሲያነሱም በወቅቱ ለማሸነፍ «እግዚአብሔር ይርዳን» ብሎ ታቦት ይዞ መውጣቱ ግዙፍ አስተማሪ ታሪክ እንደሆነ ይናገራሉ። የሰው ልጅ እምነትና እውነት ሲኖረው ለድል መብቃት እንደሚችል አንድ ማሳያ መሆኑን ይናገራሉ።

«የኢትዮጵያ ሕዝብ የዓድዋን ድል የተቀዳጀው በንፅህናና በግፍ ነው። ይህንን ማንም ሰው ሊረዳ ይገባል» የሚሉት አንጋፋው ሰዓሊ፤ ዓለም በጦር መሣሪያ ብዛት፣ በቅጥፈት ሳይሆን እውነትንና እምነትን የያዘ ግለሰብም ቢሆን በየትኛውም ግንባር ድል ከእርሱ ጋር መሆኗን መገንዘብና መማር ይገባዋል ይላሉ። እርሳቸው ከዓድዋ ድል ይህን መገንዘብ እንደቻሉና ትውልዱም ብዙ መማር እንደሚችል ይመክራሉ። ትውልዱ በማንኛውም መስክ ላይ እምነት ካለው፣ ዓላማ ካለው ግቡን የሚመታው በዚህ መሠረት መሆኑን ያስረዳሉ።

ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በጊዜው ለነበሩት ለአፍሪካውያን ጭምር ትልቅ ድል ነበር የሚሉት አንጋፋው ሰዓሊ፣ አሁንም የጥቁሮች ነፀብራቅ ሆኖ እንደሚቀጥል ይገልፃሉ።

አንጋፋው ሰአሊ ኢትዮጵያውያን የተጎናጸፉትን ይህን ታላቅ ድል በአደባባይ አለማሳወቃችን እየጎዳን ነው የሚል እምነት አላቸው። «ስለ ራስ አለመናገር» እንደ ነውር እየተቆጠረ መሆኑን በመጥቀስም፣ እውነት እንዳንናገር አፋችን ተሸብቧል ነው የሚሉት። ይህ ባህል መቅረት እንዳለበት አስገንዝበውም ትውልዱ በኪነ ጥበብ፣ ስነ ጥበብ እንዲሁም በተለያዩ ዘዴዎች የዓድዋን ድል ማጉላትና ለዓለም ማሳወቅ እንዳለበት አስታውቀዋል።

«ዓድዋ ለእኛ መሠረት መሆኑን ከድሉ ተገንዝቤያለሁ» የሚሉት አንጋፋው ሰዓሊ ልዑልሰገድ፣ ድሉ በማንነታችን የምንኮራ፣ ከማንም ምንም የማንፈልግ ለመገፋት እጅ የማንሰጥ መሆናችንን ያስተማረን በመሆኑ ትውልድም ከዚህ ሕይወት ልምድ መውሰድ እንዳለበት ያምናሉ።

እንደ እነ ጳውሎስ ኞኞ፣ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴና ሌሎች የጥበብ ሰዎች ይህንን አኩሪ ድል በተመሳሳይ በማሻገር ትውልድ እንዲማርበት ማድረግ ላይ መሥራት ይገባቸዋል የሚል እምነትም አላቸው። እርሳቸውም በስእል ሸራቸው ላይ የዓድዋን ጀግኖች ለመዘከር ብሩሻቸውን ማንሳታቸውን ገልፀው፣ መጪው ትውልድም ከዚህ ይማር የሚል መልዕክታቸውን ያሰፍራሉ። አባቶቹ በእምነታቸው፣ በንፅህናቸውና በአልበገር ባይነታቸው ያገኙትን ድል መጠበቅ ይገባዋል የሚል ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ለዝግጅት ክፍላችን ዝክረ ዓድዋ ድልን በተመለከተ ካነጋገራቸው ተፅእኖ ፈጣሪዎች መካከል አንዱ ነው። «እኔ ከዓድዋ ድል እና ታሪክ ሁሌም የሚደንቀኝ ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነው የመከሩበትና በጋራ ሆነው ልዩነታቸውን ሁሉ በመተው አገር ተወራለች፣ ዳር ድንበር ተጥሷል በማለት ሽማግሌ፣ አሮጊት፣ ወጣት ሆነ ጎልማሳ የአገራቸውን ዳር ድንበርና ነፃነት ለማስከበር መዝመታቸው ነው» ይላል።

በኢትዮጵያውያን መካከል ልዩነት ቢኖር እንኳ ኢትዮጵያውያኑ ልዩነቱ ከኢትዮጵያ በላይ እንደማይሆን የተረዱ ነበሩ የሚለው ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ በመካከላቸው ቅሬታ ያለባቸው ሁሉ «ይቅር ለእግዚአብሔር» ተባብለው በአንድነት በመትመም ግማሽ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጦርነቱን በድል እንደተወጡ ይገልፃል።


ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ

ይህ በጭቆና ስር ለነበሩት አገራት በሙሉ ብርሃን ያሳየ መሆኑንም ያስረዳል። ከዓድዋ ጦርነት በተለየ መልኩ የሚስበውና የተማረበት እውነት ይህ መሆኑን ጠቅሶም «መከራን፣ ጭቆናን፣ ተገዢነትን ማሸነፍ ይቻላል። ነፃ መውጣት ይቻላል» የሚል አስተምህሮ ዓድዋ ተራሮች ላይ ለዘላለም እንዲቀረጽ ማድረጉ ከሁሉም በላይ ድሉን ልዩ እንደሚያደርገው ያብራራል። ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ ድል ከማድረጋቸውም በላይ ለመላው ጥቁሮች ብርሃን መፈንጠቁ ዳር ድንበርን ከማስከበር ባሻገር ኅብረትን የሚያሳይ መሆኑን እንደተረዳ ጋዜጠኛው ይናገራል።

«ጦርነቱን ለማስተባበር፣ ወረኢሉ ለመክተትና ከመላው ኢትዮጵያ ሰራዊቱ ዓድዋ ላይ እስኪገኝ በጥቅሉ አስር ወራትን ፈጅቶ ነበር» የሚለው ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ፣ በመካከል ልዩነት ቢኖር፣ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ የጠሩት ክተት ላይ መተማመን ቢጠፋና በአንድ ኢትዮጵያ መፅናት የጋራ አላማ ባይኖር መተማመን ጠፍቶ ድል አይገኝም ነበር ሲል ያብራራል።

ንጉሠ ነገሥቱ ለአስር ወራት ግንባር ላይ ሲቆዩ ራስ ዳርጌ የኢትዮጵያን መንግሥት ሲመሩ እንደነበር፤ ይህም አንድ የጋራ አገርና ህብረት እንደነበር ትልቅ ምሳሌ እንደሆነም ይገልፃል። በዚህም ኢትዮጵያውያን በኅብረት የደመቁበትና ፍቅርን እንደሸማ የተላበሱበት ድል እንደሆነና በልዩነት ይህ እውነት ለእርሱ ትልቅ ትምህርት እንደሆነ ይናገራል።

«የዓድዋ ድል የኢትዮጵያዊነት፣ የነፃነት፣ የአንድነት፣ የፍትህ፣ የእኩልነት፣ የፅናት፣ የእምነት ሁሉ ትምህርት ቤት ነው» የሚለው ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ፤ ከዚህ ትውልዱ ብዙ መማር እንደሚችልም ይጠቁማል። የዓድዋን ታሪክ መረዳት፣ ማንበብ፣ መመርመርና ማወቅ እንደሚያስፈልግ አመልክቷል።በተለይ ኢትዮጵያዊነት ከምንም በላይ እንደሆነ ማሳያ መሆኑን አንስቶ፣ ኅብረትና አንድነት ካለ ኢትዮጵያውያን ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል እንደማያሸንፋቸውና እንደማያንበረክካቸው እንዲገነዘቡ የሚያደርግ መሆኑን ይገልጻል፤ ይሄ ትውልድም ከዚህ መማር እንደሚኖርበት ያስገነዝባል።

ጣሊያኖች ብዙ ጄነራሎች፣ የጦር መሪዎችና ወታደሮች ሞተውባቸው ጦርነቱን ሲሸነፉ ጭፈራና የድል ፈንጠዝያ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አልነበረም ያለው ጋዜጠኛ ጥበቡ፣ እንዲያውም እቴጌ ጣይቱ «የሞተው የሰው ልጅ ነው፤ ምንም ጭፈራ አያስፈልግም» በሚል አስከሬናቸው ፍትሃት ተደርጎለት እንዲቀበር መደረጉንም ነው የጠቀሰው።ጋዜጠኛ ጥበቡም ከዚህ ታሪክ ቅንነትን፣ እምነትንና ፅናትን መማር እንደሚቻል አንስቶ ትውልዱ ከዓድዋ ድል ይህንን እውነት እንዲገነዘብ ጥሪውን አስተላልፏል።

# ሌላኛው ዓድዋ- የአበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ ድል

ቦጋለ አበበ

ታላቁ የዓድዋ ድልና የአበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ድል ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ሁሌም አስገራሚና እንደአዲስ የሚነገር ነው። ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ቅኝ ገዢው ጣሊያን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እስካፍንጫው ታጥቆ ለመውረር ሲመጣ እጅግ ኋላ ቀር በሆነ መሣሪያ በወኔ፤አልሸነፍ ባይነትና አስደናቂ ጀግንነት ድል ተደርጎ ተመልሷል። ይህም በጥቁር ሕዝቦች የጦርነት ታሪክ ሕያው ድል ሆኖ ከመዘከሩ ባለፈ በዓለም ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ ተዘርዝሮ የማያልቅ ተጽዕኖ ማሳደር ችሏል። የአበበ ቢቂላም የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ድል ተመሳሳይ ነው። አበበ የአባቶቹን ሀገር በግፍ ለመውረር በመጣው ጣሊያኖች ሀገር በወቅቱ ዘመናዊ ሥልጠናና ዝግጅት አድርገው ምቹ የመሮጫ ጫማ ካጠለቁ አያሌ ነጮች ውስጥ በባዶ እግሩ አፈትልኮ ሌላኛውን የዓድዋ ድል ተምሳሌት ሮም ኦሊምፒክ ላይ ፈጽሟል። ይህም ድሉ በኦሊምፒክ መድረክ የጥቁር አትሌቶች ፋና ወጊ ድል ከመሆኑ ባሻገር ልክ እንደ ዓድዋ ሁሉ ጥቁሮች በስፖርቱ መድረክ ቀና ብለው እንዲሄዱ የማይፋቅ አሻራውን አሳርፏል።

በዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች ጥቁሮች አሁን ላይ በየትኛውም ዓለማቀፍ መድረክ ተፎካካሪ እንዲሆኑ ከማስቻል ባሻገር በትልቅ ደረጃ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ለማሳየት በርካታ ጥቁር ከዋክብት ብዙ ችግሮችን ተጋፍጠዋል። በተለይም ጥቁር አሜሪካውያን አትሌቶች በዚህ ረገድ ያዩት ፈተና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም።

አፍሪካውያንም ቢሆኑ በርካታ መከራዎችን ተጋፍጠው ለታላቅ ክብር በመብቃት ለአሁኖቹ አትሌቶች ፋና ወጊ ሆነው እኩልነትን ማንፀባረቃቸው አይካድም። ለዚህም ታሪካዊውን ኢትዮጵያዊ የማራቶን ኮከብ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ በትልቁ የሚነሳ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆኖ እናገኘዋለን።

ኢትዮጵያውያን በስፖርቱ ብቻም ሳይሆን በዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌትና የማዕዘን ድንጋይ ሆነዋል። የጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል የሚዘከርበት የካቲት ወር በመላው ዓለምም የጥቁር ሕዝቦች መታሰቢያ ሆኖ ይከበራል።

በስፖርት መድረክ ዘረኝነትን የታገሉ፤ እኩልነትን ያንፀባረቁና በድላቸው የጥቁር ሕዝቦችን አንገት ያቀኑ በርካታ ጥቁር ከዋክብቶች መኖራቸው አይካድም። ከነዚህ ከዋክብቶች ግን ተፅዕኗቸው ከፍተኛ የነበረ፤ ድላቸው በርካታ ትርጉም የነበረውና በትልቅ ደረጃ ከሚነሱት መካከል የታላቁ ዓድዋ ድል ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንቁ ልጅ አበበ ቢቂላና የሮም ኦሊምፒክ ሕያው የማራቶን ድል ተጽዕኖ ቀላል እንዳልነበረ በብዙ ድርሳናት ተጽፎ ይገኛል።

1928 ፋሺስት ጣሊያን በአምባገነኑ ቤኒቶ ሞሶሎኒ በመመራት ኢትዮጵያን ከወረረ ከሃያ አራት ዓመታት በኋላም ታላቁ አበበ ቢቂላ ታላቋን ሮም በባዶ እግሩ ወሮ ዓለምን ጉድ አሰኘ። የምንጊዜም የማራቶን ንጉሡ የአፍሪካውያን ኩራትና የነፃነት ተምሳሌት እንዲሁም፤ የመጀመሪያው ጥቁር የማራቶን ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ በጥቁሮቹ በጀግኖች መታሰቢያ ወር የካቲት የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆኖ ከስልሳ ዓመት በፊት በኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት ዋዜማ በሮም ኦሊምፒክ የፈፀመው ታሪካዊ ጀብድ በመላው ዓለም ያሉ ጥቁር አትሌቶችን በእጅጉ ያኮራና ያነሳሳ ነበር።

ጳጉሜን 5 ቀን 1952 አስራ ሰባተኛው የሮም



ኦሊምፒያድ በታላቋ ሮም ጎዳናዎች በርካቶች ዓይናቸውን ለማመን የተቸገሩበት ጀብድ በአምባገነኑ ሞሶሎኒ አገር በበርካታ ነጮች መሐል አንድ ጥቁር በባዶ እግሩ ይጽፈዋል ብሎ ማንም አልጠረጠረም። ልክ እንደ ዓድዋ ድል ሁሉ የጥቁር ሕዝቦች ተዓምርን ለመቀበል የሚተናነቃቸው ዘረኝነትን በደማቸው ያሰረፁ ነጮች እንዴት ይህ ሊሆን እንደቻለ አሁንም ድረስ ግራ ይጋባሉ። አፍሪካውያንን ያኮራ ኢትዮጵያውያንን ከልብ ያስፈነጠዘው ታሪካዊ ድል በአበበ ቢቂላ ቀጫጭን እግሮች በወርቅ ቀለም መጻፉን ግን እየተናነቃቸውም ቢሆን ሊያላምጡት ተገደዋል።

ከ83 አገራት የተውጣጡ ከ5ሺ በላይ አትሌቶች በተካፈሉበት የሮም ኦሊምፒክ፤ የዓለም ሕዝብ ትኩረት በአውሮፓውያን አትሌቶች ላይ ነው፤ ስለኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተለይም ስለ አበበ ቢቂላ የሚያውቀው ነገር አልነበረም።አበበ ቢቂላ ወይም ሌላ አፍሪካዊ አትሌት ሊያሸንፍ እንደሚችል አልተጠበቀም። ከዚያ በፊት አንድም አፍሪካዊ በኦሊምፒክ ታሪክ ሜዳሊያ አግኝቶ አያውቅም።።።

የሮም ኦሎምፒክ የማራቶን ውድድር ግን፤ የዓለምን ታሪክ ቀየረ።የውድድሩ ውጤት፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፤ ለመላው አፍሪካና ለዓለም ጥቁር ሕዝብ ድል ያበሰረ ችቦ አቀጣጣለ። ኢትዮጵያዊው አትሌት አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጦ ታላቁን የኦሊምፒክ ማራቶን በአንደኝነት ከማሸነፍም በተጨማሪ፤ 2፡5፡6.2 በሆነ ሰዓት አዲስ የዓለም ክብረወሰን አስመዘገበ። በኦሊምፒክ ታሪክ የሜዳሊያ ባለቤት ለመሆን የቻለ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ስፖርተኛ ሆኖ ስሙ በታሪክ መዝገብ በወርቃማ ቀለም ሰፈረ።

አበበ ቢቂላ የማራቶንን ርቀት ሮጦ ያሸነፈውና ሪከርድ ያስመዘገበው፤ በባዶ እግሩ መሆኑ ደግሞ የመላ ዓለም ስፖርት አፍቃሪዎችን በእጅጉ ያስደነቀ ነበር። የአበበ በቂላን ስምና የኢትዮጵያን ዝና በመላው ዓለም ተቀርፆ እንዲቀር አድርጓል። በዓድዋ ጦርነት ላይ የዘመቱ ኢትዮጵያውያን ባዶ እግራቸውን እንደነበሩ ያስታውሳል። ጋዜጠኞች አበበ ለምን ያለ ጫማ በባዶ እግሩ እንደሮጠ ጠይቀውታል፣ "ዓለም ሁሉ እንዲያውቅ ፈልጌ ነው" ሲል የተናገረው አበበ፤ "እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም የምናሸንፈው በጀግንነትና በወኔ እንደሆነ፤ ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ በመፈለጌ ነው" ብሏል።የዓድዋን የጦርነት ታሪክ እያስታወሰ።

የአራት ዓመት ታዳጊ ሆኖ እናት አገሩ ኢትዮጵያ በጣሊያን ፋሺስት ስትወረር መጥፎውን ጊዜ ገና ባልጎለበተ የሕፃን አዕምሮው የሚያስታውሰው አበበ ቢቂላ፣ ሃያ ስድስት ዓመታት ጠብቆ ታላቁን የሮም ጎዳና በባዶ እግሩ ወሮ የማይደገመውን ታሪክ አኑሯል።

ከአራት ዓመት በኋላም 1956 በድጋሚ ጫማ አጥልቆ በቶኪዮ ኦሊምፒክ ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር አሸንፎ ጥቁሮች በማይደፈረው ርቀት አሁን ላይ ቁንጮ እንዲሆኑ መሠረቱን ጣለ። እሱ በከፈተው በርም ቁጥር ስፍር የሌላቸው የማራቶን አትሌቶች ለዘመናት ለርቀቱ የተፈጠሩት እነሱ ብቻ እስኪመስሉ አሁን ድረስ በዓለም አደባባይ እያንጸባረቁ ነው።

አበበ ምናልባት ያንን ውድድር ባያሸንፍ ኖሮ የጥቁር አትሌቶች በተለይም የረጅም ርቀት ታሪክ ዛሬ ከምናውቀው ተቃራኒ ሊሆን እንደሚችል በርካቶች ይስማማሉ።

እርግጥ ነው በሮም ኦሊምፒክ አበበ ብቸኛው ተሳታፊ አልነበረም። ብቸኛው ወርቅ ያጠለቀም አትሌት አይደለም። በዚያ ኦሊምፒክ ከተሳተፉ ጥቁሮች መካከል ሌላ ባለድልም ነበር። አሜሪካዊው ጥቁር የቡጢ ተፋላሚ መሐመድ ዓሊ በቀላል ሚዛን የወርቅ ሜዳልያ ተጎናፅፎ ነበር። ቢሆንም ኦሊምፒኩ በመሐመድ ዓሊ ወርቅ ሜዳልያ እምብዛም የደመቀ አልነበረም። በወቅቱ ታሪክ የሚያስታውሰው ሌላ ክስተትም ነበር። ጊዜው ደቡብ አፍሪካ በአህጉራዊ ውድድሮች ለመጨረሻ ጊዜ ተሳትፋ የታገደችበት ነበር። የእገዳዋ ምክንያት ደግሞ ትከተለው በነበረ የአፓርታይድ ሥርዓት መሆኑ ነው። ቢሆንም የያኔ የሮሙ ኦሊምፒክ በመሐመድ ዓሊ የወርቅ ሜዳልያም ይሁን በደቡብ አፍሪካ መታገድ አይደለም የሚታወሰው።

ታዲያ በምን ይታወሳል? ያሉ እንደሆነ በውድድር ዘመኑ የማራቶን ሩጫ ያለ ጫማ ሮጦ የርቀቱ አዲስ ክብረወሰን ባስመዘገበው ኢትዮጵያዊ አትሌት ሻምበል አበበ በቂላ ነው። በወቅቱ በርካታ ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮች ቢከናወኑም አበበ ግን ታሪኮችን ሁሉ ልቆ የሚታወስ ድንቅ ታሪክ አስመዘገበ።

ያኔ፣ አይደለም አበበ ቢቂላ የሚባል አትሌት፣ ኢትዮጵያ ተብላ ስለምትጠራ አገርም የሚያውቅ ነጭ ብዙም አልነበረም። ይሁን እንጂ ውድድሩ በጣሊያን መካሄዱ እና የጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቅቆ ድል የመጨበጧ ወሬ ገና ከዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች የወሬ አጀንዳነት ባለመረሳቱ፣ የአበበ ቢቂላ ድል ገነነ። ለዚህም ነው ብዙዎች የአበበ ድልና ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች የጦርነት ድል ዓድዋ የሚመሳሰልባቸው ወይም የሚገጣጠምባቸው። አበበ ቢቂላ ለመጀመርያ ጊዜ በተሳተፈበት የማራቶን ውድድር አሸነፈ። የጥረት እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም።ጀግና፤ ጀግናን ያፈራል።

የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀሩ ባልተጠበቀው የአትሌት አበበ በቂላ ድል ተደምመው ደጋግመው፣ በባዶ እግር ሮጦ የወርቅ ሜዳልያ ስላገኘው ኢትዮጵያዊው አትሌት ተናገሩ። በውድድሩ ማግስትም የጣሊያን ጋዜጦች ‹‹ኢትዮጵያን ለመውረር የኢጣሊያ አገር ወታደር ሁሉ አስፈልጎ ነበር፤ ኢትዮጵያ ግን አንድ ወታደር ብቻ ልካ ድፍን ሮምን ወረረችው›› የሚል ጽሑፍ ይዘው ወጡ። ይህም አጋጣሚ ብዙ ጥቁር አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉ በር ከመክፈቱ በዘለለ ከቅኝ ግዛት ለመላቀቀ የነጻነት ትግል በማድረግ ላይ ለነበሩ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የ”ይቻላል” መንፈስና ትልቅ የስነልቦና ስንቅ ሆኗቸዋል።

የአበበ ቢቂላ አንፀባራቂ ድሎች ለአፍሪካውያን በፋና ወጊነት ጠቅሟቸዋል። በኩራችን ብለውም ሰይመውታል። አዲስ አበባ በ2000 ዓ.ም. ያዘጋጀችውን 16ኛውን የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አጋጣሚን ምክንያት በማድረግ በ50 ዓመታት ውስጥ ለአፍሪካ አኩሪ ታሪክ የፈጸሙ አትሌቶች ሲሸለሙ፤ አውራው ተሸላሚ አበበ ቢቂላ ነበር። ‹‹የአፍሪካ ማራቶን አባት›› ተብሎም በዶክመንተሪው ፊልም ላይ ተመልክቷል።

አፍሪካውያን ለአበበ ያላቸው ፍቅርና አክብሮት እስከዚህ ድረስ ነው አይባልም። የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሴኔጋል መዲና ዳካር በ1971 ዓ.ም. ሲጀመር ወደ ዳካር ስታዲየም የሚያስገባውን መንገድ ‹‹አበበ ቢቂላ ጎዳና›› በማለት መሰየሟ ይታወሳል። ኢጣሊያም ብትሆን ለአበበ ክብሩን አልነፈገችም። የሮም ኦሊምፒክ 50ኛ ዓመትን ስትዘክር አንድ ድልድይ በስሙ ሰይማለች።

አምስተርዳም ከተማም የአበበ ቢቂላ መንገድ አላት። ‹‹ቶኪዮ ኦሊምፒያድ›› በተባለው የትረካ ፊልም ላይ የአበበ ቢቂላ የቶኪዮ ድል ተጨምሯል። ከዚሁ ፊልም የተወሰደ ክፍልም በ1968 በተሠራው ‹‹ማራቶን ማን›› በተባለው ፊልም ላይ ይገኛል። ‹‹ቪብራም›› የተባለ የአሜሪካ የጫማ አምራች ድርጅት በ2002 ‹‹ፋይቭ ፊንገርስ ቢቂላ” (Five Fingers Bikila) የተባለ ጫማ ለገበያ አቅርቧል።